መዲና

ዲጂታል መጽሔት

ቅጽ ፡ ቁጥር ፩



መጣጥፍ | ሒስ | ፈርማታ | ወግ | ግብዣ | አፍታ | ሽርሽር | ልብወለድ | አርኬ | አጤሬራ | እንቆቅልሽ

@MEDINAMAGAZINE

ነሐሴ
2016ዓ.ም

ቀዳሚ ቃል

መዲና ዲጂታል መጽሔት በዚህም ወር በስድስተኛ እትሟ እንደተለመደው ትጥቋን አሳምራ ወደእናንተ ደርሳለች። እፍታው፣ ቤት ለእንግዳው፣ አጨሬራው፣ ልቦለዱ፣ መጣጥፉ፣ ሒሱ... ያጎደለችው የለም። እንግዳ አምደኞችንም አካትታለች። እንደልምዷ በቅርብ ያጣናቸውን የኪነ ጥበብ ሰዎች፣ በሩቅ የምንዘክራቸውንም ታነሳሳለች። በተለይ በዚህ ወር እንደ ተዋናይ ኩራባቸው ደነቀ እና ተዋናይ ጌታቸው እጅጉ ያሉ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎችን አጥተናል። ይህን እትም ለእናንተ ለአንባቢዎቻችን ለማድረስ በምንሠራባቸው የመጨረሻዎቹ ቀናት ደግሞ የታላቁን ምሑር የፕሮፌሰር አንድርያስ እሸቴን ዜና እረፍት ሰምተናል። ምንም እንኳ በታሪክ አጋጣሚ በበጎም በክፉም ቢነሱ፤ ፕሮፌሰር አንድርያስ እሸቴ ግን ኢትዮጵያ አሉኝ ከምትላቸው ትልልቅ ጭንቅላቶች መካከል አንዱ እንደነበሩ የሚክድ የለም። ለሁሉም ቤተሰቦች ፈጣሪ መጽናናቱን ይስጥልን።

ነፍስ ይማር!

ልስሽፋን ምስል መነሻ(Inspiration) ከpinterest reelstore ከሚባል ገጽ የተወሰደ።
የዚህ የማውጫ ገጽ ምስል ደግሞ፡ ከፍሊከር የተወሰደ።





ቅጽ 1፥ ቁጥር 6







ማውጫ

የማለዳ ናፍቆት 3
ሳሚያ ጡሀ

ቤት ለእንግዳ 9
መዲና

ታላቁ አቤ 24
ብሥራት መብራቱ

ሐዲስ አድባር 27
ቃለአብ አባይነህ

ሕይወት ዘለሰኛ 35
ቤዛዊት

ዋቢ ሳቢ 55
ሚሊየን

Remember me 58
መስፀድ ጀማል

የክረምት ቀለም 65
በረከት ጌታነህ

የት ይመስላችኋል? 75
ቤዛ ተዘራ

ወግ| ፌርማታ| ሽርሽር| ግብዣ| እንቆቅልሽ



የመጣሁደ ናፍቆት...

ደራሲ | ሳሚያ ጡሀ

በጠዋት ዓይኔን ስገልጥ ማታ ከራስጌዉ በኩል አብርቷት በነበረችዉ መብራት ምትክ ከበሩ በኩል ወደ ውስጥ የሚዘልቀው የጧት ጮራ ብርሃን ሙሉ ክፍሉን እስከ'ኔ ወርሷል። ለብሼው የነበረው ብርድ ልብስ ግማሽ አካሌን አልብሶ የተቀረዉን ጭኔን እንዳራቆተ ተዝለፍልፎ መሬት ስሟል። የተበተነው ጸጉሬ አንገቴን ቀብሬ ከተኛሁበት ትራስ ጋር በአንድ ላይ እንደዳዋ ውጦኛል። በበር የገባው የፀሐይ ብርሃን በስሱ የተገለጠ ጭኔን ሲዳብሰኝ ይሰማኛል። ቀና ስል ፊት ለፊቴ የሚታየኝ ትልቅ የመጽሐፍ ሼልፍ አለ። ከዚያ ቀጥሎ በቀኝ በኩል የተዘረጋ ትልቅ ጠረጴዛ ተንጋሏል። በሁሉም ላይ ብዙ ዓይነት መጽሐፍ ተደርድሯል ።

መጀመሪያ ቀን ስመጣ እዚህ መደርደሪያ ላይ ነዉ ዓይኔ ያረፈዉ።

***

መጀመሪያ ቀን...

[ከሰውም ሰው አለ ከቀንም አለ ቀን
እንደ ዋዛ እንደ ቀልድ እኛን ያላመደን]

በሙያዬ አካውንታንት ስሆን ከምሠራበት መሥሪያ ቤት ተዘዋውሬ ወደ ደሴ ከመጣሁ ወር ቢሆነኝም ሳምንት የቆየሁ እንኳ አልመሰለኝም ነበር። ሕይወቴ አዲስ ነገር ሲጠፋው ይጨንቀኛል። አዲስ ሰው መተዋወቅ፣ አዲስ ከተማ ማየት፣ አዲስ መጽሐፍ፣ አዲስ ሙዚቃ ሲኖረው ነው ሕይወት የሚያጓጓኝ። አንድ ወዳጄ እንደውም "ጭር ሲል አልወድም" ብዬሻለሁ አንቺን እያለ ይስቅብኛል። ከሰሞኑ ዝም ያለ ሕይወቴ ላይ ምን ልጨምር ስል "ለምን ወጥቼ ቡና አልጠጣም? ለምን መጽሐፍ አልገዛም?" ብዬ ከቤት ወጣሁ። ከተማው ላይ ዞር ዞር እያልኩ መቃኘት ጀመርኩ። ደሴን አስሳለሁ... ቧንቧ ውኃን ይዤ መናፈሻን አሳብሬ፣ ሼልን ታክኪ በፒያሳ እያለፍኩ፣ አራዳን እንደ አደባባይ ዙሬ ሼልፍ ተራን አዳርሼ ሳበቃ፣ ብዙ ሳልደክም መጽሐፍ ቤት አገኘሁ። ወደ ውስጥ እንደዘለቅኩ አንድ እፈልገው የነበረ መጽሐፍ ላይ ዓይኔ አረፈ። ተክለፍልፌ ስንጠራራ እጄ አይደርስም። ምናልባት መጽሐፍ ሻጩ ይረዳኝ እንደሆን ለመጠየቅ ወደ ኋላዬ ስዞር ከአንድ ሽጋ፣ ለግላጋ ወጣት ጋር ተላተምኩ። እየሳቀ ያየኛል። ግራ በመጋባት አፈጠጥኩበት።

"እያየሁሽ ነበር ስትቸገሪ። የትኛዉን ፈልገሽ ነው?"

ድምፁ የሆነ ቦታ የማውቀው ይመስለኛል፤ የትም ሰምቼው የማላውቅም ዓይነት ይመስለኛል። የሙዚቃ መሳሪያ ይመስለኛል። ረቂቅ ሙዚቃ ይመስለኛል፤ እንደ ጃዝ፣ እንደ ብሉዝ ያለ ነገር። ወይንም የወፎች ዝማሬ፣ የወንዝ የጅረት አወራረድ አይነት? ድምፁን ከማውቀው ድምፅ ጋር ሁሉ ሳመሳክር በጎኔ አልፎ ሄዶ የተንጠራራሁበት ሼልፍ ላይ መጽሐፉን መዝዞ አቀበለኝ ።

"ይሄን መጽሐፍ መሰለኝ የፈለግሺው?" ሲለኝ ባነንኩ ።

"አ... አመሰግናለሁ በጣም!" ብዬ መጽሐፉን ተስገብግቤ ከእጁ ወስጄ ወደ ሻጩ ቀረብኹ። የመጽሐፉን ዋጋ ከፍዬ ስወጣ ከበሩ አልፎ ወደቀኝ ታጥፎ መንገዱን ሲይዝ በፊቴ ዉልብ አለኝ። 'ይሄ ሰው ማነው?' ይለኛል ውስጤ ። በደመ ነፍስ ከኋላው እራመዳለሁ። በእጁ አንድ ትልቅ የታሪክ መጽሐፍ እና አንድ ሌላ የሩስያዊውን ደራሲ የዶስቶቭስኪን 'ወንጀልና ቅጣት' ይዟል። ሲራመድ ቃዳ ቃዳውን[1] ነዉ። እንኳን ተራምጄ ሩጩ የምደርስበት አይነት አይመስልም። ቀለል ያለ ሸሚዝ በቲሸርት ነዉ የለበሰው። ጸጉሩ ተንጨባሮ ሲራመድ ወደ ግማሽ ጎኑ ይዘናፈላል። የምንሄድበት መንገድ ወደ አንድ ሆነ መሰለኝ፤ በታጠፍኩበት መንገድ ከቅርብ ርቀት አየሁት። ልቤ ግራ ሲጋባ ይሰማኛል። ቃል ሳላወጣ በሆነ አይነት መልኩ ከኋላዉ እራመዳለሁ። ከትንሽ ደቂቃ የተራራቀ እርምጃ በኋላ ወደ ጀርባው ዘወር ሲል ዓይን ለዓይን ተጋጨን።

ደንግጫለሁ! ወይንም አልጠበቅኩም ይዞራል ብዬ። እንዳየኝ ተረጋግቶ ቆሞ እርሱ ጋር እስክደርስ በፈገግታ ያየኛል። እንደደረስኩ "የምትፈልጊዉን መጽሐፍ አገኘሽ?" ሲል ከቅድሙ ፈገግታ ጋር ነው። ይሄ ፈገግታና ይሄ ድምፅ የሆነ ቃና አለው። አሁንም እንደቅድሙ አይነት የድምፅ ጎሰሳ ውስጥ ሳልገባ ቶሎ ብዬ አእምሮዬን ተቆጣጥሬ መልስ ለመስጠት ተሽቀዳደምኹ። "አዎ! አገኘሁ። አመሰግናለሁ በድጋሚ።" አልኩ (አሁን አፈ ሰልቶልኛል።)

"እ... ሳንተዋወቅ ፈራህ እባላለሁ።" አለኝ።

'ህህ እውነትም ፈራህ[2]...' አልኩ በልቤ።

***

በእንዲህ አይነት ትውውቅ የተጀመረው ጓደኝነት በሳምንታት የቅርርብ እድገት አሳይቷል። አብሮ ቡና መጠጣት፣ ሃሳቦች ላይ ማውራት፣ አብሮ መጽሐፍ መግዛት ተጀምሯል። ስለእርሱ ውስጤ የሚሰማኝ አንዳች አይነት የእንግድነት ስሜት የለም። ስለ ግል ጉዳይ ብዙ አናወራም። ስለራሳችን በዚያ መጠን የማናወራበት ምክንያት ባይገለጥልኝም እንዲሁ ግን ተቀብለነው እንኖራለን።

ፈራህ የሳቅ አምባ ነዉ። በችምችም ጥርሶቹ አምባ ላይ ሆኜ ሳይ ውስጤ የሚጫር ንጋት አለ። የሆነውን አይነት መጽሐፍ ይዞ በዚያ ሳቁ እየተብረቀረቀ ሲጠጋኝ ካሉብኝ ችግሮች ሁሉ፣ ከመኖር ውጣ ውረድ... ወደእርሱ አርፋለሁ። ዓይኔ ዓይኑን ሲስም ያለ ቦታ ብቻዬን እንሳፈፋለሁ። እንደ ሚስቲክ[3] እስከ ቀሚሴ ዓይኔ ተከድኖ በምህዋሩ ዙሪያ ስንሳፈፍ ይሰማኛል። የተማሩት ሒሳብ ከፍቅር አያስጥልም። ያነበብኩት፣ የመጣሁበት ስሌት ሁሉ

1. ቃዳቃዳውን - (ዘዬ) በረጅሙ ይራመዳል እንደማለት
2. ፈራህ - አረብኛ ቃል : فَرَح , farah ደስታ....እንደማለት
3. ሚስቲክ(Mystic)-በፀሎትና በመመሰጥ ከአምላክ ለመገናኘት የሚሞክር፣ ረቂቅ

እርሱን በወደድኩበት መውደድ ልክ በዜሮ የሚባዛ ነው። በረጃጅም ክንዶቹ ሲያቅፈኝ እንደአክቶፐስ ተላጥቄ መቅረት ያምረኛል። ሳላውቀው ወደ'ርሱ ተንሸራትቼ በማላውቀው ስበት እጠጋዋለሁ። ሁሉ ነገሬን ትቼ ተከተልኩት፤ ኩራቴ እርሱ ጋር ዋጋ እስኪያጣ ይሉኝታ አልነበረኝም።

የመከተሌ ጥግ ቤቱ ድረስ ይሰበኛል። "ቤት እንሂድ! ቡና እጋብዝሻለሁ። ምናልባት የምትወጂው መጽሐፍ ካለ ትወስጂያለሽ።" ሲለኝ ባንዳ'ፍ አልኩ።

***

ቤት እንሂድ?

[ሰው ከማይደርስበት ጋራ ስር ነዉ ቤትህ...]

ቤቱ ፀጥ ያለ ሠፈር ዉስጥ የሚገኝ አንድ ሰፊ ግቢ ነው። የሠፈሩ ፀጥታ ከሚሰማኝ የፍቅር ስሜት ጋር አብሮ ሁሉ ውስጤን አንዳች መደርበብ ዉስጥ ከቶታል። ለጥ ያለ ሜዳ አልፈን ስንሄድ "ከከተማ ውጪ ነዉ እንዴ የምትኖረው?" እያልኩ እስቅበታለሁ። ቤቱ ገብተን ቁጭ ስል እያወራኝ ዓይኔን ስገባ ካየሁት የመጽሐፍ ሼልፍ ላይ አልነቅልም። ፈገግ እያለ ያየኛል።

"ምግብ ትበያለሽ?" ይለኛል።

እንደማልፈልግ ራሴን በአሉታ እነቀንቃለሁ።

ብዙ አያወራም። ግን ብዙ ይከውናል። ብዙ ያነባል፤ ጭስ ያጨሳል። ጭሱ መሐል ዓይኔን አጥብቤ አየዋለሁ።

ዝም ስለው ከእጁ የማይለያትን መጽሐፍ ይከፍታል። 'የአዳምን ማህሌት ታቂያታለሽ? እ...' እያለ አጠገቤ ይቀመጣል። እዚህ መሀል እየሆነ ያለው ሁሉ፤ ድባቡ አኳኋኑ ሁሉ ፊልም ይመስላል። እስኪ አንዴ እዚች ጋ አቁሜ ልየዉ አይሉበትም እንጂ እዉነት ፊልም ይመስላል። ጋቢውን አምጥቶ በስሱ ጣል ያደርግልኛል። ፍቅር ለሆነ ሀጃ እዚህ የተገኘ ይመስላል። እዚች ላይ ብቻ መብራት እንደማብራት፤ ዙርያ ገቤ ጨልሞ እኔነቴ ላይ ብቻ ወጋገን ሲያጥለቀልቀኝ ይሰማኛል። እቅፉ ዉስጥ አስገብቶ ማህሌትን ያነብልኛል። ይሄን መጽሐፍ ስንቴ አንብቤዋለሁ? ስንቴ ይዤው ዞርኩ? እርሱ ሲያነበው ግን ሌላ ምትሐት ይመስለኛል። አፈን ከፍቼ እሰማለሁ፤ እንዳ'ዲስ ....

***

የሚያነብ ወንድ በሆነ በማላውቀው አይነት ስሜት ወደራሱ ይስበኛል። ከዚህ ከሚያምር አቋሙ፤ ከሉጫ ጨብራራ ጸጉሩ (እየተጠቀለለ የሚዘናጠፍ ነገር)፤ ከዘናጭነቱ፤ ከምወድለት ቲሸርቶቹ፤ ከሚያደርገዉ ቁንጠኛ መነፅር፤ ከሳቁ (አወይ ሳቁ እና ጥርሶቹ)፤ ከዚህ ሁሉ በላይ አንባቢነቱና እቺን የምታምር ቤቱን እወዳለሁ። እቺኑ እዚችሁ ላይ ደጋጌሜ ብኖር እላለሁ። ሳልወጣ ከእቅፉ የሆነ የሆነ ዘመን ቢያልፍ እላለሁ...

እነዚህ ቀኖቹ መሀል ስሆን ስስምው ብቻ አስባለሁ። ሳቅፈው ብቻ፤ ስጠጋው ብቻ። የቀኔ ጠዋት ላይ ውስጤ በባዶነት ሲማታ ሙላት እንዲሆን ብዬ ወደውስጡ ለመጠጋት የጋቢ ሙቀት ስንጋራ የሆነ ነገሩ ልቤን ሲያብረከርከው ይሰማኛል። (ለልብ ተብረከረከ ይባላል ?) ...ሁሉ ፀጥ ይልና እሱ ብቻ ይኖራል ሁለንተናዬ ውስጥ ። አሁን እዚህ መሀል ሥራዬ ፀጥ ብሏል። ዓለም፤ ልሄድበት ያሰብኩበት ቦታ፤ የነበርኩበት፤ ያለሁበት ጊዜና ሁናቴ

ሁሉ። ቤተሰብ፣ ጓደኛ፣ የዚህች መኖር ግሳንግስ፣ የጦርነት ጥበቷ፣ ድህነቱ፣ ድህነታችን፣ ዓለም በራሷ፣ ሁሉ ሁሉ ለአፍፍፍፍታታታ...

ፀጥጥጥጥጥታታታ!

እንዲህ ፀጥ ሲል እኔ ግን አስባለሁ። ለምን እንደምለፋ ያን ሁሉ? ይሄን ሁሉ?

አሁን እዚህ መሀል እየባከንኩ ይሁን እየኖርኩ አይገባኝም። ግን በዚህም መንገድ አልፋለሁ።

ሰው አልፎብኝ የሚሄድ መንገድ ልሁን መልካ፣ ወይንም ዳናቸውን የሙጥኝ የምል የአሸዋ መንገድ አላቅም። ግን አስባለሁ። 'አሁን እዚህ አንተ ጋ የሆነው ትዝታ ሆኖ ይቅር፣ የሚነሳ ታሪክ ይውጣው አላውቅም። ጊዜና ቦታ እንደአበባ ቆሞ የሚታይ፣ የሚዳሰስ ቢሆን ይህቺ ቅፅበት ፅጌዳዬ ናት።

የማልነግረው ነው ይሄ ሁሉ። (የተተወ የአእምሮ ክፍል አለኝ፣ መጽሐፍ እየሰማሁ በጎን የሚያብሰለስለኝ።)

እየተብሰለሰልኩ እግሩ ቀስ እያለ እግሬን ሲነካኝ ይታወቀኛል። እየሳመኝ ከተቀመጥኩበት ስንሸራተት ይሰማኛል። የለበስነው ጋቢ እያፈረን ሲሸሽ ፊቴን የምትነካኝ ጣቱ ወደ ወገቤ ቦታዋን ስትቀይር እኔነቱ እዚች ቦታ እየራደች ስትፈረካከስ ይሰማኛል። እርሱን የሆንኩ ያህል ወደ'ርሱ ስዋሐድ ይታወቀኛል።

***

ተመልሼ ወደ ንጋት...

በጠዋት ዓይኔን ስገልጥ ማታ ከራስጌው በኩል አብርቷት ከነበረችዉ መብራት ምትክ ከበሩ በኩል ወደ ውስጥ የሚዘልቀዉ የጧት ጮራ ብርሃን ሙሉ ክፍሉን እስከ'ኔ ወርሷል። ለብሼው የነበረው ብርድ ልብስ ግማሽ አካሌን አልብሶ የተቀረውን ጭኔን እንዳራቆተ ተዝለፍልፎ መሬት ስሚል። የተበተነው ጸጉሬ አንገቴን ቀብሬ ከተኛሁበት ትራስ ጋ በአንድ ላይ እንደዳዋ ውጦኛል። በበር የገባው የፀሐይ ብርሃን በስሱ የተገለጠ ጭኔን ሲዳብሰኝ ይሰማኛል።

እንደተነሳሁ አይቶ ነዉ መሰለኝ መጥቶ ግንባሬን ሳመኝ።

"ጥሩ እንቅልፍ ተኛሽ..?"

አሁንም ራሴን በአዎንታ ነቀነቅሁ።

ቃል ባወጣ የማፈስሰው ፍቅር ያለ ይመስል ዝም ብዬ ዓይኑን ብቻ አየዋለሁ። ‹ንዲህ ድቅቅ ብዬ ጠዋት ስነሳ ውስጤ የሞላው ፍቅር እንደውኃ ብቻውን በደሜ ሲራወጥ ይታወቀኛል፣ ግን አላወራውም። ተነስቼ ፊቴን እታጠባለሁ።

[ሀገር ቆርጦ ሲሄድ አይፈራም ነጋዴ
ካ'ንተ ጋር ልሞት ነው አልችል ቢለኝ ሆዴ]

አስቱ

አስቱ ሆዴ ያለች ናት። የምሰማት አይደለችም። ሆዴ ያለች ሙዚቃ ናት። አስቱን በሆዴ እያመላለስኩ ይሄን ይሄን አስባለሁ። ምን አለ መሰለህ? እዚህ ፊት ለፊቴ ወጣ ገባ ስትል ብዙ ነዉ የማስበው። እዚህ ብቻ አይደለም። ቤቴ ገብቼ አልጋዬ ላይ ዘፍ ስል ሁሉ ጭንቅላቴ ላይ ውልል ትላለህ።

የ'ኔ ብቻ ስለሆንክ ነው እንዲህ የወደድኩህ? አለ አ? ደስ የሚል ነገር ባይኖረውም እጅህን ስይዝ ያለፈውን ሁሉ ዘንግቼልሃለሁ። ብዙ ደስ የማይሉኝ ነገሮች'ኮ አሉ። አለ አይደለ? ግን እያወቅን ዘፍ ብለን የምንወድቃቸው አወዳደቆች ነገ ተነስተን እንደምንሄድ ሁሉ እርግጠኛነት አያስቀሩም። አውቃለሁ፤ ይሄ ሁሉ ነገር ዋጋ የለውም። ማነህ? ምን ነበርክ? የት? ከማን ጋር? የምልበት ምንም ሞራል የለኝም። ለምን ብትል ባለፈው እንደነገርኹህ ነው። ምናልባት አንተን በጥያቄ ስይዝ ራሴን ብቻ ወድጄ እንዳይሆን እሰጋለሁ።

እና አሁንም... አውቃለሁ፤ ወጣትነት ብዙ ስህተት መሀል እንደሚዘርር፤ ብዙ ቀን መሀል ደሞ ጥሎ እንደሚጠፉ። ግን እንደስህተትም ብትሆን እዚህ ነህ አደል?

የሆኑ ከመጣንበት እና ካለንበት መስመር የሚያፈነግጡ ነገሮች አሉ፤ የማይገቡን ግን የሚኖሩ... የምደብቅህ አበባ ነህ። የምወዳት አጭር ቀሚስ ነገር! የሆነ... ልኮራብህም፤ ልደምቅብህም፤ ልደብቅህም የማልደፍር አይነት...

እኔ እምልህ ማን ነህ?

እዚያ ብርድ ሀገርህ መሀል ሙቀት ሆነህ ተገኘህና ምን ይጠበስ?

ብክንክን እያልኩ አልጋዉን ሳነጥፍ ቁርስ ሠርቶ ያቀርባል። (ይሄ ልጅ እዚሁ ሊያስቀረኝ ነው? ምን እሠራለሁ እዚ? በጠዋት አልወጣም? ሀገሬ አልሄድም?

"ደገኛ ሙጠምጢሙ ከባድ ነው። እዚያ ብርድ መሀል በረደኝ ብለሽ ጠጋ እንዳልሽ እዛ'ው ተጣብቀሽ ነዉ 'ምትቀሪዉ።" የምትለኝ ጓደኛዬ ትዝ ትለኛች... ብቻዬን ሂሂሂ አልኩ፤ በሆዴ። ...እንደ ፍቅሩ

ከዚያ ወደ ቁርሱ...



ከበደች ተክለአብ

ገጣሚ እና ሠዓሊ



ደስ ይላል አበባ
ደስ ይላል መዓዛው
ደስ ይላል ቀለሙ
ደስ ይላል እንቡጡ...

አበባ - ከበደች ተክለአብ

ደስ ይላል





ቤት ለእንግዳ

ፀደይ ወንዶሙ (ዶክተር)
የሥነ ጽሑፍ እና Art Theories ባለሙያ

[ዶክተር ፀደይ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ በአለ ሥነ ጥበባትና ዲዛይን ጊቢ መምህር ናት። የመጀመርያ ዲግሪዋን ከአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ አግኝታለች። የሁለተኛ ዲግሪዋን ከአዲስ አባባ ዩንቨርሲቲ እ.ኤ.አ በ2007 ስትቀበልም መመረቂያ ጽሑፏን The Case of Existence in Fəqər eske Mäqabər, Kä'admas Bashagär and Gəracha Qachəloch: From Existentialist Perspective በሚል ርዕስ ነበር የሠራችው። የPHD ዲግሪዋንም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነው ያጠናቀቀችው። በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ ከማስተማሯ በፊት በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ታስተምር ነበር። የሒስ ሥራዎቿ እንደ 'መልክአ ስብሐት' እና 'መልክአ ዓለማየሁ' ባሉት ስብስብ መጽሐፍት ላይ እና እንደ ብሌን ባሉ መጽሔቶች ላይ ታትመውላታል። በተለያዩ የሥነ ጽሑፍ መርሐ ግብሮች ላይ በመገኘት እና ማኅበራዊ ሚድያውንም በመጠቀም ለየት ያሉ ሥነ ጽሑፋዊ ትንታኔዎችን በመስጠት ትታወቃለች። ከዚያም ውጪ ግጥሞችን፣ አጫጭር ልቦለዶችንም ትጽፋለች፣ ትተረጉማለች። የዛሬዋ እንግዳችንን ለማስተዋወቅ ከዚህም በላይ ማለት እንችላለን። ነሐሴ 1 ቀን 2016 ዓ.ም፣ ዘጠኝ ሠዓት ላይ አራት ኪሎ አካባቢ ተቀጣጥረን ተገናኘን። ትሑት ናት። በየመሐሉ ጥልቅ እያልኩ ከሀሳቧ ሳናጥባት በትዕግስት አዳምጣኛለች። የተጣመሙ እና የተሳሳቱ ጥያቄዎቼን እያቃናች መልሳልኛለች። ሥራ ሳላበዛባት አልቀርም እንደውም። መጀመርያ ጥያቄዬን ማቃናት! ለጥቆ ለ'ኔ ማስረዳት! በመጨረሻ መልስ መስጠት! እንደ አስተማሪነቷ ነገሮችን ከስር ከመሠረቱ የመመርመር ልምድ አላት። የዚያን ዕለት ጠዋት ሠዓሊ እና ገጣሚ ከበደች ተክለአብን ለመቀበል በ'አለ የሥነ ጥበባት ትምህርት ቤት' ውስጥ የተዘጋጀው ፕሮግራም ላይ ፀደይን አግኝቻት ነበር። ጭውውታችንን የጀመርነው በአጠቃላይ ስለከበደች ተክለአብ እና ስለጠዋቱ ፕሮግራም በመወያየት ነው።]

መልካም ቆይታ!

መዲና- ጠዋት የጠየቅሽው ጥያቄ ተመልሶልሻል?

ፀደይ- ነበርክ እንዴ?

መዲና- አዎ! ነበርኩ እኮ።

ፀደይ- ኦ! አሪፍ አሪፍ። አብረን የምንመጣውን ታዲያ።

መዲና- አዎ። አሪፍ ነበር። ከሰው ጋር ነበርሽ። እኔ ሙሉ ለሙሉ የተመለሰልሽ አልመሰለኝም።

ፀደይ- Partly ነው የመለሰችልኝ። አንዱ የጠየቅኳት የነበረው ለራሷ ያላትን... ለድምጽና ለቀለም የምትሰጠውን ትርጉም ነበር። ያው እርሷ ግንኙነታቸውን አብራራችልን።

መዲና- ሁለተኛው ደግሞ ከተጠቀመችው ምሳሌ አንጻር... ይኼ እንደውም በኮብልስቶኖች መካከል መራመድ እና በመካከሉ ስላለው ቦታ መሰለኝ።[1]

ፀደይ- አዎ! ከ'Being' እና ከ'Becoming' ጋር የተያያዘ ጥያቄ።

መዲና- ስትመልስልሽ መጀመርያ ወዳነሳችው የ'in between' ሃሳብ ወሰደችው።

ፀደይ- አዎ። ያው 'Journeyኡን ነው Becoming ያልኩት!' አለች። ነገሩ ያስኬዳል ስታየው። ያው Creativity... እ... ራስህንም መፈለጊያ ስለሆነ፥ የምትለዋወጥበትንም መንገድ ሬኮርድ ስለምታደርግ Becoming ጋር ሊያያዝ ይችላል።

መዲና- መንገዱ ነው እንጂ ውጤቱ አይደለም ዋናው... እንደማለት።

ፀደይ- ሂደቱ ነው። Journeyኡ ነው አለች።

መዲና- ያነሳችው ምሳሌ በጣም Specific ነው። እንዴት ከዚያ ጋር እንዳገናኘችው ነው ያልገባኝ።

ፀደይ- እርሱን እንድታወራኝ ነበር እኔም የፈለግኩት። እንዴት ነው በዚያ Space ውስጥ Becomingን የምትይዘው የሚለውን። ግን ምን መሰለህ። እዚያ ቦታ ላይ ስትሆን... ብዙ ጥያቄም ሲወረወር፥ ደግሞ የጻፈችውም አይመስለኝም ጥያቄውን... እርሱ እርሱም ተጨምሮ ነው። ግን ምናልባት ለብቻም መጠየቅ ይቻላል።

መዲና- አዎ! ልክ ነሽ! እዚህ ከመጣች አይቀር በደንብ መጠቀም አለብን።

ፀደይ- አዎ! አዎ! ደግሞ እንትኖቿ.... ከለሮቿ በጣም ደማቅ ናቸው። Vibrant ናቸው... ብዙዎቹ። አሉ አንዳንድ... ትንሽ ወደ Dark ነገር የሚወስዳቸው። የሚገርም

---

1. "...ለእኔ ግጥም መግጠም በንጣፍ ደንጊያ (Cobblestone) ላይ እንደመረማመድና፥ እየተራመድኩም የመርገጪያዬን ድንጋዮች የሚያገናኟቸውን ቀጫጭን መስመሮች ሳላስተውል ማስተዋል ነው።" ከበደች ተክለአብ ፥ ነሐሴ 11፥ በወመዘክር በተዘጋጀው የመጽሐፍ ምረቃ መርሐ ግብር ላይ በጽሑፍ ካነበበችው የተወሰደ። የነሐሴ አንዱ ፕሮግራም ላይ በአለ የሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት የተናገረችው በእንግሊዘኛ ከመሆኑ በቀር ልዩነት የለውም።

ነው በጣም። እንደገና ደግሞ የግጥምን Concept፣ የሙዚቃን Concept ነው የምትሰለው። እርሱ ነው አንድም Strike ያደረገኝ። እና ከVibration ጋር ምናምን አያይዛ መለሰችልኝ። ጥሩ ነው በጣም።

መዲና- ከከበደች ተክለአብ ወሬ ሳንወጣ በአጠቃላይ ስለሥነ ግጥም Craft ብናወራ... ግጥም ይተረጎማል? የሚተረጎም አይነት ነው ግጥም? አሁን የእርሷን Process ስለማላውቅ ነው እንጂ ግጥም የሚተረጎም አይመስለኝም። እርሷ ደግሞ ጠዋት ሰምተሻት ከሆነ... 'Inspirationኡ በተለያየ መንገድ ነው የሚመጣው። በግጥም የመጣውን በሥዕል አላወጣም፣ በሥዕል የመጣውን በግጥም አላወጣም።' ትላለች። ግን ከቋንቋ ቋንቋ ግጥም ትተረጉማለች። ሥዕል Remake ታደርጋለች። እንዴት ታዪዋለሽ ይኼንን?

ፀደይ- ምን ማለቷ መሠለህ... አሁን አንዳንድ ሃሳብ ተስተካክሎ ለግጥም የሚመች ሆኖ የሚመጣ አለ፣ ወደ ሥዕል ልቀይረው ብትል የሚያስቸግርህ... Capture የማይደረግ። በሌላ በኩል ደግሞ በቀለም የሚያዝልህ ሆኖ በቃላት የማይያዝልህ ሊሆን ይችላል። እንደእርሱ ማለቷ ነው።

መዲና- ልክ ነሽ እኮ። ግን ደግሞ ያልገባኝ... ለምሳሌ የሌላ ሰው ሥዕል አይታ እና Inspired ሆና ግጥም መጻፍ የምትችል ከሆነ፣ የሌላ ሰው ግጥምም አንብባ በእርሱ ተነስታ ሥዕል መሳል የምትችል ከሆነ... ለምንድነው ይኼ ሕግ ለራሷ የማይሠራው? በራሷ ሥዕል inspire ልትደረግ አትችልም ወይ? የሚለው ነው።

ፀደይ- እርሱን ነው የምልህ። Inspiration ነው። እርሱን አይደለም የምትተረጉመው። አንድ ቃል ልትሆን ትችላለች Inspire የምታደርገኝ። ሌላ እሳት እንደማለት ነው። ለምሳሌ ከጎረቤት እሳት ብወስድ ከሰሉ ምናምን የራሴ ነው። በቃ! መጫር ብቻ ነው የፈለግኩት። እዚህ ጋ ሌላ Idea ነው የማበስለው። ከዚያ ጋ አንድ ዓይነት ላይሆን ይችላል። ላይገጥምም ሁሉ ይችላል። እንደዚያ ማለቷ ይመስለኛል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሠዓሊው በሥዕል ብሎት አንተ ጋ ደግሞ በግጥም ሊመጣ ይችላል። እንደ Subjective Difference ማለት ነው። ሀሳቡ አንድ አይነትም ሆኖ አንዱ ጋ በሥዕል አንዱ ጋር በግጥም ሊመጣለት ይችላል።

መዲና- እሺ ከቋንቋ ወደቋንቋስ መተርጎም? ግጥም ሲሆን በተለይ...

ፀደይ- እርሱ ከባድ ነው። ይቻላል! ግን ከባድ ነው። ግጥም ሲሆን የሚያስቸግረው ምንድነው? Cultural ልዩነቶች አሉ። በዚያ ላይ ከስሜት ጋር በጣም Attached ነው ግጥም። እና ስትገልጠው በደንብ ላይመጣ ይችላል። የቃላት ልዩነት አለ። አንዳንድ ጊዜም ውስጥህ ያለው image እና ተርጓሚው ጋ ያለው image ሊለያይ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ግጥምን ወደculture ለማምጣት መጎተት አለብህ፣ ስሜት እንዲሰጥ። ምክንያቱም ግጥም ላይ አንዱ የሚፈቀድልህ Poetic License የሚባል ነገር አለ አይደለ? እርሱ ስላለህ ቃላቱን ልትሸራርፍ ትችላለህ፣ ልትቆራርጥ፣ ድምጾች ልታጠፋ ትችላለህ። እንደዚያ ስታደርግ በዚያኛው በሚተረጎምበት ቋንቋ ትርጉም ሁሉ ላይሰጥ ይችላል። ስለዚህ ወደ Cultureህ እንዲቀርብ የምትጎትተው ነገር ይኖራል።


መዲና- የእኔ ሃሳብ ደግሞ ምንድነው... ቅድም ለሥዕሉ ሌላ እሳት ነው አላልንም? ልክ እንዲሁ ግጥም ብተረጉም ሌላ ግጥም ነው የሚሆነው ነው።

ፀደይ- አዎ። ግን ምን መሠለህ? Essenceኡን መያዝ ትችላለህ። አሁን ትርጉም ሲሆን

Essenceኡ ነው ዋናው። መጨበጥ ያለበትን Idea ልትይዘው ትችላለህ። አሪፍ ተርጓሚ ከሆነ አንኳሩን መያዝ ይችላል። እርሱን ከያዘ ቃላቱ ሌላ ቢሆኑም፣ ዞሮ ዞሮ ግን ወደእዚያ ያመጣኻል። ዋናው እርሱ ነው።

መዲና- ስለዚህ ግጥም የሚያሰኘው Essenceኡ እስከሆነ ድረስ... ቅርጹንም ባይጠብቅ፣ መስመር በመስመርም ባይተረጉም በቂ ነው ማለት እንችላለን?

ፀደይ- እንደሁኔታው ነው። ለምሳሌ ግጥሙ መስመር በመስመር መተርጎም ያለበት ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ላይሆንልን ይችላል። ለምሳሌ ባለፈው ነቢይ [መኮንን] ተረጎመው ተብሎ ያየሁት ግጥም ነበር። ዋናው ባለአራት መስመር ግጥም ነው። እርሱ ጋ ግን ስምንት ነው ዘጠኝ መስመር ነው የሆነው፣ ከእንግሊዘኛ ሲያመጣው። ሃሳቡን ለመያዝ። ስለዚህ አንዳንዴ ሊመጣልህ ይችላል። በተለይ እነዚህ የተለመዱ አይነት ግጥሞች አሉ አይደለ? ቤት አመታታቸው ምናምን የሚታወቅ... መስመር ለመስመር ታግለህ ልታመጣው ትችላለህ። ምክንያቱም በባሕል ብንለያይም ሰው በሚለው ነገር ሁላችንም አንድ አይነት ስለሆንን ተመሳሳይ ስሜት ሊመጣ ይችላል። ግን Free Verse የምንለው አይነት Experimental የሆኑት ሊከብዱ ይችላሉ። አሁን ለምሳሌ... Concrete Poem የሚባሉ አሉ። እነዚህ ምንድናቸው? በግጥሙ ቅርጹን ራሱ ማምጣት። ለምሳሌ አንድ ግጥም ነበረ፣ 'Snake in the Grass' የሚል። *[አጠገቧ ያለ ወረቀት ላይ ከታች የተያያዘውን ጽሑፍ መሳል ጀመረች።]* እና እንደዚህ Exactly ላይሆን ይችላል። አየህ፣ እባቡን ራሱ ነው የሚሠራልህ ግጥሙ። አሁን ይኼንን 'እባብ በሣር ውስጥ' ብዬ ብተረጉመው ዋናውን Concrete Poem አያመጣልኝም። ግን ሌላ መንገድ ልጠቀም እችላለሁ። እና እንዲህ ያሉት Experimental የሆኑት ለመተርጎም ይከብዳሉ። እንኳን አይደለም ግጥም፣ Prose ም እንኳ ቢሆን ከባድ ነው ለመተርጎም።



መዲና- እሺ ወደዋናው ጉዳይ እንግባ።

ፀደይ- አልጀመርንም እንዴ?

መዲና- ጀምረናል እኮ።

ፀደይ- እኔ ደግሞ ሙሉ ሠዓቱን ስለእርሷ ብቻ የምናወራ መስሎኝ... ደስ ብሎኝ... ሂሂሂ

መዲና- አይ ወደያዝኳቸው ጥያቄዎች እንሂድ ለማለት ነው። እንጂ እኔም ደስ ይለኛል ስለከበደች ብቻ ብናወራ። ሂሂሂ...

ፀደይ- እሺ!

መዲና- ምን ያህል ጊዜ ሆነው ጥናታዊ ጽሑፉ?

ፀደይ- የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲው? ሁለት ሺህ.... ሰባት በፈረንጆቹ። 99 ማለት ነው።

መዲና- የPHD ጽሑፍሽስ?

ፀደይ- እርሱ ደግሞ 2007 ነው።

መዲና- ምን ላይ ነው የሠራሽው እርሱን።

ፀደይ- Spacetime realities in Ethiopian Postmodernist Literature: Convergence of Postmodernism, Physics and Mysticism የሚል ነው። ሦስቱን አገናኝቶ ለሥነ ጽሑፍ ትንተና መሥሪያ Tool እንደመፍጠር ማለት ነው። ሙከራ ነው።

መዲና- የትኞቹ ልቦለዶች ናቸው የተካተቱት?

ፀደይ- ያው አዳም [ረታ] አይቀርም። ሁለቱ አሉ፤ ግራጫ [ቃጭሎች] እና እቴሜቴ [የሎሚ ሽታ]። እ... የኦታም ፑልቶ። ከዚያ የስብሐት [ገብረ እግዚአብሔር] አለ። 'አምስት ስድስት ሰባት' ላይ ያለው። ራሱ 'አምስት ስድስት ሰባት' እና ፋንታሲው... 'ስምንተኛው ጋጋታ'። እና ሌሎችም አሉ። ይኼ ምንድነው የሚለው... 'ተከታትለው ሽው ወደቢሾፍቱ' የሚለው። እርሱም አለ። የዓለማየሁም [ገላጋይ]። ብቻ ስድስት ናቸው የተካተቱት [መጽሐፍት]።

መዲና- ፊዚክስ ትወጃለሽ አይደል?

ፀደይ- ማቲማቲክሱን ትተህ... ሂሂሂ... አዎ። ሒሳቡንም ቢሆን በደንብ ስላላስተማሩን፤ ለእኔም ሥራ Immediate ስላላስፈለገኝ ነው የተውኩት እንጂ፤ እንደ Concept ግን እወደዋለሁ። በተለይ የSpace ጉዳይ ፤ የTime ጉዳይ እና የReality ጉዳይ። Conciousnessን አራተኛ መጨመር ትችላለህ። እነዚህ ማወቅ የምፈልጋቸው ነገሮች ናቸው።


መዲና- አዎ። Academia ላይም Profileሽ 'Physics, Mysticism, Litrature' ይላል። 'መልክአ ስብሐት'ም ላይ፥ 'መልክአ ዓለማየሁ'ም ላይ የጻፍሻቸውን ጽሑፎች ስመለከት የSpace እና Timeን ሀሳብ ተጠቅሞ ምስቅልቅል የሆነውን ነገር በአንዳች ብልሃት ስሜት እንዲሰጥ የማስቻል ነገር ነው።

ፀደይ- ወደ Order ማምጣት አንድ ነገር ነው። የሒስም አንዱ ተግባር እርሱ ስለሆነ። Meaning መስጠት ነው። አሁን እዚህኛው ላይ ያደረግኩት ምንድነው? Spaceን ነው ላጠና የሞከርኩት። አሁን ለምሳሌ ፉኮ [Michel Foucault] የለያቸው የቦታ አይነቶች

አሉ አይደለ?[2] እኔ መካነ-ካልእ ብዬ የለየሁት.... እርሱ Heterotopia ብሎ የለየው አይነት ማለት ነው። የዓለማየሁ ገላጋይ ድርሰት ውስጥ ይኼ Space አለ። Analysisም ነው፤ Interpretationንም ነው። በእርግጥ በደንብ ማብራራት ይጠበቅብኝ ነበር፤ ድጋሚ አይቼው እንደዚያ ተሰምቶኛል። ግን ዋናው ነጥብ ምንድነው? በፉኮ Principle መሠረት የመካነ-ካልእ መለያዎች ውስጥ፤ ያለንበትን እና እውነታ የምንለውን ዓለም ከእነዚህ Space አች አንጻር በማየት አስቀያሚነቱን እንድንረዳው ማድረግ የሚል አለው። በልቦለዱ ዓለም ይኼኛውን ያለንበትን ዓለም እንድናነጻጽር ነው። ይኼንን ትርጉም መስጠት ነው፥ የእኔ ዓላማ። የጽሑፉ ዓላማ 'በዚህ ድርሰት ውስጥ ሥፍራን እንዴት ነው የምናየው? ዓለማየሁ እንዴት ተጠቅሞታል?' ነው የመጀመርያው ነገር። ያንን Analyze ሳደርግ Mystify የሆኑትን ነገሮች Demystify ላደርግ እችላለሁ። እርሱን Analyze ስናደርግ ስለእኛ ዓለም፤ ስላለንበት ሁኔታ ማየት የምንችላቸው ነገሮች አሉ ማለት ነው፤ ልክ እንደ መስኮት ነው።

መዲና- ስለዚህ የሆነ የቴዎሪ Framework ተጠቅሞ የራስን ትርጉም የመፈለግ ጉዳይ ነው እንጂ፤ ያ ትርጉም በመሠረታዊነት የደራሲው ሃሳብ ላይሆን ይችላል።

ፀደይ- አዎ። ላይገናኙ ይችላሉ። ግን ምንድነው... ለምሳሌ እዚህ መልክአ ዓለማየሁ ላይ Spaceን ስናጠና ጆንያዎቹ ለእኔ ትርጉም ሰጥተውኛል። አንደኛ ነገር ድርሰት ላይ የሆነ ነገር እንዲሁ ያለ Purpose ይገባል ብለህ አታስብም። ያለ Purpose መግባቱ ራሱ Purpose ስለሆነ። ስለዚህ ምንም ነገር ያለ ዓላማ መሆን አይችልም ድርሰት ውስጥ። ሁለተኛ ነገር ደግሞ.... እ.... ጆንያዎቹን አስተውለሃቸው ከሆነ... መጀመርያ አካባቢ በቁም ነበር የሚቀመጡት። የምዕራፍ ቁጥር መጻፍያ ሲሆኑ ግን ይዘቀዘቃሉ። እኔ ደግሞ የማወቅ ጉጉት እንዳለው ሰው Curiosity ስለሚፈጥርብኝ ለምን ብዬ እጠይቃለሁ። ሒስ አንዱ ጥቅሙ ትርጉም መሥጠት ነው ብዬሃለሁ። ስለዚህ ትርጉም ነው የምፈልገው። ትርጉም ስፈልግ ያገኘሁት ነገር ምንድነው? አንደኛ ስለዱቄት በጣም ብዙ ቦታ ይወራል። ሁለተኛ 'ጆንያ' የሚለው ቃል አራቱም ድርሰቶች ውስጥ አለ። ያለ ምንም Purpose ዝም ብሎ ጆንያ ጆንያ እያለ አይጽፍም አይደለ? ምስልም አድርጎ አያመጣውም። ስለዚህ ምንደነው ያ ትርጉሙ? ለምንድነው ጆንያን ያመጣው? ለምን አንዱ ጋር ቀጥ አድርጎ ሲሰላቸው አንዱ ጋ ተዘቀዘቁ? እነዚህን ጥያቄዎች ስትጠይቅ የምታገኘው መልስ ይኖራል።



ምስል፡ ሐሰተኛው በእውነት ስም መጽሐፍ

2. Of Other Spaces - Michel Foucault - PDF ለማግኘት የምከተለውን ማስፈንጠሪያ (Link) ይጠቀሙ።
https://drive.google.com/file/d/1d_PoYQXdGupckVvqjvTg76-0oCa0z0A9/view?usp=drivesdk

መዲና- ያ መልስ ግን ያንቺ መልስ ነው።

ፀደይ- የ'ኔ መልስ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም Space ነው የማጠናው። እዚያ ድርሰት ውስጥ ለማየት የፈለግኩት ያንን ነው። Spaceን ሳይ እዚያ ላይ ... ወረቀት እንደ አንድ Space ነው። በተለይ ሥነ ጽሑፍ ሲሆን ወረቀት Space ነው። ስለዚህ እዚህ ወረቀት ላይ የሚቀመጥ ማንኛውም ነገር ትርጉም ሊኖረው ይችላል። ያን ትርጉም ትፈልጋለህ። ለዚያም ነው፣ ሐያሲ አንዳንድ ጊዜ Coauthor ነው የሚባለው፤ ለዚያ ነው። አብረህ ነው የምትጽፈው።

መዲና- አሁን ዓለማየሁ ቢጠየቅ እና 'ጆንያዎቹ ምንም ትርጉም የላቸውም።' ቢል ያንቺን ትርጉም Nullify ሊያደርገው አይችልም?

ፀደይ- አይችልም። ምንም ቢል ለውጥ አያመጣም። ምክንያቱ ለምን መሠለህ? አሁን የ Sartrean ፍልስፍና ስታይ... አንዱ የምወድለት ነገር ምንድነው... ስትጽፍ ሁለቱንም ነህ። ደራሲ ከሆንክ ከሥራህ ጋር የተለየ ግንኙነት ስለሚኖርህ ድርሰቱ ያንተ ነው። At the same time ደግሞ ያንተም አይደለም። ምክንያቱም ከአንተ Already ወጥቷል። ታትሞ ወጥቷል። በየቤቱ እየሄድክ ልታብራራ አትችልም። ሁለተኛ ያ ዘመን አልፏል። እንደዚያ ማድረግ የምትችልበት። ሶቅራጠስ ነበር እንደዚያ የሚያደርገው። Dialogic Philosophizing አይደል የሚባለው? ለምሳሌ የሆነ ሃሳብ ታነሳለህ፣ ይጠይቅሃል። ትመልሳለህ። ይጠይቅሃል። መጨረሻ ላይ የተነሳህበትን ነጥብ እንድትስት ነው የሚያደርግህ አንዳንዴ... አይተኸው ከሆነ። ስለዚህ በDialogue ነው የሚመሠረተው የ'ርሱ ፍልስፍና። ያ ምን ማለት ነው? ያንን ሃሳብ ከተሸከመው ሰው ጋር በእያንዳንዱ ሃሳብ ምልልስ አለህ ማለት ነው። ድርሰት ሲሆን ግን ጽፈህ ትጨርሳለህ። Dialogue የለም። ሊኖር የሚችለው ቃለ መጠይቅ ስትደረግ፣ ወይ የሆነ መድረክ ላይ ተጋብዘህ ስታወራ፣ ወይ አብረህ መግቢያው ላይ የምትጽፈው ነገር ካለ ምናምን ነው። ሰዎች ለሚያስቡት ነገር ሁሉ መልስ አትሰጥም። በረከትም ነው፤ መርገምም ነው ይኼ። በረከትነቱ... ለማሰብ ነጻነት ይሠጣል። አንዳንዴ ደግሞ... ለምሳሌ የፍሮይድን Psychoanalysis እኔ ሙሉ ለሙሉ ባልቀበለውም... አንዱ የሚሠጥህ ነገር ምንድነው? ድርሰት Subconscious እና Unconscious Mindህ ውስጥ የተቀመጠንም ነገር ያወጣል። አንተ ራስህ የማታውቀውን ነገር። ስለዚህ አንተ ሳታውቀው የጻፍከውን ነገር ሌላ ሰው ሊያገኘው ይችላል። ስለዚህ ብዙ መንገድ ሊኖረው ስለሚችል ደራሲው የግድ ይኼ ብቻ ነው ስላለ አይሆንም። ዋጋ ሊሠጠው ይገባል በሚለው ግን አምናለሁ፤ ደራሲው የተነሳበት ነገር ካለ Value ሊሰጠው ይገባል። ያ ብቻ ነው ትክክለኛ መንገድ ማለት ግን አይቻልም። ምክንያቱም እንደዚያ ከሆነ ድርሰት Meaningless ነው፤ Impose ማድረግ ነው የሚሆነው። አንተ ትርጉም እንድታወጣ ዕድል የማይሰጥህ ከሆነ እንደ ሕጻን ቆጥሮኻል ማለት ነው። ብዙ ጊዜ አይተህ ከሆነ ሠዓሊዎችም ደራሲዎችም 'በቃ ከእኔ ወጥቷል፤ ከዚህ በኋላ የእናንተ ነው።' ምናምን ይላሉ። ምክንያቱም የተደራሲውም ነጻነት መኖር አለበት። ድርሰትም የሚያብበው እንደዚያ ሲሆን ነው።

መዲና- አንድ የፈጠራ ሥራ ለሠራው ሰው እንኳ እንግዳ ነው የሚሆነው ማለት ነው። ምናልባት በPsychoanalysis የሚደረስበት ነገር ሊሆን ይችላል።

ፀደይ- እንዳልኩህ የፍሮይድ Analysis ላይ የምጠነቀቃቸው ነገሮች አሉ። አንዳንድ ጊዜ ድርሰቱን Analyze ማድረግ ደራሲውን Analyze ማድረግ ነው የሚል ነው የመጀመርያው መነሻ። እርሱን ሃሳብ አልወደውም። ሰውየውን በእጅህ እንደመጨበጥ ይሆናል። የሰውን Subjectivity የመገደብ ነገር አለው። ሁለተኛ ነገር ደራሲ ልክ እንደ ተዋናይ የተለያየ

Soul ሊያስተናግድ ይችላል። አሁን እኔ ደራስያንን፣ ተዋናዮችንም እንደዚያ ነው የማያቸው። አካላቸውን ያከራያሉ። የተለያየ ነፍስ ሊጠቀምበት ይችላል። ሰውነታቸውን ነው የሚፈቅዱት። ደራሲም እንዲያ ነው። አንዳንዴ ሲጽፍ የተለያዩ ሰዎች ሊወጡ ይችላሉ። እነዚህ ሁሉ ግን እርሱ ናቸው ማለት አይደለም። ድሮ ፕሌቶ አንዱ Poetryን እንዲጠላ ያደረገው ነገር ይኼ ነው። እንደ ፈላስፋ አመክንዮአዊ ሆኖ የሆነ ነገርን Develop አያደርግም። የማያውቀው ሁሉ ነገር ውስጥ ሊገባ ይችላል። ስለ ጋሪ ነጂ ሊያወራ ይችላል። ስለ አሳ አጥማጅ ሊያወራ ይችላል። ይኼ ሁሉ ግን ሥራው አይደለም። እና ለምንድነው? እንደዚያ የሚያደርግ ከሆነ Irrational ነው። እነዚህ Muses የሚባሉ አሉ አይደል? ዘጠኙ? እነርሱ ናቸው በእርሱ ውስጥ የሚናገሩት። ስለዚህ Conscious ያልሆነበትን፣ Rational ያልሆነበትን ነገር ነው የሚጽፈው። ስለዚህ Poetry ከእንትን መሰረዝ አለበት ይላል... እርሱ ሊመሠርተው ከሚፈልገው ሪፐብሊክ። ድርሰት እንደዚያ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ያ ሁሉ ሰው አንተ ነህ ማለት አይደለም። አንተ ካልሆንክ ደግሞ የአንተ Sub-Conscious Mind ነው የተመረመረው የሚለው ሃሳብ አያሳምነኝም እኔን። ትችት አይታጣውም። በአንድ ወቅት እኔም ልጠቀምበት ሞክሬ ነበር፣ ሳይኮ አናላሲስን። የካዛንትዛኪስ ድርሰቶች ላይ። ምክንያቱም ካዛንትዛኪስ [Nikos Kazantzakis] ሆነ ብሎ የፍሮይድን ሃሳብ ይጠቀማል። ግን [ድርሰቱን እንጂ ደራሲውን] Analyze ማድረግ አልፈለግኩም።

መዲና- ለምን?

ፀደይ- ልክ አይደለማ። አሁን እንዳልኩህ። አንደኛ Subjectivityውን ልነጥቀው አልፈለግሁም። በድርሰት ውስጥ ስለደራሲው የሆነ የሆነ ነገር ላገኝ እችላለሁ። ግን ሰውዬው እኔ ያየሁት ብቻ ነው ማለት አይደለም።

መዲና- ግን እንደ አማራጭ የአተያይ መንገድ አይሆንም? እንዲህም ይታያል እንደማለት?

ፀደይ- አዎ። እንደዚያ ነው የሚጠቀሙት እነርሱም። ግን ይገድባል። ደራሲው ያላሰበውን ነገር ሁሉ እንደዚህ ናቸው ብለህ እንድትደመድም ያደርግሃል። ለምሳሌ 'በእናት ወይ በአባት ባለማደጉ ምክንያት Trauma ስላለበት Narcissist ነው!' ወይ ደግሞ 'Psychopath ነው!' ብለህ ብትደመድም ከባድ ነው። ሊያስከስስህ ሁሉ ይችላል። ሂሂሂ... ገባህ አይደለ? የሆነ ቀዳዳ ውስጥ አስገባኸው፣ አጠርከው ማለት ነው። ስለዚህ Analyze ስታደርገው ነጻነቱንም ነው አብረህ የምትገፈው። በሰዎች የሚታይበትንም መንገድ ነው የምትወስነው። እኔ ደግሞ በግሌ እርሱን አልወደውም። የሚሠሩ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። Psychoanalysis ይሠራበታል። አንዳንዴ የካርል ዩንግ [Carl Jung] የሚሻልበት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ Archtype የሚላቸው ነገሮች አሉ። እነዚህ Archtype ደግሞ Collective Unconscious ሊሆኑ ይችላሉ። አንዳንዴ የጻፍከው ነገር የሆነ ጊዜ የሆነ ሃገር ሚቶሎጂ ሆኖ የተነገረ ሊሆን ይችላል። አንዳንዴ የካርል ዩንግ የተሻለ ይሆናል።

መዲና- አንዳንዴ ደራሲዎቹ ራሱ የሚደነግጡበት መንገድም እኮ ሊኖር ይችላል አይደለ? 'እንደዚህ አይነት ሰው ነኝ እንዴ?' ወደማለት የሚሄዱ አሉ።

ፀደይ- አዎ! አንዳንዴ እርቃን መቅረት ነው የሚባለው ለዚያ ነው። ውስጥህ ያለው የተደበቀ ነገር ሊወጣ ይችላል። አንደኛ ድፍረት ነው። ውስጥህ የነበረን ቁስል፣ የነበረን አስቀያሚ ነገር ምናምን መጋፈጥ መቻል ነው። ምክንያቱም Unconscious ነበር፣ ወደ Conscious አመጣኸው። ያን መጋፈጥ ትልቅ ድፍረት ይጠይቃል። አሁን ያን ሰው ያለፈቃዱ Analyze ማድረግ፣ በዚያ ጀግንነቱ መቀጥቀጥ፣ አሳልፈህ መስጠት ማለት ነው።

ነገር ግን ራሱ ፈቅዶ አምኖበት ከሆነ የሚያደርገው እርሱ ሌላ ጉዳይ ነው።

መዲና- Therapeutic ነው ዝም ብዬ ሳስበው። ጠዋትም ከበደች ተክለአብ ስታነሳው የነበረው ይኼንን ነው። አሁንም ከላይ ያነሳነውም ላይ መጋፈጥ ነው ብለናል። የመመረቂያ ጽሑፍሽ ላይም ለተለያየ ነገር መድኃኒት ሆኖ ቀርቧል። ስለዚህ ኪነ ጥበብ ያለው ቦታ ምንድነው? ለSocial Evilም፣ ለNauseaም፣ ለPersonal Traumaም ያለው ፈዋሽነት?

ፀደይ- ሰበዞች ናቸው እነዚህ። ይኼ ብቻ ነው ማለት ግን አይደለም። ግን እንደ አንድ ሰበዝ Healing Process ሊሆን ይችላል። የሆነ Trauma ራሱን ሊገልጥ ይችላል። እንደ አንባቢም፣ እንደ ደራሲም። ከድሮ ጀምሮ አለ በነገራችን ላይ። ለምሳሌ አርስቶትል Poetics የሚለው መጽሐፉ ላይ የሚጠቅሰው Catharsis የሚለው ነገር አለው። በዚያ ዘመን የነበሩት ድራማዎች ናቸው። ግጥሞች አሉ፣ Epic። በነገራችን ላይ [Epic] ለቀናት ሊደረግ ይችላል፣ ይከወናል። ሰዉም ይሳተፍበታል። እየተቀበሉት ምናምን። የሆነ አምፊ ቴአትር ነገር ተዘጋጅቶ ተውኔት ይቀርባል። እንደዚያ ሲደረግ ተመልካቹ አብሮ Catharsis ያገኛል። ማልቀስ አንዱ Cathersis ነው። Noble በሆኑ ገጸ ባሕርያት መሰቃየት ወይም አሳዛኝ መጨረሻ ራሳችንን Associate አድርገን እንድናለን። ስለዚህ ጥበባት በአጠቃላይ ከመዳን ጋር ያላቸው ግንኙነት Identify ከተደረገ ቆይቷል ማለት ነው። ጥንታዊ ነው። ግን ያ ብቻ ነው ማለት አይደለም እንጂ፣ ደራሲው የራሱን ውስጣዊ ነገር ወደማከም ሊሄድ ይችላል። ቅድምም ስናነሳ እንደነበረው... ከበደች ተክለአብም ያለችው ይኼንን ነው። 'እኔ ለሥራ ባልደረቦቼ Therapist ጋ ሄጂ አላውቅም ብላቸው ይገረማሉ።' አለች። እነርሱ ጋ [ውጪ] በጣም Normal ነው። ሁሉም ሰው Dentist እና Therapist አለው። እርሷ ግን ጓደኞቿም ስላሉ፣ ሥዕልም፣ ግጥምም ስላላት በዚያ በኩል Productive ሆኖ ሊወጣ ይችላል።

መዲና- እንግዲህ አንዱ ሰበዝ ነው ይኼ Personal Traumaው። ጽሑፍሽ ላይ የተነሳው ማኅበራዊው ችግር እና የሕልውና በሽታ (Nausea) ነው።

ፀደይ- አዎ። መመረቂያ ጽሑፌ ላይ ያለው ምንድነው መሰለህ? እንደማኅበረሰብ ብዙ ችግሮች አሉን። Social Evil የምንላቸው። እነዚህን Social Evils አንዱ ማከምያ መንገድ ኤግዚስተንሻሊዝም ነው። ኤግዚስተንሺያሊዝምን ሙሉ ለሙሉ Apply ማድረግ አይደለም። ከዚያ ውስጥ የተወሰኑ ነገሮችን መውሰድ። ለምሳሌ የምዕራቡ ፍልስፍና አንድ ያደረገው ጥሩ ነገር ምንድነው? Individuality ላይ ትልቅ ሥራ ሠርቷል። ግለሰብን ማክበር፣ እንደSubject፣ ሕሊና እንዳለው ፍጡር እውቅና መስጠት። Recognise ማድረግ። ሁለተኛ ነገር ኤግዚስተንሺያሊዝም በዚያ ውስጥ ምን ይሠጠናል? ግለሰብም ለሚያደርገው ለእያንዳንዱ ነገር ኃላፊነት አለበት የሚለውን። ለምሳሌ እነ ሳርት የሚለያቸው ነገር ምንድነው መሰለህ? አምላክ የለም ባዮች ናቸው። "አምላክ በሌለበት ሁኔታ ራሱ ሞራሊቲ መጠ'በቅ አለበት፣ Ethics መኖር አለበት።" ነው የሚሉት። ፈጣሪ ስለሌለ እንደፈለግን እንሆናለን ማለት አይደለም። ግለሰቡ Still ኃላፊነት አለበት። እኛ ማኅበረሰብ ውስጥ ግን የታዘብኩት የነበረው ነገር ምንድነው... ያኔ ማለት ነው፣ አሁን እንደዚያ ላስብ አላስብ እርግጠኛ አይደለሁም። ... ግለሰብ እውቅና የለውም ኢትዮጵያ ውስጥ። እንደግለሰብ ግን ብዙ ጥፋቶች ይሠራሉ። ለምሳሌ ሙስና አንዱ እንደግለሰብ የሚፈጸም ጥፋት ነው። ውጤቱን ግን እንደማኅበረሰብ ነው የምንሸከመው። ስለዚህ ግለሰቡ ኃላፊነት አይሰማውም። ስለዚህ ይቀጥላል ማለት ነው፣ እየዘረፈ። ግለሰቡ ኃላፊነት እንዲኖረው የሚያደርግ System ብንዘረጋ ግን ይሄ ችግር ላይፈጠር ይችላል። ወይ እንቀንሰዋለን፣ ሙሉ ለሙሉ ማጥፋት እንኳ ባንችል። ያው የአፍሪካም፣ የእኛም ማኅበረሰብ Communal ነው። Individuality ላይ ብዙ አልተሠራም። እና ያ ከተደረገ ሊስተካከል ይችላል ነው።

ድርሰቶቻችንስ ውስጥ ምን አይነት ሰዎች ነው የምናገኘው? ምክንያቱም ድርሰት አንዱ ማኅበረሰቡን መገንቢያ የሚሆን ነው። ስለዚህ በጣም Classic የምንላቸው ድርሰቶች ውስጥ በሳርት የኤግዚስተንሽያሊዝም መለኪያ Exist የማያደርጉ ሰዎች ካሉ ማኅበረሰቡንም እንደዚያ ነው እያደረግነው ያለነው ነው መነሻው። ዋናው ነጥቡ ይኼ ነው። ለግለሰቦች እውቅናም ኃላፊነትም አብሮ መሰጠት አለበት፤ ነው። ከኤግዚስተንሽያሊዝም ልንወስደው የሚገባው ጠቃሚ ነገር ይኼ ነው ብዬ ነው የተነሳሁት።

መዲና- ስለዚህ በመሠረታዊነት የድርሰት ሥራዎቹ ይህንን Social Evil አያክሙም። የሚያክሙት በውስጣቸው ኃላፊነት የሚወስዱ ገጸ ባሕርያትን ሲቀርጹ እና ማኅበረሰቡን ለግለሰቦች እውቅና ወደመሥጠት ሲመሩ ነው። እንደዚያ ነው ሃሳቡ?

ፀደይ- ሥነ ጽሑፍም ሆነ ሌላው የኪነ ጥበብ ዘርፍ ይኼ ኃላፊነት አለባቸው ማለት አይደለም። የእውነታው ነጸብራቅ ስለሆኑ፤ ማኅበረሰቡን ቅልብጭ አድርገው ማሳየት የሚችሉ ስለሆኑ እነርሱ ውስጥ ራሳችንን እናገኛለን። ምን አይነት ናቸው ግለሰቦቹ? ኃላፊነት ይወስዳሉ ወይስ አይወስዱም? እውቅና አላቸው ወይስ የላቸውም? ሕልው ናቸው? ማለትም Exist ያደርጋሉ? ወይስ አያደርጉም? ገጸ ባሕርያቱ እኛን ይወክላሉ፤ አንደኛው ይኼ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ነጸብራቅ የሚሆነው... ደራሲዎቹም እዚህ ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ ስለሆኑ ነው። ስለዚህ ደራስያኑ የጻፏቸው ግለሰቦች Fail የሚያደርጉ ከሆነ፤ ማለትም ሳርት እንደሚለው Bad Faith ውስጥ ያሉ ከሆነ፤ Anxietyን የሚሸሹ ፍጡራን ከሆኑ ማኅበረሰቡ ጋም ይኼ ነገር በትልቁ አለ ማለት ነው። እንደ አንድ ማሳያ ነው። ግዴታ ነው ማለት አይደለም። ድርሰቶቹም ይኼ ጫና አለባቸው ማለት አይደለም። ምክንያቱም አንድ ደራሲ ነጻነት አለው። እኔ ድርሰት እንዲህ መሆን አለበት የሚል ብያኔ የለኝም። የራሴ ምርጫ ሊኖረኝ ይችላል። 'እንደዚህ ቢሆን...' ልል እችላለሁ። 'እንደዚህ መሆን አለበት!' የሚል ሃሳብ ግን የለኝም። *ሦስቱም ድርሰቶች [በመመረቂያ ጽሑፏ ላይ የተመረጡት ሦስቱ ድርሰቶች ፍቅር እስከ መቃብር፤ ከአድማስ ባሻገር እና ግራጫ ቃጭሎች ናቸው።]* የተመረጡበት ምክንያት ምንድነው? ሦስቱ ድርሰቶች ውስጥ ያሉ ገጸ ባሕርያት ሲታዩ ሕልው ያልሆኑ ገጸ ባሕርያት አሏቸው። በሳርት ዓይን ነው በነገራችን ላይ... በሌላ ዓይን ሕልው ሊሆኑ ይችላሉ። በሳርት መለኪያ ከሄድን ግን ብዙዎቹ ገጸ ባሕርያት ሕልውና የላቸውም። የአዳም የሚለየው መጨረሻ ላይ ሕልውናውን የሚያውጅ፤ Exist የሚያደርግ ገጸ ባሕርይ ይመጣል። ሌላው Interesting ነገር ምን መሠለህ? እዚያ ላይ አልጻፍኩትም በእርግጥ... በኋላ የፒ ኤች ዲው ጽሑፍ ላይ፤ ምናልባት አንብባችሁት ከሆነ አላውቅም፤ ግን ከፒ ኤች ዲው ጽሑፍ አንዱን ክፍል መርጬ ብሌን ላይ ጽፌ ነበረ። እና እዚያ ላይ የሚነሳው አንድ ነገር ምንድነው? መዝገቡ እንደሰው የለም። Exist አያደርግም። እንደሰው ስልህ እንደ ሌሎቹ ገጸ ባሕርያት። ጽሑፍ እንደሆነ ያምናል። በጽሑፍ የተገነባ ፍጡር እንደሆነ ያምናል። ለምሳሌ... " 'ጨ' የምትል ፊደል ነከሰችኝ።" ይላል፤ ትዝ ይልህ ከሆነ።[3] 'ጨረቃ ስትወጣ' የምትል መጽሐፍ ሲያነብብ ይቆይና... የብርሃኑ ዘሪሁንን... ትራሱ ስር ይከታታል። ከዚያ " 'ጨ' የምትለዋ ፊደል ወጥታ ንክስ!! ንክስክስስስስ... አደረገችኝ።" ብሎ በጣም ብዙ 'ስ'ዎች ደርድሮ የሚጽፋት አለች። እና 'ጨ' የምትባለዋ ፊደል ልትበላው የምትችለው እርሱ ራሱ ፊደል ከሆነ ነው። Postmodernistኦች ደግሞ እንደዚያ ናቸው። የድርሰት ሰው መሆናቸውን ያውጃሉ። እንደእኛ ሥጋ የለበሱ አይደሉም። ሕልውና አላቸው፤ Exist ያደርጋሉ። አሁን መዝገቡን እንደሰው እናወራዋለን አይደል? ሌሎች ድርሰቶች ላይ እዚያ ጋ እናቆማለን። እንደሰው አውርተናቸው ምናምን እንንናደዳለን፤ እናለቅሳለን፤ እንስቃለን ወዘተ ወዘተ... Postmodernistኦች ጋ ስንመጣ ግን ከጽሑፍ የተሠሩ ሰዎች መሆናቸውን ፊት ለፊት ነው የሚያውጁት። እንደዚያ አይነት አዋጅ ነው የመዝገቡ። ከፊደል የተሠራ ፍጡር ነው። ወደሕልውናዊ ሊያድግ የሚችል፤

3. ግራጫ ቃጭሎች - አዳም ረታ- ገጽ 167

የሚታይበት ባሕርይ ግን አለው። ምክንያቱም እዚያ ውስጥ ወለዬው ደጋግሞ ይለዋል አይደለ? 'ሕልውናህን ማሳየት አለብህ! መረበሽ አለብህ! መኖርህን ማሳወቅ አለብህ!' ምናምን ይለዋል። በፊት ያንገራግር ነበር፤ ወይም አይገባውም ነበር። ልክ መጨረሻ ላይ ግን በኩረን በወንበር ሲመታው... እዚያ ጋ በቃ! Stand Out እያደረገ ነው። ኤግዚስተንሽያሊስቶች 'Environment ውስጥ Stand Out ማድረግ ነው Exist ማድረግ ማለት።' ይላሉ። ልክ እንደ Being for Itself አይነት። መውጣት ማለት ነው። የራስን ጭንቀት Accept ማድረግ ማለት ነው። ኃላፊነት መውሰድ ማለት ነው። ስለዚህ እዚህ ጋ ሕይወቱ ላይ ኃላፊነት እየወሰደ ነው። ገነትን ይፈልጋታል። በገነት በኩል የሚመጣበትን ማንኛውንም ነገር Fight ለማድረግ ተዘጋጀ ማለት ነው። ስለዚህ Exist ወደማድረግ ይቀየራል ነው። እንጂ አሁን እንዳልኩህ ከጽሑፍ የተሠራ ሰው መሆኑን ፊት ለፊት ይናገራል። በዚያ Different ነው። ይኼ የሁሉም ባሕርይ ነው። በሁሉም ድርሰቶች ውስጥ እናገኘዋለን። Even የራሱ የሳርት ልቦለዶች ውስጥም የምናገኛቸው ገጸ ባሕርያት መገለጫ ነው። ከወረቀት፣ ከጽሑፍ የተሠሩ ሰዎች ናቸው። ልዩነቱ እዚህ ጋ ጮክ ብሎ መናገሩ ነው። ጥበባዊ በሆነ መንገድ አጉልቶ ማውጣቱ ነው፣ Differenceኡ።

[እዚህ ጋ አስተናጋጁ መጣ። ቡና አዘዝን። ጨዋታችን ቀጥሎ አዲስ ቅርጽ የያዘው ከዚህ በኋላ ነበር። ፀደይ በጨዋታ እያዋዛች ኤግዚስተንሺያሊዝምን ከሀ እስከ ፐ እንደአዲስ አስረዳችን። ስለኒቼ፣ ስለ ሀይድገር፣ ስለ ሳርት እና ስለ ሾፐን ሃወር አወራን። ፍልስፍናዊ ቀልዶች ቀለድን። ይሄ ረዥም ጊዜ የወሰደው ውይይት ነው። ቀጥታ ማቅረቡ አስፈላጊ መስሎ አልታየንም። ወደፍሬ ሃሳቡ እንመለስ።]

መዲና- ስለፍልስፍና ካወራን አይቀር እግረ መንገዳችንን ስለ በይነ ዲሲፕላናዊነት ብናወራ ጥሩ መሠለኝ። እኔ የምዕራባውያን ሥነ ጽሑፍ ያደገው ከፍልስፍናው እና ከሥነ ልቡናው ጋር Interdisciplinary ሆኖ ስለቀጠለ ነው ብዬ አስባለሁ። የእኛ ሃገርም ሥነ ጽሑፍ ያልዳበረው ከዚህ አንጻር በመድከሙ ሊሆን ይችላል። ጠንካራ የሆነ ፍልስፍና የለንም። ጠንካራ ሥነ ምግባር ነበር የነበረን። ይኼ ሥነ ምግባር በነብላቴን ጌታ ጎሩይ ወልደ ሥላሴ ጊዜ፣ በነ 'ወዳጄ ልቤ' እና በነ'አዲስ ዓለም' ጊዜ ከሥነ ጽሑፉ ጋር አንድ ነበር። ለማደግ ጊዜ ፈጅቷል። ከዚያ በኋላም ደግሞ በጉልህ ልናነሳቸው የምንችላቸው ወሳኝ ደራስያን፣ እነ ስብሐት፣ እነ አዳም፣ አሁን ደግሞ እነ ዓለማየሁ ከምዕራባውያን ባሕል እና ፍልስፍና እየተዋሱ በማልመድ፣ እና ኢትዮጵያዊ በማድረግ ነው አሁን ያለንበት ደረጃ የደረስነው።

ፀደይ- አዎ! ምናልባት Paperኡን ስታየው ልብ ብለህ እንደሆነ የሳርትን ኤግዚስተንሽያሊዝም የመረጥኩበት ዋነኛው ምክንያት ምንድነው? ብዙ ነገሮች በውስጡ አሉት። Politics አለው። Phenomenology አለው። Psychoanalysis አለው።

መዲና- Litrary Theoryም አለው።

ፀደይ- አዎ! Litrary Theoryም አለው። እና ወደስድስት ምናምን አይነት ነገሮች አጭቋል። ነገሮችን ከተለያየ Perspective ለማየት ዕድል የሚሠጥ ነገር አለው። አንዱ የመረጥኩበት ምክንያት እርሱ ነበረ። አሁን እኛ ሃገር ግራ ተጋብቷል ብዬ የማስበው ነገር ምንድነው መሰለህ? ትንሽ ማጣራት ያስፈለግ ይሆናል በርግጥ። ግን Multidisciplinary እና Interdisciplinary ተቀላቅሎብናል። ሁለቱ ልዩነት አላቸው። ወደዚህ ሃሳብ ከመምጣታችን በፊት ከፍልስፍና እንጀምር። ከጥንታዊው... ከመሠረቱ ማለት ነው። ፍልስፍና በመጀመርያ ሁሉንም ነገር የሚያቅፍ ሳይንስ ነበረ። ቅድም ያነሳነው የአርስቶትል Poetics የሠራው ትልቅ ቁም ነገር ምንድነው መሠለህ... ለመጀመርያ ጊዜ Discipline አችን ከፋፈለ። Applied Sciences፣ Productive Sciences ምናምን ብሎ ወደ ሦስት ቦታ ሸነሸነው። ያንን ያደረገው 'ከVirtue ጋር የተያያዘው የትኛው ነው? ሥነ ጽሑፍ ምን

ሚና ይጫወታል? እነ አርክቴክቸር እነ ኢንጂነሪንግ ምናምን... ምንድነው ሙያቸው?' የሚለውን ለመመለስ ነው። ፍልስፍና እንደዚያ ነው ለመጀመርያ ጊዜ የተከፋፈለው እንጂ፣ ሁሉም ነገር የሚወራበት ትምህርት ነበር ከመጀመርያውም። ምክንያቱም እውቀትን፣ እውነትን፣ ጥበብን ፍለጋ ስለሆነ ማንኛውም ከዚያ ጋር የተገናኘ ነገር በሙሉ እዚያ ውስጥ ነበር የሚነሳው። አርስቶትል ጀመረው። በኋላ ሄዶ ሄዶ [ኢማኑኤል] ካንት [Immanuel Kant] ጋ ስንመጣ... ከካንት በፊት፣ በምዕራቡ.... ያው የምዕራቡን ነው የምንመለከተው ብዬ ነው፣ በኋላ ወደእኛ እመጣለሁ... በምዕራቡ ዓለም Periodኦች ነበሩ አይደል? ያው Dark Age የምንለው አለ። በጣም Reductionist በሆነ መንገድ ብናየው ሳይንስና ሃይማኖት የተጣሉበት ጊዜ ነበር ማለት እንችላለን። ስለተጣሉ ለዚህ መፍትሔ ሲፈለግ ነበር። ዴካ'ት [René Descartes] ይመጣል። ዴካ'ት ምንድነው ያደረገው? ለረዥም ዘመን፣ ለሺህ ዓመታት Body እና Mind እንደአንድ Entity ነበር የሚታዩት። እነርሱን ነጣጠላቸው። Mind በመንፈሳዊው እንዲታይ፣ Body ደግሞ በማቴርያሊዝሙ... ከሳይንስ ጋር እንዲሄድ። ስለዚህ ሳይንስም በራሱ ሄደ፣ ሃይማኖቱም በራሱ ይሂድ ብሎ ነጠለው። ያ ነገር የምዕራባውያን አስተሳሰብ ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ነበረው። ከዚያ በኋላ እነ ኒውተን [Issac Newton] ሲመጡ ይኼንን Cosmos እንደማሽን ነው የወሰዱት፣ Mechanical አድርገው። "እግዚአብሔር የሠራቸው Absolute የሆኑ ሕጎች አሉ። እነዚህ ሕጎች ልክ እንደማሽን አውቶማቲክሊ ይሠራሉ።" የሚል ሃሳብ አመጡ። ስለዚህ እንዲህ እያለ ይኼድና... አሁን ዝም ብለን ፈጠን ፈጠን እያልን ብንመለከተው፣ ካንት ጋ ነው የምንደርሰው። ካንት ጋ Natural Science ከፍ ከፍ ብሎ እንዲጠና፣ የበለጠ መነጠል ጀመረ። Natural Science ብሎ ሥያሜ ላይሠጠው ይችላል፣ ግን ፊዚክስን፣ ማትስን ነጠለ። ስለዚህ ምን ሆነ? እነዚህ ሳይንስ ተባሉ። የተቀሩት ሳይንስ አይደሉም ማለት ነው። ምክንያቱም ያን ጊዜ እነ [ፍራንሲስ] ቤከን ምናምን መጥተዋል። ማይክሮስኮፕ ተሠርቷል። ኢንዳክቲቭ ዲዳክቲቭን ለይቷል፣ ፍራንሲስ ቤከን [Francis Bacon]። ስለዚህ ሳይንስ Already ቅርጽ እየያዘ መጥቷል። በቃ፣ የዚያን ጊዜ ሳይንስ ከታሪክ፣ ከፍልስፍና፣ Even ከባዮሎጂ ሁሉ የተነጠለ ሆነ። በነገራችን ላይ ባዮሎጂ በዚያን ጊዜ እንደሳይንስ ሁሉ አይቆጠርም ነበር። So ምን ሆነ? ሳይንስ እና ሳይንስ ያልሆኑ ተብሎ ተነጠለ ማለት ነው። የእነርሱ Culture ደግሞ ሳይንስን ፣ Objective የሆነውን ዓለም ወደመከተል ሄደ። 'ተፈጥሮን Conquer ለማድረግ፣ እኛ እንዲስማማን አድርገን ለመሥራት ምናምን ሳይንስ ነው ዋናው። ስለዚያኛው... Spiritual ስለሆነው ነገር ማረጋገጥ አንችልም። ስለዚህ ላብራቶሪ ውስጥ Experiment ሠርተን Prove/ Disprove ማድረግ የምንችለውን ነገር... እርሱን ነው መከተል ያለብን።' ወደሚል ሃሳብ ደረሱ። ሄዶ ሄዶ የኢንዱስትሪ አብዮትን አመጣ። በዘመኑ ኤኮኖሚውን ጨምሮ፣ ብዙ ነገሮችን ቀይሯል ይኼ አብዮት። የሳይንስና የሃይማኖትም ነገር እዚያ ጋ እየለየለት መጣ። ካልተሳሳትኩኝ 1830 [እ.አ.አ] ላይ ይመስለኛል... ለመጀመርያ ጊዜ Scientist የሚለው ቃል የተፈጠረው። ከዚያ በፊት ሳይንቲስት የሚል ቃል አልነበረም። ሳይንስ አለ። ሳይንቲስት ግን አልነበረም። ይኼ ሳይንቲስት የሚለው ለማን ተሰጠ፣ ያን ጊዜ? Exclusively Natural Science ለሚያጠኑ ሰዎች ተነጥሎ ተሠጠ። ስለዚህ ተነጣጠሉ። ከዚያ ትንሽ ይቆይና 1913 አካባቢ ይመስለኛል... 'አንዱ ያለ አንዱ Exist አያደርግም። ስለዚህ ፍልስፍና ላይ እንደነበሩት ወደመገናኘት መምጣት አለባቸው።' የሚል ነገር እንደገና መነሳት የጀመረው። C. P. Snow ይመስለኛል፣ በሙያው ኬሚስት ነው፣ ግን ሥነ ጽሑፍ ውስጥም አለ። እና The Two Cultures የሚል መጽሐፍ... ማነው ንግግር አለው፣[4] በዚያ ንግግር ካልተሳሳትኩ ከሃያ በላይ የክብር ዶክትሬቶች ተሸልሚል፣ በዚህ ንግግር ብቻ። በ1950ዎቹ ውስጥ ይመስለኛል። [በንግግሩ] የተነበየው ነገር ምንድነው? 'ሩስያ ከእኛ ማለትም ከምዕራባውያን በተሻለ Humanities እና ሳይንስን አጋብታ ነው እየሄደች ያለችው። እኛ ግን ሳይንስ

---

4. The Two Culture - C. P. Snow - በPDF ለማግኘት የሚከተለውን ማስፈንጠርያ (Link) ይጠቀሙ። https://drive.google.com/file/d/1djcZqszy-EV8qca6ZmqsF99w16vzajjC/view?usp=drivesdk

ሳይንስ እያልን ነው። በኋላ ላይ አፍሪካውያን ከእኛ በተሻለ መልኩ ሳይንሱ ላይ ሲደርሱበት ልንደርስባቸው አንችልም። ምክንያቱም ሳይንስ ሊደረስበት የሚችል ነገር ነው። ቀድመን ሁለቱን ወደማገናኘት መሄድ አለብን።' ምናምን የሚል ነው። እርሱም በኬምስትነቱ ሳይንቲስት ነው፤ በሥነ ጽሑፉ ደግሞ Humanities ስር ይጠቀለላል። በአጭሩ እንደዚህ አይነት እንቅስቃሴዎች ነበሩ። 1913 ላይ Already Interdisciplinary ነገሮች ተጀምረዋል። ግን አሁን ልዩነቶቹ ምንድናቸው? ቅድም ያልኩህ ይኼ... Multidisciplinary ማለት... Interdisciplinary የሚለውን ቃል የፈጠሩት ሰዎች ሲተረጉሙት ማለት ነው... የሆነ ነገር ከተለያየ Discipline ፤ ከኬምስትሪ፣ ከፊዚክስ፣ ከሚስቲሲዝም ወዘተ... ሲታይ ነው። Interdisciplinary ግን እነዚህ Disciplineኦች አንድ ላይ ይሆኑና ሌላ Tool Develop ያደርጋሉ። ከዚያ በዚህ Develop በተደረገው Tool ነው የሚያዩት፤ የሚጠናውን ነገር። አየህ፣ Inter ነው የሚሆኑት፤ ይገናኛሉ። እርስ በእርስ ይተሳሰራሉ። ስለዚህ ይለያያል ማለት ነው [ከMultidisciplinary]። So አሁን ወደእኛ ሃገር ስንመጣ ምን መሰለህ? Multidisciplinary እና Interdisciplinary መምታታቸውን አያለሁ አንዳንዴ። የእኛ ሥነ ጽሑፍ ለረዥዥዥ...ም ዘመናት ሃይማኖት ላይ መሠረት ያደረገ ነበረ። ግዕዙን ካየን ማለቴ ነው። Oral Litrature ብዙ አለ። Oral የሆነው ብዙ ጊዜ ከግብረ ገብ ጋር የተያያዘ ነው። ወይ ያለፈ ታሪክን በአጭር ግጥም ወይ ተረት ለማስቀረት ነው። ወይ ጀግናን ለማወደስ፣ ፈሪን ለማንቋሸሽ ነው። So Functional ነው ማለት ነው። ለረዥም ዘመን ይኼ ነው የሆነው። ልብ ወለድ ወደሚለው የመጣነው ሃያኛው ክፍለ ዘመን ላይ ነው። 1900 ላይ ነው አይደል... እነ ጦቢያ ሲመጡ ወደ ልቦለድ የመጣነው? ከዚያ በፊትም ነበር የሚሉ አሉ በእርግጥ። በትግረኛ የተጻፈ የመጀመርያው ልቦለድ አለ ብለው የሚከራከሩ ሰዎች አሉ። እኔ አላነበብኩትም Actually። በእርግጠኝነት መናገር አልችልም። አንዳንድ አፍሪካውያን ደግሞ ጦቢያን ለጣልያኖች አማርኛ ማስተማርያ የተጻፈ ስለሆነ አንቀበልም በሚል ከብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ የሚጀምሩ አሉ። እንደዚያ የሚል Encyclopedia አይቻለሁ። ምክንያቱም ከኢትዮጵያ የመጀመርያው የሆነው ልቦለድ ከአፍሪካም የመጀመሪያው ስለሚሆን። ዞሮ ዞሮ ልቦለድ ያኔ ነው የተጀመረው። መጀመርያ ጦቢያ፤ ከዚያ ወዲያው ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ። በዚህም ምክንያት ለረዥም ጊዜ የOral Litrature እና የሃይማኖቱ ተጽዕኖ ነበር። ግብረ ገብ ማስተማርያ ነው የሆነው። የሆነ Functionality ይጠበቅበታል። እ... ከዚያ በኋላ ጣልያን ገባ። ጣልያን ከወጣም በኋላ ብዙ ተጽፏል። በጥራት መርጠህ የምታወጣለት ላይኖር ይችላል እንጂ፤ ሄደህ ሄደህ የምትደርሰው 1960ዎቹ ላይ ነው። 'ፍቅር እስከ መቃብር' 58 ነው አይደል የተጻፈው? 62 'አደፍርስ'ና 'ከአድማስ ባሻገር'። ከዚያ በኋላ ነው ልቦለድ የሚለው ነገር በትክክል ቅርጽ እየያዘ የሚመጣው። ስለዚህ ረዥም ዘመን አልነበረውም። የምዕራባውያኑን ግን ስታየው እንደው ቢያንስ ቢያንስ ከፕሌቶ እንኳ ጀምሮ ቴዎሪዎች አሉ። ጭቅጭቆች ክርክሮች ነበሩ። የሆነ ያህል ዘመን አልፎ Neoplatonism ተብሎ ይመጣል፤ መልሶ። ሌሎችም አሉ። Dark Age ይመጣል። Renaissance ይመጣል። Realism፣ Romanticism ከዚያ በኋላ እነዚህ... Experimental የሆኑት Avant-garde የምንላቸው። እንደዚህ እንደዚህ እየተቀያየረ ይመጣል። በዚህም ምክንያት ለረዥም ዘመን በፍልስፍና እየዳበረ፣ እየተፈተሸ፣ እየተጠየቀ፣ እየተተቸ ነው እዚህ የደረሰው። እኛ ጋር ግን አርቱ ቢኖርም ግን 'ጥበብ ምንድነው? ኤስቴቲክ ምንድነው?' ምናምን በሚል ግን ውይይቶች የሉም። ጥበብ ከሃይማኖት አንጻር ብቻ ነው የሚታየው። ይኼ ምድራዊው ነገር ተረስቷል። ችግር ነው ለማለትም ይከብዳል። ችግር አይደለም። ግን እንደዚህ አይነት ባህል አልነበረንም ነው። ምዕራባውያኑ ጋ ስንመጣ ጥበብ ሃይማኖታዊ በሆነ መንገድ ይታይበት በነበረበት ዘመን ሁላ ክርክሮች ነበሩ። እነ ቅዱስ አውግስጢኖስ... እነ...

መዲና- ቶማስ አኩዊናስ

ፀደይ- አዎ! እነ ቶማስ። ሌሎችም ነበሩ። እነርሱ ጋ አሁን 'አርት ውሸት ነው፤ አያስፈልግም።' ያሉ ነበሩ። ነገር ግን እርሱ ራሱ Definition ነው። ያስፈልጋል። እኛ ሃገር አይተነተንም ነው እንጂ፤ አርቱ አለ። በነገራችን ላይ የቤተ ክርስቲያን ባሕል ውስጥ አለ ይኼ። ትችት ይሰጣል። ይበል ይበል ይባላል።

መዲና- ሚስጥር ማብራራትም አለ እኮ። ከተቀኘ በኋላ ምንድነው የተቀኘኸው ይባላል። ምናልባት በቃል የሚተላለፍ ስለሆነ ስላልተጻፈ ሊሆን ይችላል።

ፀደይ- ስላልተጻፈ ብቻ ሳይሆን ቅድም ያልኩህ ነገር አለ። 'ኤስቴቲክሱ ምኑ ጋ ነው?' ምናምን የሚል አይደለም ክርክሩ። የሆነ ፎርሙላ አለው አይደለ? በዚያ ፎርሙላ ነው የሚመዝኑት። አዳዲስ ነገሮች ይመጣሉ። በጣጣጣ...ም Rarely ነው ግን የሚመጡት። አሁን ለምሳሌ የቅዱስ ያሬድ አለ አይደለ? ከዚያ ውጪ አዲስ የመጣ ነገር አለ?

መዲና- ምናልባት የአለቃ ገብረ ሐና የተክሌ ዝማሜ... ሩቅ ቢሆንም ዘመኑ፤ ከቅዱስ ያሬድ እስከ አለቃ ገብረ ሐና ያለው...

ፀደይ- አዎ። ግን እርሱም ቢሆን ዝማሜው ብቻ ነው። ዜማዎቹ ላይም የጨመሩ አሉ ሌሎች። ቅዱስ ያሬድ ስምንት በፊደል የማይወከሉ ምልክቶችን ነው የፈጠረው። ከዚያ በኋላ በፊደል የሚወከሉ ብዙ ምልክቶች ተጨምረዋል። ግን እነዚህ ራሳቸው ከራሱ ከቅዱስ ያሬድ የሚወጡ ናቸው እንጂ፤ ሙሉ ለሙሉ አዲስ አይደሉም። ማናቸው.... አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ የጨመሯቸው አንብር እና ድርስ የሚባሉ አሉ ይባላል...

መዲና- ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ደግሞ እነ አዛዥ ጌራ እና አዛዥ ራጉኤልን ያነሳሉ፤ የቅዱስ ያሬድን ዜማ አዳብረዋል በሚል።

ፀደይ- አዎ። ጭማሪ ነው። ግን ጭማሪው ምን መሰለህ፤ ከራሱ ከያሬድ ዜማ ነው የሚወጣው እንጂ፤ የተለየ አይደለም። ምዕራባውያኑ ጋ የያሬድ ዜማ ለምንድነው የሚስብ የሆነው የሚለውን ማብራራት ይቻላል። እኛ ጋ ይህ አልተደረገም። በአጠቃላይ ዓለማዊ የሚባል ጥበብ ለረዥም ጊዜ የለንም። ይኼ ማለት ክርክርም የለም ማለት ነው፤ ለረዥም ዘመን። መንፈሳዊው ነገር፤ የመለኮት መገለጥ ነው ስለሚባል ትንሽ ለመከራከር ላይመች ስለሚችል። ስለዚህ አንዱ ችግር ይኼ ይመስለኛል። ችግርም ባንለው... አንዱ ልዩነታችን ይኼ ይመስለኛል። 'ለምን ዓለማዊው አልዳበረም?' ምናምን ማለት አንችልም። እንደ አንድ ልዩነት ግን ልናስቀምጠው እንችላለን። ዓለማዊው ነገር አጭር ነው ታሪኩ። ስለዚህ Interdisciplinary ለመሆን ጊዜ የለውም። ሁለተኛ ደግሞ ሐያሲያኑስ Interested ናቸው ወይ? ከሥነ ጽሑፍ ውጪ ያለ ነገርን ከሥነ ጽሑፉ ጋር ለማዛመድ? ከLiterary Theory ውጪ ለማንበብ?

መዲና- በጣም ጥሩ። ...

ወደ ገጽ43 ዞሯል!

ገጣሚ | ቤዛ ተዘራ

አርኬ

...?

የማይጠገግ ልጠግን፥
ሽንቁር ልደፍን ስታትር፤
ቀን፣ ጊዜ ስንት ዘመን፥ እንዲሁ ስውተረተር፤
ከሄደ ከራቀ ጋራ፥ እጅ ለእጅ፥ እግር በእግር፤
የጠላሁትን ስወድ፥ የፈራሁትን ስደፍር...


ለቀዘቀዘ ወና፥ ነፋስ ለሚጮህበት፤
እኔ ሙዚቃ ልሆን፥
ከጭርታ ላወጣው፥ በባዶ ቦታ መገኘት፤
የጉጉት ማንቋረር ብቻ ፣ ጨለማ የዋጠን ሁነት፤
ይሻል ፣ ይቀር ይመስል፥ በእኔ ብቻ መገኘት።

የዛፎቹ ሽውታ፥ እርስ በእርስ መፋጨት፤
የውሾቹ ማላዘን፥ የድመት ጥል ከሚታይበት፤
ስጥ ተሰጥቶ መሃል፥ ወፎች ሲሻኩቱበት፤
እሽ ዘወር በሉ የሚል፥ አንድ በሌለበት፤
እኔ ብቻ መገኘት...

ብርሃኔን እያየሁት፥ ጨለማ ወረሰኝ፤
የሳቄን ድምጽ እየሰማሁ፥ የዝምታ ጩኸት ዝም አስኘኝ፤
ትርትር ቀዳዳ ልሰፋ፥ የማይደፈን ልደፍን፤
የማይሞላ ጎዶሎ ልሞላ፥ ብቻዬን ሳብሰለስል፤
ሽንቁር ፣ የባሰበት ስታገል ልሸነቁር፤
የማይጠገን የማይጠገግ፥ ልጠግን ስሞክር፤
ብቻዬን ስጎትት ክፍተቱ የሚሰፋ፤
በዚያ ወገን ያለው ለካ፥ ወደራሱ እየገፋ፤
የገዛ ምኞት ሃሳቤን፥ የ'ኔን ብቻ መመልከቴ፤
ለምን? እንዴት?
በጥልቅ አለማየቴ...

ድቅድቅ ምልክት የሌለው፥ መንገዴን ይዞት ሄደ፤
ብርሃን ልሆን ተገኝቼ፥ ብርሃኔ ተወሰደ....

የዛፎቹ ሽውታ፥ እርስ በእርስ መፋጨት፤
የውሾቹ ማላዘን፥ የድመት ጥል ከሚታይበት፤
ስጥ ተሰጥቶ መሃል፥ ወፎች ሲሻኩቱበት፤
እሽ ዘወር በሉ የሚል፥ አንድ በሌለበት፤
እኔ ብቻ መገኘት...
ስህተት!



> *It was the will of God that I won the olympics, and it was the will of God that I met with my accident.* ”

እፍታ

ታሳቁ አቤ

አዘጋጅ | ብሥራት መብራቱ

“ይሻልሻል ይሻልሻል
አበበ ቢቂላ ያገባሻል
ጥላሁን ገሠሠ ይድርሻል...”

ጳጉሜ 5 ቀን 1952 ዓ.ም አትሌት አበበ ቢቂላ በሮም ኦሎምፒክ ድል ካደረገ በኋላ ዝናው በዓለም መልቶ ነበር። በሃገራችንም ከነበረው ዝናና ክብር የተነሳ፤ አቤን ለመቀበል አደባባይ ከወጣው ሕዝብም ብዛት ጭምር ለብዙ ዘመናት ይኼ ከላይ ያነሳነው ግጥም የሠርግ ማጀብያ ዘፈን ሆኖ አገልግሏል።

'ኤል ግራንዴ አቤ' ይሉታል ጣሊያኖቹ። ታላቁ አቤ እንደማለት። በጣም ትልቁ ማለት ነው፤ ኤል ግራንዴ። አቤ በሮም ኦሎምፒክ የወቅቱ ክብረ ወሰን በነበረ ሰዓት 2፡15፡16 በመግባት አንደኛ ወጥቶ ያገኘው ወርቅ ለአፍሪካ የመጀመሪያው ሆነ። ጊዜው ደግሞ ብዙ የአፍሪካ ሀገራት ከቅኝ ግዛት ነጻ ይወጡበት የነበረ በመሆኑ ድሉን ይበልጥ አደመቀው። ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ደግሞ ከጣሊያን ጋር ታሪክ ስላለን ድሉ ደማቅ ሆነ። “ጣሊያን ሁለቱ እጅ ሰጠች”፣ “አቤ በባዶ እግሩ ሮምን ወረረ” ... ዓይነት ርዕሶች የወቅቱ የጋዜጣ ሽፋን ነበሩ። (ሻምበል አበበ ቢቂላ፤ 2023) (እንግዳ፤ 2006 ዓ.ም)

አበበ ቢቂላ በሰሜን ሸዋ መንዲዳ ከምትሰኝ አነስተኛ ከተማ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ገባ ብላ ከምትገኝ ጃቶ ከምትባል መንደር ነሐሴ 1 ቀን 1924 ዓ.ም ተወለደ። ከዚህ በተለየ መረጃ ደግሞ በ1925. ዓ.ም ከአባቱ ከአቶ ደምሴ ዓለሜ እና ከወይዘሮ ውድነሽ በነበሩ፣ ሙጢ የተባለ ቀበሌ ውስጥ ጅሩ ተወልዶ በአባት እና በአባቱ ቤት ከአደገ በኋላ በንጉሠ ነገሥቱ ሠራዊት ውስጥ በክቡር ዘበኝነት ተቀጥሮ በማገልገል ላይ የሚገኝ እንደሆነ ወታደር እና ዓላማው የተሠኘው ጋዜጣ አስነብቧል። በሌላም በኩል የኢትዮጵያ ድምጽ ጋዜጣ በመስከረም 5 1953 ዓ.ም እንዳስነበበው አበበ ቢቂላ በሸዋ ጠቅላይ ግዛት በሙጢ ቀበሌ እመት ውድነሽ ከአቶ ደምሴ ዓለሜ አበበን የስምንት ወር ነፍሰ ጡር ሆነው ከመንዝ ወደ ጅሩ ተሻገሩ። እዚያም አበበን ወለዱ። እመት ውድነሽ በጅሩ ቢቂላን አግብተው ስለነበር አበበ በአቶ ቢቂላ ቤት አደገ። በዚህም ምክንያት አበበ ደምሴ በመባል ፈንታ አበበ ቢቂላ ተሰኝቶ ተጠራ። (ተፈሪ ዓለሙ፤ 2015 ዓ.ም)

አበበ ቢቂላ በ21 ዓመት ዕድሜው ከተወለደበት መንደር በእግሩ ተጉዞ በሚያዚያ 15 1945 ዓ.ም በክቡር ዘበኛ ክፍለ ጦር በተራ ወታደርነት ተቀጠረ። ከሦስት ዓመት በኋላ ወደ ስፖርት ክፍል እስኪመደብ ድረስ በልጅነቱ ለጨዋታ ከተሯሯጠው በቀር የሩጫ ልምድ አልነበረውም። ለዚያም ነበር የዋሚ ቢራቱ ተጠባባቂ ተደርጎ የተያዘው። ሯጮቹ ወደ ሮም ሊበሩ ጥቅት ቀናት ሲቀራቸው ግን ዋሚ ቢራቱ በህመም ምክንያት መብረር እንደማይችል ስለታወቀ አበበ እርሱን እንዲተካ ሆኖ ሮም ላይ መሮጥ እና ማሸነፍ ችሏል። በወቅቱ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ “እኔ የዓለም አንደኛ ብሆንም ከኢትዮጵያ ግን ሁለተኛ ነኝ።” ያለው በዚህ ምክንያት ነበር።

ኤል ግራንዴ አቤ በሩጫ ሕይወቱ አንድ ጊዜ ብቻ ነው ሽንፈትን የቀመሰው። በቦስተን ማራቶን አምስተኛ ከመውጣቱ በቀር የሮጠባቸውን ሁሉንም (12ቱንም) ማራቶኖች አንደኛ አንደኛ እየሆነ ነው ያሸነፈው። ከሁሉ ከሁሉ በላይ ግን የቶኪዮው ድል ይገርማል። ከቶኪዮው ማራቶን 40 ቀን በፊት፣ ለጉዞው 15 ቀናት ሲቀሩ ማለት ነው፣ አቤ በድንገት ታመመ። ጋሽ ይድነቃቸው እና የአበበ አሰልጣኝ የነበሩት ሜጀር አኒ ኒስካን በታመመበት ሌሊት አበበን ይዘው ወደ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሆስፒታል ይወስዱታል። ሐኪሙም አቤን ካየው በኋላ አፕራሲዮን መደረግ እንዳለበት ሲነግራቸው፣ ሁለቱ ብቻ ይስማሙና የሐኪሞች ቦርድም ሆነ የኦሎምፒክ ኮሚቴው ሳያውቅ በአፕሬሽን ትርፍ አንጀቱ ይወጣለታል። ታላቁ አቤ አፕሬሽኑን ካደረገ ከአርባ ቀናት በኋላ የራሱን ክብረ ወሰን በማሻሻል በ2፡12፡11 ለኢትዮጵያ ሁለተኛውን የወርቅ ሜዳሊያ አስመዘገበ። (Marta Pausilli & Priya Sippy, 2024)

ከዚህ በኋላ በ1962 ዓ.ም ቮልስዋገን መኪናውን እያሽከረከረ ሳለ ሰላማዊ ሰልፈኞች በመንገዱ ድንገት ስለገጠሙት መንገዱን ለመልቀቅ ሲዞር መኪናው ከቁጥጥር ውጪ ይሆንበትና መንገዱን ስቶ ይገለበጣል። በዚህ አደጋ ምክንያት ከአንገት በታች ፓራላይዝድ ሆነ። እንግሊዝ በሚገኘው ስቶክ

ማንዴቪል ሆስፒታል ለሕክምና ቢወሰድም ድጋሚ መራመድ እንደማይችል ዶክተሮቹ ነገሩት። (Marta Pausilli & Priya Sippy, 2024) (ተፈሪ ዓለሙ፣ 2015 ዓ.ም)

ታላቁ አቤ ጋዜጠኞች ስለአደጋው ለጠየቁት ጥያቄ እንዲህ ሲል ተደምጧል። “ኦሎምፒክን በእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳሸነፍኩ ሁሉ አደጋም የደረሰብኝ በእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር። እነዚያን ጣፋጭ ድሎች እንደተቀበልኩት ሁሉ ይህንን አሳዛኝ አደጋም ተቀብያለሁ። ሁለቱም የሕይወት ገጽታዎች ናቸው።”

የጽናት ተምሳሌቱ አቤ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እጆቹን ማንቀሳቀስ ቻለ። ይኼኔ ነው ወደ ቀስት ውርወራ እና ቴኒስ ዓይነት የስፖርት መስኮች የተሰማራው። በ1970 ለንደን በሚካሄደው የስቶክ ማንዴቪል ጨዋታዎች ላይ ተሳተፈ። ይህ ውድድር አሁን ፓራሊምፒክስ ተብሎ የሚጠራው ውድድር ነው።

በቀጣዩ ዓመት አካላዊ ጉዳት ያለባቸው ሰዎች በሚሳተፉት ውድድር ላይ ለመሳተፍ ወደ ኖርዌይ አቅንቶ በፈረስ ጋሪ ግልቢያ አሸናፊ ሆኖ ተመለሰ።

ታላቁ፣ የመጀመሪያው የኦሎምፒክ ወርቅ አሸናፊ አፍሪካዊ፣ የጽናት ተምሳሌቱ፣ ኤል ግራንዴ፣ ሻምበል አበበ ቢቂላ በአደጋው ምክንያት በደረሰበት ሕመም ጥቅምት 15 ቀን 1965 ዓ.ም በ41 ዓመቱ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። (Marta Pausilli & Priya Sippy, 2024)

የአፍሪካውያን፣ በተለይም የእኛ የኢትዮጵያውያን ኩራት የሆነው አቤ ነፍሱ በሰላም ታርፍ ዘንድ እየተመኘኹ፣ ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድኅን “አበበ እንጂ መቼ ሞተ!” ብሎ ከተቀኘው ላይ እኚህን ስንኞች ጋበዝኳችኹ።



"...
የምድር ዓለሙ ገሞራ
አገሩን በክብር ያስጠራ
ሳተናው እግረ ጆቢራ
ሎጋ ቢቂላ ዋቅጂራ፣
...
በአገር ፍቅር ልቡን ሞልቶ፣ ላቡን ነጥቦ የዋተተ
የዓለምን ጀግና በአድናቆት፣ በቅን ቅናት ያስሸፈተ
አልሞተም እንበል እባካችሁ፣ ‹‹አበበ እንጂ መቼ ሞተ!››..."

አበበ እንጂ መቼ ሞተ! ፡ ጸጋዬ ገብረ መድኅን

Marta Pausilli & Priya Sippy. (2024, July 17). BBC News. Retrieved from BBcC Sport: https://www.bbc.com/sport/athletics/articles/cqv5qde4w52o

ሻምበል አበበ ቢቂላ. (2023, June). Retrieved from Sewasew: https://am.sewasew.com/p/%E1%88%BB%E1%88%9D%E1%89%A0%E1%88%8D-%E1%8A%A0%E1%89%A0%E1%89%A0-%E1%89%A2%E1%89%82%E1%88%8B-abebe-bikila

ተፈሪአለሙ (2015 ዓ.ም, ሐምሌ 29). በዓለም ኦሎምፒክ መድረክ ፋና ወጊው አትሌት አበበ ቢቂላ [የሬዲዮ ዝግጅት]. አዲስ አበባ.

አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ ሲታወስ. (2020, ጥቅምት 25). Retrieved from ቢቢሲ አማርኛ : https://www.bbc.com/amharic/news-54672466

እንግዳ, ፋ. (2006 ዓ.ም). *ታሪካዊ መዝገበ-ሰብ ከጥንት እስከ ዛሬ ቅጽ 2* .

ሐዲስ አድባር - 2

ቃለአብ አጣይነህ



ሦስት: የመጥምቁ ዮሐንስነት ግብር - አዲስ ጨዋታ አምጡ!

ዓለማየሁ በእነዚህ መጻሕፍቱ እያለን ያለው ትክክለኛ ነገር ግን ምንድነው?

ከላይ ዓለማየሁን ከመጥምቁ ዮሐንስ ጋር ስናናጽረው በምድረ በዳ እንደሚጮህ ድምጽነቱ ብቻ አይደለም። በአሻጋሪነቱም ጭምር ነው። መጥምቁ ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው ነቢይ በመሆን የሐዲስ ኪዳንን መምጣት አብስሯል። ዓለማየሁ ገላጋይ በመጥምቁ ዮሐንስነት ተግባሩ ከብሉዩ ትርክት ወደሐዲስ ትርክት እንድንሸጋገር ነው ጩኸቱ።

የተጠላው እንዳልተጠላ ይህንን ብሉዩን ትርክት የማፍረስ (Deconstruct የማድረግ) እና አዲስ ትርክት የማምጣት ተግባር በተረዳ መልኩ (Boldly) የተከወነበት መጽሐፍ ነው። ከዚያም በላይ በቴክኒክ ደረጃ ዓለማየሁ ገላጋይ ከፍታውን ያሳየበት ሥራውም ጭምር ነው።

ደራስያን የተማሩት ትምህርት ወይም የሚሠሩት መደበኛ ሥራ የሚያስቡበት መንገድ ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም። አዳም ረታ ለምሳሌ የካርታ ሥራ እና የጂአግራፊ ትምህርቱ በየልቦለዶቹ ላይ ተጽዕኖው በጎላ መልኩ ይታያል። ለምሳሌ በሠንጠረዥ የሚገልጻቸው ሁነቶች አተራረክ፤ ለጥቃቅን ነገሮች ያለው ስሱነት፤ በየልቦለዱ የሚያስገባቸው የእጅ ስዕሎችና ፎቶግራፎች ፤ለጂኦግራፊያዊ ቦታዎች ያለው መረዳት በግልጽ ይነበባሉ። ከአክሊሉ ደሳለኝ ጋር ባደረጋቸው ቃለ ምልልሶች ውስጥም ልቦለዶችን ስለመሳል እና በግራፍ ስለመግለጽ (Pictorial Representation) ደጋግሞ ያነሳል። ዓለማየሁም ከዚህ የተለየ አይደለም። ጋዜጠኝነቱ ደጋግሞ ደራሲነቱ ውስጥ ይገባል። በተለይ በሦስቱ መጻሕፍት ውስጥ ያሉት ገጸ ባሕርያት... በተለይ በተለይ ደግሞ ወንዶቹ ተንታኞች ናቸው። ስለነገሮች መግለጫ መስጠት ይወዳሉ። ዶስትዮቭስኪ ተቀሽሮ ነገር ናቸው። ታለ በእውነት ስም ውስጥ መዝገበ ቃላት እንደቅኔ ቤት ግስ ገሠሣ አቡነ ዘበሰማያት እየደገመ ይሸመድድ የነበረ ረድ ሠርዌ በሆነ ተአምር ሐሰተኛው በእምነት ስም ላይ ዶስትዮቭስኪን ይጠቅሳል። ዓለማየሁ ከሐሳቦች ጋር የሚጫወትበትን ሜዳ ለማግኘት በየልቦለዱ ውስጥ እየቃሙ የሚፈላሰፉ ሰዎችን ያስገባል። ናዝሬት ራስ ገዝ ምሳሌ ነው። ቤባንያ ላይም ጥል ሲጫወቱ የምናገኛቸው ጎረምሶች በልብወለዱ መጨረሻ ስለዶስትዮቭስኪ የሚከራከሩ ቃሚዎች ይሆናሉ። "የማያስብ ገጸ ባሕርይ እኔ ልቦለድ ውስጥ ምን ያደርጋል?" ይላል ዓለማየሁ። እውነትም የማይሞግት፤ የማይጠይቅ፤ ዶስትዮቭስኪን የማይጠቅስ ወንድ ገጸ ባሕርይ የለውም። በተቃራኒው ግን ሴቶቹ በሙሉ አመክንዮ የማይገዛቸው፤ ወይ በጥንቆላ፤ ወይ በኮከብ ቆጠራ የሚያምኑ፤ ወይ ዝም ብሎ ለወንድ ሲሉ ከአመክንዮ የወጣ ነገር የሚያደርጉ ናቸው። ናዝሬት ራስ ገዝ ውስጥ ወንዶቹ ስለእግዚአብሔር ሲመራመሩ ሴቶቹ እነሲፈን ከማዳመጥ እና የሚያሳፍር ዓይነት አስተያየት ከመስጠት የዘለለ ሥራ የላቸውም። ሴቶቹን ከገጸ ባሕርይ አይቆጥራቸው እንደሆነ እንጃ። (የጾታውን ነገር ወረድ ብለን ለብቻው እናየዋለን።) አንዳንዴ ደግሞ የመጽሔት መጣጥፍ ላይ እና ወጎች ላይ የሚገቡ፤ ልቦለድ ውስጥ ሲገቡ ግን አላስፈላጊ የሚመስሉ እና ደረጃውን የሚያወርዱ ቀልዶች እና አገላለጾች ይገባሉ። ለምሳሌ በፍቅር ስም ላይ የብዜን ፉርጎን ብሴአዴግ ብሎ ይገልጻቸዋል። ብሴአዴግ ከፍትሕ መጽሔት የተወሰደች ቀልድ ናት። የዛሬ አርባ ሃምሳ ዓመት እንደተጻፈችበት ዘመን የምታስቅ አይመስለኝም። አንድ ቦታ ላይ ደግሞ "የዓመቱ በጀት መዝጊያ የሚመስል ኃይለኛ ዝናብ እየዘነበ..." ይላል። መልሶ ደግሞ በሌላ ቦታ በፍቅር ስም ላይ (ገጽ 137) "በአማርኛ የምንፈራው በእንግሊዘኛ የምንደፍረው ሴክስ ይኼ ነው?" ይላል። አስቡት ከወሲብ ታሪክ በጎላ እንደዚህ ያለ ማኅበረሰባዊ ተኃዝቦት። እነዚህ ጋዜጠኝነቱ ምን ያህል ተጽዕኖ እንደሚያሳድርበት ለማሳያነት የጠቀስኳቸው ናቸው እንጂ የያዝነው ፀጥር ስንጠቃ

አይደለም።

እንዲህ ያሉ የማብራሪያት፣ የመተቸት እና የማጫወት ግብሮች በሙሉ የደራሲው ማንነት ናቸው። ዓለማየሁን ልብ ብሎ ያየ ሰው አልአዛርንም ሆነ ሌሎቹን ወንድ ገጸ ባሕርዮቹን እርሱ ውስጥ ይመለከታል። እንደ ዶክተር አሮን እና እንደ ዶክተር ማርቆስ ያሉ የMentor Archetype ያላቸው ገጸ ባሕርያት ብቻ አብደላ እዝራን ያስታውሱናል። አብዛኛዎቹ ግን በጋዜጠኝነቱ ጠልፎ የጣላቸው ገጸ ባሕርያት ናቸው። የተጠላው እንዳልተጠላ ላይ የተጠቀመው ብሉይ የመዝሙርና የቅኔ ቅርጽ ግን ይህን ሁሉ በሆነ መልኩ (ሙሉ ለሙሉ ባይሆንም) ገድቦታል የሚል ሐሳብ አለኝ። የቴክኒክ ልህቀቱ ከዚህ የመጣ ይመስለኛል።

እዚህ ጋር ብሉዩን የእግዚአብሔር ትርክት እናፍርስ ለሚል ጽሑፍ ብሉይ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅርጽ መምረጡ ፈገግ የሚያሰኝ ኩሸት ነው። ምክንያት ልንፈልግለት እንችላለን። አንደኛው ምክንያት የጠቢቡ ሰሎሞን ጉዳይ ነው። ከፍቅር ስም ጀምሮ 'እኔ እና ሰሎሞን ብቻ' እያለ ራሱን ከሰሎሞን ሲያናጽር ነው የመጣው። ይኼ ንጽጽር ወሪሳም ላይ ያለ ነው። ጠቢቡ ሰሎሞን እንዲፈርስ የሚታገለው የክብረ ነገሥት ትርክት ዋናው ተዋናይ ነው። ሐዲሱም ትርክት የራሱ የሆነ ሴት የሚያተራምስ፣ ደግሞም ከሴት አጥብቆ የሚሸሽ (ቢያንስ በጽሑፍ) ሐዲስ ሰሎሞን ያስፈልገዋል። ሁለተኛው ምክንያት ቴዎድሮስ አጥላው እንደሚለው ሐዲሱን ሥርዓት፣ ማለትም ከእግዚአብሔር መነጠልን የማጽናት (የ Secularism) መዝመረ ዳዊት ሊሆን ይችላል። ከዚያም በላይ አንዳንዶች እንዳመለከቱትም፣ እርሱ ራሱም እንደተናገረው፣ ይህን በሚጽፍበት ወቅት የነበረውን የወጣቱን ዓለማየሁ መከራ ኢዮባዊ በሆነ ቋንቋ ለመግለጽ ታስቦ የገባ ይሆናል። ኢዮብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትዕግስተኛ ነው ቢባልም መጽሐፉን ያነበቡ ሁሉ ግን ምን ያህል ሞጋች እና ተሳፋጭ እንደነበረ መመልከት ይችላሉ።


ከቴክኒክ ውጪ ግን የመጽሐፉ ሁለንተናዊ ጭብጥ 'አዲስ ጨዋታ አምጡ!' ነው። "አንጋጠን ስንጸልይና ስንጠብቅ ማጎንበስና መሥራትን ረሳን፣ አሁን ደግሞ አጎንብሰን መጸለይና መለመን እንተው!" የሚል ነው። "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች።" የሚለውን መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ ትርክት አፍርሶ "ኢትዮጵያ እጆቿን ለሥራ ታውለው።" የሚለውን አዲስ ትርክት መገንባት ነው። የሚፈርስ ሃገራዊ ትርክት አለ፣ ይኼ ትርክት ለዘመናት በሃገሪቱ ውስጥ ገዢ የነበረ ትርክት ነው። ለዚህ መጣጥፍ "የክብረ ነገሥት ትርክት" እንበለው። በዚህ ትርክት ምክንያት ብዙ ዘመን በጦርነት እና በረሐብ ስንታመስ ነው የከረምነው። እንደዓለማየሁ ገላጋይ ሐሳብ መፍትሔው ይኼን ትርክት ከሥሩ መንግሎ ጥሎ ሌላ ሐዲስ ትርክት መፍጠር ነው። ሁለተኛው እና ሐዲሱ ትርክት "የተጠላው እንዳልተጠላ" ትርክት ብለን የምንጠራው ነው። በግልጽ ለመበየን ይቸግራል። መሠረታዊው ሐሳቡ ግን ቤተ መቅደሶቻችንን አፍርሰን ወደሥራ መግባት አለብን የሚል ነው። ይኼን ጭብጥ በማስተላለፍ ረገድ መጽሐፉ ያነከሰበት ቦታ የለም። ማለት የፈለገውን ሁሉ ይላል። የአቅም ማነስ ችግር የለበትም። እውነት ለመናገር የሦስቱ ተለጣጣቂ መጻሕፍት ጭብጥም ምንም እንኳ ዘግይቶ ቢገለጽ ይኼ ነው። ሐሰተኛው በእምነት ስም ላይ በሐሰተኛው አንደበት እንዲህ ይላል።

> *“የንግሥተ ሳባ ትርክት አለ ደሞ፡፡ ጥበብ ፍለጋ ወደ ንጉሥ ሰለሞን ሄደች፣ ትሂድ፣ ከእርሱ ጋር ወድቃ አረገዘች፣ ታርግዝ። ልጇን ለአቅመ አዳም ሲበቃ ወደአባቱ ላከች፣ ትላክ፣ ይሄ ሁሉ ችግር የለውም፡፡ ግን እንዴት ልጅ አገሩ ላይ እንዲነግሥ የአባቱን ቡራኬ ትጠይቃለች? ያኔኮ ሰሎሞን የአንድ የተኮማተረች ቀበሌ ትንሽ ንጉሥ ነው። እንዴት ይሄንን ታላቅ ህዝብና ሀገር፣ ለዛ በአካባቢው ለተናቀና እንዳለ ለማይቆጠር [ሥ]ር[ወ] መንግሥት አሳልፋ ትሰጣለች? ያኔ እኮ ኢትዮጵያ እስከ ህንድ ውቅያኖስ የምታስገብር ታላቅ ሀገር ነበረች። ወንድምዓለም ይሄ ነው የሆነው፣ ይሄ መሆኑ ደግሞ ያምማል! በጣም ያማል!!!" (ገጽ 297)*

ነገር ግን ሐሳቡ መሞገት ያለበት ነው። በዋልያ መጻሕፍት መጽሐፉን በተመለከተ በነበረው ውይይት አንዲት ልጅ እንደዚያ ትጠይቃለች። "ሃይማኖታዊውን ትርክት ንዶ ሐዲስ የሥራ ትርክት መገንባት የሚለው ሐሳብ አዲስ ነው ወይ? 'እስከመቼ ተቀባይ እንሆናለን። የራሳችንን አስተዋጽዖ አናመጣም ወይ? እስከመቼ የዛሬ ምናምን ሺህ ዓመት እንደተማርነው በበሬ እናርሳለን?' ያላለን ደራሲ አለ ወይ?" ትለዋለች። መልሱ "አየሽ ወጣት ስትሆኚ ሁሉ አዲስ ይመስልሻል።" የሚል ዓይነት ነው። በዚህ ውይይት ውስጥ አብዛኛውን ነገር ወጣቱ ዓለማየሁ ላይ አላክኮ ነው የሚያልፈው። ፊት ለፊት መጋፈጥ የሕጻን ወይ የነቢይ ተግባር ነው አላልንም? በነቢይ ወግ መጋፈጥ በመጋዝ የሚያስተረትር፣ በኩላብ የሚያሰቅል ነውና ይህን የማይፈልግ ቢኖር ሁሉን ነገር ወደሕጻንነት ይመራዋል። አጼ ቴዎድሮስ ለማድረግ የሞከሩት ምንድነው? በቅርብ ጊዜ እንኳ ይኼንን ትርክት የመናድና ወደሥራ እንሒድ የማለት ነገርን በ'ያ ትውልድ!' ውስጥ አልተመለከትንም ወይ? ዓለማየሁ ይህንን ሳያይ ቀርቶ ነው?

ለምሳሌ የ'ያ ትውልድ'ን እንቅስቃሴ እንመልከት።

በፍልስፍናው የሚወሳ የቼስቴትሮን አጥር (Chestetron Fence) የሚባል ምሳሌ አለ። ይህን ምሳሌ ያቀረበው ጄ ኬ ቼስቴትሮን (J.K Chestetron) የተባለው የ19ኛው መቶ ክፍለዘመን ፈላስፋ፣ ገጣሚ እና ፀሐፌ ተውኔት ነው። ምሳሌው እንዲህ ነው። ወደሆነ ቦታ የሚሔድ ሰው በመንገዱ ላይ አጥር ቢያጋጥመው ማድረግ ያለበት ነገር ምንድነው? አጥሩን ማፍረስ ነው? ወይስ መጀመርያውኑ አጥሩ ለምን እዚህ ጋር ቆመ ብሎ ለማወቅ መሞከር? እንደቼስቴትሮን አመለካከት አጥሮች እንዲሁ አይሠሩም። ጊዜ፣ ጉልበትና ሃብት ይፈልጋሉ። ስለዚህ አጥር ካለ የታጠረበት ዓላማ አለ ማለት ነው። አጥሩን ለመጣስም ላለመጣስም ይህንን የታጠረበትን ዓላማ ማወቅ ግድ ይላል። በ'ያ ትውልድ' ዘመን የሆነው ይኼ ነው። የዘመኑ መንፈስ አጥር መናድ ስለነበረ ብቻ የተናዱ አጥሮች ይበዛሉ። በአብዛኛው በሶሻሊስት ሃገሮች ውስጥ እንደዚህ ያሉ ብዙ ነገሮች ተካሒደዋል። ለምሳሌ በሶሻሊስት ቻይና ውስጥ ከ1958 እስከ 1962 የቆየ The Great Leap Forward የሚባል ዘመቻ ነበረ። በዚህ ዘመቻ እንዲተገበሩ ከተያዙት ዕቅዶች አንዱ ትንኞችን፣ ዝንቦችን፣ አይጦችን እና ድንቢጦችን ከሃገረ ቻይና ማጥፋት ነው። "እነዚህ አራት ነገሮች ናቸው ግብርናችንን ያዳከሙት፣ እነርሱን ካላጠፋን እረፍት አናገኝም።" ተባለ። በኋላ ገበሬዎቹ



በመንግስት አስተባባሪነት ተረባርበው ድንቢጦቹን በዘመቻ አጠፏቸው። በየዛፉ እየሔዱ ቆርቆሮ እና ድስት እየደበደቡ የሚያርፉበት ፋታ በማሳጣት በድካም ወድቀው እንዲሞቱ አደረጓቸው። አንዳንዶች ጎጇቸውን አውርደው ጨፈለቁት። አንዳንዶች በጠመንጃ ድንቢጥ ማደን ጀመሩ። በዚህም ትጋታቸው የቻይና ድንቢጦች ለመጥፋት ተቃርበው ነበር ይባላል። በኋላ ግን ድንቢጦቹን አጠፋን ብለው እፎይ ሲሉ አዝመራቸውን ከየት መጣ የማይባል ትል ድምጥማጡን አጠፋው። ሲያጣሩ ለካ... እስካሁን አዝመራቸው በዚህ ትል ያልተጠቃው ድንቢጦቹ እየለቀሙ ይበሉት ስለነበረ ነው። በዚህ ዘመቻ ምክንያት ቻይና ዝናብ ሳይቸግራት፣ ድርቅ ባልተከሠተበት እና ብዙ ማምረት በምትችልበት ዓመት ረሐብ ገብቶ ብዙ ሰው ፈጅባት።

እኛም ሃገር ከዚህ የባሰ ሞኝነት ተሠርቷል። የ'ያ ትውልድ' ሰዎቻችን በተትረፈረፈው እና ይበል በሚያሰኘው የሥነ ጽሑፍ ባህላቸው ውስጥ ጣት ከመጠቋቆም የጂላጦስ ተግባራቸው ተግ ሲሉ ሠርክ ግመሷን እየተዉ ትንፏን መናዘዝ ከጀመሩ ሰነባብተዋል። ሁሉም 'ያ ትውልድ' ወርቃማ፣ አብዮቱም የማያስቀሩት (Inevitable) እንደነበረ ካነሱ በኋላ ግን አፈጻጸሙ ላይ ችግር በመፈጠሩ ምክንያት እንደከሸፈ ያስረዳሉ። የኢሕአፓም፣ የመኢሶንም፣ የደርግም ሰዎች ቢጠላሉም በመሠረታዊነት በዚህ ሐሳብ ላይ መስማማታቸው አይቀርም። እውነታው ግን ምንድነው? የቼስቴትሮንን አጥር ያፈረሱት በግብታዊነት መሆኑ፣ አብዮቱ የተደራጀ አመራር ያልነበረው የሃገር ፍቅር ያናወዛቸው ጎረምሶች ተግባር መሆኑ። ይኼንን ለመቀበል ብዙዎቹ ፈቃደኞች አይደሉም። በእርግጥም ወጣትነትን... ከምንም በላይ ሕይወትን የከፈሉለት ተግባር በመሠረቱ ትክክል አይደለም ሲባል ለመቀበል ይቸግራል። ነገር ግን ቁጭ ብለን መወያየት አለብን። እስካሁን ድረስ እንደሃገር የሚያጋጥሙን ችግሮች ከዚያ ትውልድ የሚመዘዙ አይደሉም ወይ? ያኔ እንደቀልድ የናድነውን የቼስቴትሮን አጥር፣ እንደቀልድ ያፈረስነውን ብሔራዊ ትርክት እስካሁን ድረስ መተካት ችለናል ወይ? ወዘተ ወዘተ...

ወዶ አይደለም ዳኛቸው 'አደፍርስ' ያላቸው። ክርስቶስም በወንጌል "ንግሥተ አዜብ ትትነሣእ... ወትትዋቀሶሙ ለዛ ትውልድ።" ማለቱ እውነቱን እንጂ ነው ያሰኛል።
ዓለማየሁ ከ'ያ ትውልድ' የተለየ የነገረን ነገር አለ? ቤተ መቅደሶቻችን ዘግተን ወደሙዚየምነት በመቀየር ወደእድገት በሕብረት ዘመቻ የሔድነው እኮ ከሠሞኑ ነው። ምን ለውጥ አመጣን? ለምን በቂ የሚተካ ትርክት ሳያመጣ የነበረውን ትርክት (አሁንም ካለ ማለት ነው!) ሊያፈርስ ይሞክራል? ለምን የቼስቴትሮንን አጥር ይጥሳል? ይኼ ሁሉ መጠየቅ አለበት። ዓለማየሁም ሊሞገት ይገባዋል።

ይኼን የምንለው ብሔራዊ ትርክት አለመኖሩ ያመጣብንን ጣጣ ስለምናውቅ ነው። ነፍሱን ይማረውና አያልቅበት ኒቼ እግዚሃር ሞቷል ሲል የተናገረው ተራ የነገረ ጎልውና አዋጅ ብቻ አልነበረም። ማኅበረሰባዊ ተኃዝቦቱን ጭምር እንጂ። በሰው ሕይወት ውስጥ ሃይማኖት ያለው ቦታ መንምኗል ነው እያለን ያለው። በምእመናን ኑሮ ውስጥ ፈሪሃ እግዚአብሔር ዋጋ አጥቷል ነው። ያኔ "በሕግ አምላክ" ብትል ማንም አይሰማህም። ያኔ የማርያም መንገድ ብትጠይቂ የሚሰጥሽ የለም ነው ነገሩ። ሙሾ ነው ያወረደው ኒቼ። ምን ይውጠናል ዓይነት:: ምን እንሆናለን ዓይነት። የእግዜር መሞት የትርጉም መሞት ምሳሌ ነው:: ቀስ በቀስ ሰው የራሱን እግዜር ለመፍጠር እንደሚሞክር ገምቷል። ያ ትውልድ በአፍላ ጉልበቱ ማቴርያሊዝምን አውጆ እግዜር የለም ሲል የገደለው እግዜር አከል የሆኑትን ጃንሆይን እና ዘውዳዊ ሥርዓታቸውን ብቻ ሳይሆን ምናምን ሺህ ዘመን እንደሃገር ያኖረንን ፉንሲ ትርክት ጭምር ነው። ደርግ አምጥቶ ሶሻሊዝምን ሲጭን በሆነ መልኩ ስለማክዳ እንድንረሳ መፈለጉ ነበር። ቀጥሎ ብሔር ብሔረሰቦች ብለንም፣ መደመር ብለንም ያንን ሃገራዊ ትርክት መመለስ አልቻልንም። ከሁሉ የሚያስቀው ደግሞ ሕዳሴ ይሉት ነገር ነው። ያኔ 'ዘ ኮምዩኒስት ማኒፌስቶ'ን በጥናት ቡድን ለብልበው ኢትዮጵያ ምንም ሃገራዊ ትርክት

የላትም ያሉን ጎረምሶች በሽምግልናቸው ወቅት ሞክረው ሞክረው ሲያቅታቸው ለመደገፍ ያነነበሱት በጉብዝናቸው ወራት ወደገረሰሱት የኢትዮጵያ ጥንት መሆኑ ያስቃል።

አያልቅበት ኒቼ ሌላም ሌላም ብዙ ነገር ብሏል። የእግዜሩና የእግዜር አከል በያኝ አካላት መሞት ያመጣው ትርጉም ማጣት ሁለት ውጤት እንደሚኖረው ተንብዮ ነበር። አንደኛው ጠቅልሎ የሚገዛ አምባገነን ነው። ለአባቶቻችን የደረሳቸው ዕጣ ይኼ ነው። ትርጉም ያጣን ሕዝብ መግዛት ይቀላል። ሌጣዋን የተገኘች ፈረስ ለመጫን ታመቻለችና። እስከዛሬ ድረስ በነቀሉት የዘመናት ትርክት እግር የሚተካ ፍልስፍና ባለመገኘቱ ያመጡልን ጫማ ሁሉ ጠብቦን ስንሰቃይ... ባስ ሲልም የጫማውን መጥበብ እግራችን ላይ እያሳበቡ አንድ በአንድ ጣቶቻችንን ሲቆርጡ ከርመው አላስቆም አላራምድ ብለውናል።

ለዚህ የሚሆን ምሳሌ አሁንም ከቻይና አብዮት እንምዘዝ። እስካሁን ቻይናውያን ያላገገሙበት አንድ ቁስል አላቸው፤ የባህል አብዮት የሚባል። ማኦ ዜዱንግ በነባሩ ባሕል ውስጥ ካፒታሊዝም ገንኖበታል ብሎ በማሰቡ የዩንቨርሲቲ ተማሪዎችን መልምሎ ቀዩ ዘብ (The Red Guard) በሚል ጥንታዊው የቻይና ባሕል ውስጥ ያሉ ካፒታሊዝም የተፋፋማባቸውን ቦታዎች በሙሉ እንዲያጸዱ አዘዛቸው፡፡ እነርሱም በተሰጣቸው ትእዛዝ ሥራቸውን በጉልበት ሳይቀር ተልእኳቸውን ማስፈጸም ጀመሩ። ጥንታዊ የሃይማኖት ቤተ መቅደሶች ተመዘበሩ። ብዙ መጻሕፍት ተቃጠሉ። ብዙ መነኮሳት ተገደሉ። ልክ በእኛ ሃገር ገድለውን "ቀይ ሽብር ይፋፋምብን!" የሚል መፈክር እንዳስታቀፉን ሁሉ እዚያም እንዲሁ ሰዎች ሲገደሉ ጥፋታቸውን የሚዘረዝር ረዥም ጽሑፍ አንገታቸው ላይ ይንጠለጠልባቸው ነበር። እንዳሰቡትም ብሎዩ ትርክት ፈረሰ። ነገር ግን ለማፍረስ የተኼደበት ርቀት ራሱን ማኦ ዜዱንግን ሳይቀር አስፈርቶት ስለነበረ በገዛ እጁ የመለመላቸውን የቀዩን ዘብ አባላት ያስቆሙለት ዘንድ የፋብሪካ ሠራተኞችን መረጠ ላከ። እነዚህ የፋብሪካ ሠራተኞች ተማሪዎቹን አሸንፈው የሥልጣን ዘመናቸውን ደመደሙት።

ከዚህ በኋላ ግን ማኦ እነዚህን በጭንቅ ቀን የደረሱለትን የፋብሪካ ሠራተኞች ለማመስገን ያደረገው ነገር ግራ የሚያጋባ ነው። የፓኪስታኑ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ለሥራ ጉብኝት ወደቻይና ሲመጣ እንደገጸ በረከት ይዟቸው የመጣቸው ማንጎዎች ነበሩ። እነዚህን ማንጎዎች በምስጋና መልክ እንደስጦታ ለየፋብሪካው አንድ አንድ ላከ። ብዙዎቹ የፋብሪካ ኃላፊዎች እና የፋብሪካ ሠራተኞች ማንጎዎቹ ለምን እንደተላኩ እና ምን ማድረግ እንዳለባቸው ግልጽ አልሆነላቸውም ነበር። አንዳንዶቹ ማንጎዎቹን ልጠው ተከፋፍለው በመብላታቸው ተረሸኑ። አንዳንዶቹ ማንጎውን ተጠቅመው የራሳቸውን ሃይማኖት መሠል ክንውን (Cult) በመፍጠር ከማንጎው እንደሥጋ ወደሙ መቀበል ጀመሩ። አንዳንዶቹ ማንጎዎቹን በኋላ ሲጠየቁ ለመመለስ እንዲያመቻቸው የማይበላሹበትን መንገድ በመፈለግ ተጠመዱ። በኋላ ይኼ የማኦ ማንጎ ጉዳይ እየበረታ ሔዶ ማኦ ለሠፊው ሕዝብና ለሶሻሊስቱ መንግስት ሲል ንቆ የተወውን ጣፋጭ ሕይወት የሚወክል ትእምርት ሆነ። ሰውየውን ወደመለኮታዊነት ከፍ አደረገው። ሰዎች ፕሮግራም እየተያዘላቸው እና ከየፋብሪካዎቻቸው በሥራ ሰዓት እየወጡ ማንጎዎቹ እንዳይበላሹ ከተቀመጡበት ብርዳማ እና በረዷማ ተራራ ላይ በመሔድ እንዲጎበኙ በመስሪያ ቤት ደረጃ መገደድ ጀመሩ።

ጥያቄው... ለዓለማየሁ ገላጋይ - ጣዖት መስበራችን አዲስ ጣዖት ለማምጣት ከሆነ ምን የሚፈይድልን ነገር አለ? እስካሁን አካልበው ለውጥ ለውጥ ያሉን ሁሉ ልጓም እየተነጣጠቁ ጋለቡን እንጂ መቼ አሳረፉን? በአጠቃላይ 'እግዚአብሔር የለም፤ ትቶናል። ከእንግዲህ በግንባራችን ላብ፤ በእጃችን ሥራ፤ በሰው ልጆች ተዓምር እንታመን!' የሚለው አስተምህሮ በራሱ ተቋማዊ (Institutionalized) ሆኖ ሲመጣ ችግር አይሆንም ወይ? በ'የተጠላው እንዳልተጠላ' መጨረሻ ላይ ሐዋርያው ማስተዋል (እስከነአሙም ማስተዋል፤ በኋላ የምናነሳውን ሦስተኛ አድባር አመክንዮን ያጠይቃል።) እውነትን ስለተናገረ ለሞት ተላልፎ

መሠጠቱ የዚህ ማሳያ አይደለምን? ኒቼ በዛራቱስትራ አንደበት ደቀ መዛሙርቱን እንዳይከተሉት መበተኑ ለዚህ ሳይሆን አይቀርም። ተቋማዊ የሆነ 'ሃይማኖት አያስፈልግም!' ማለትም ቅርጹን የቀየረ ሃይማኖት ነውና። እና አንዱ ትርክት በገነነ ቁጥር ስንደሁኔታው ጣዖት እየቀያየሩ በመንጋ ከመነዳት እና እንደማስተዋል የበራላቸውን እስጢፋኖሶቻችንን በድንጋይ ከመውገር በቀር ምንም ተስፋ የለንም ማለት ነው?

አባቶቻችን በወጣትነታቸው ገብተው ሲንቧቸበት ከነበረው የአቻ ትርጉም ፍለጋ ዋና... የሰመጡት ሰምጠው የተረፉት በእርጅና ዘመናቸው እያለከለኩ ሲወጡ ለእኛ ለልጆቻቸው ያወረሱን ሁለተኛው የእግዜር ሞት ዳፋ ትርጉም አልባነት እና ተስፋ መቁረጥ ነው። ያ ሁሉ ሰው ሞቶ ያልመጣ ነጻነት መች እንደሚመጣ አይታወቅም ብለን እንደምጽአት ቀን በምናኔ ጠበቅነው። ከወደቁ በኋላ አለመንፈራገጥን የተማርነው ያኔ ነው። ደግሞ አያፍሩም! በኩሽት ኮትኩተው ያሳደጉን አባቶቻችን መልሰው በወኔ ቢስነት፣ በሥርዓት አልበኝነትና በጫታምነት ሊወነጅሉን ይፈልጋሉ። ፈትፍቶ ካጎረሱ በኋላ ለምን ዋጥከው ብሎ ጠብ አለ? የድሮ እርድናቸው ከፀጉራቸው ጋር አብሮ ሳይኮበልል አይቀርም።

አንዳንዴ 'ራሳቸውን የሚወቅሱበት መንገድ አጥተው ይሆን ወጣቱ ላይ የሚወርዱበት?' እላለሁ። አንዳንዴ 'የምር ኩርንችት ዘርተው በለስ ጠብቀው ነበር?' እላለሁ። አንዳንዴ ለእነርሱ እረፍት ሲባል ብቻ ትውልዱ ተስፋ ባይቆርጥ እመኛለሁ። ዓለማየሁ ገላጋይ ከእነዚህ የድሮ አራዶች የተለየ በ"የተጠላው እንዳልተጠላ" ላይ ምን የሚለን ነገር አለው? ይኼ በአያሌው መሞገት አለበት።

የመጨረሻው ክፍል በቀጣይ ዕትም ይቀጥላል...

አግቢ አግቢ

እንደመሐል ጣት፣ መሐል እገኛለሁ። ከፊት (ከቀኝ) አባትና እናቴ፣ ከኋላ (ከግራ) ወንድምና እኅቴ። ለአቅመ ሔዋን መድረስ ሳይሆን ገስግሼ ላመልጠው እየቀረብሁ ያለሁ።

እናም የ'አግቢ' ጭቅጭቃቸው እጅግ አሰልችቶኛል። መቆሚያ መቀመጫ አሳጥቶኛል።

አራዳው አባቴ፣ "አሁን ካላገባሽ... ትንሽ ዓመት ብትቆዪ የሚያገኙሽ ወንዶች 'ሹገር ማሚ!' ነው የሚሉሽ።" ሲለኝ...

ምስኪኗ እናቴ፣ "አይመስልም እንጂ መንግሥትም ሆነ ጡትሽ እንደተሰቀሉ እኮ አይቀሩም!!" ስትለኝ...

ወንድሜ፣ "በዚህች ሀገር እና ባንቺ ተስፋ ከቆረጥሁ ቆየሁ።" ሲለኝ...

ትንሿ እኅቴ፣ "አግብተሽ ሻማ ያዥ ታደርጊኛለሽ ብዬ ሳስብ አደግሁ። ቢያንስ ሚዜ እንድሆን ብታገቢስ?" ስትለኝ...

ሲለኝ + ስትለኝ + ሲለኝ + ስትለኝ = ሲሉኝ።

እናም እንዲያ ሲሉኝ እንደመሐል ጣትነቴ መሐል ጣቴን ባወጣባቸው በወደድሁ። ግን ቤተሰቦቼ ሆነው ተቸገርሁ።

ኧረ የባል ያለህ!!

***

ልብወለድ



ሕይወት - ዘለሰኛ...

ደራሲ | ቤዛዊት

ሕይወቷን የሞላው መባከን ልብ ልቤን ይበላኛል... ስለተቆጠረ ስላልተኖረ ዕድሜዋ፣ "በምን ቁጥር ከሰው ተራ ኖረች ተባለ?" እላለሁ... የወየበ ሳቅን ከጥርሷ ፈልጌ አላጣም። የተለየ ፈገግ አላት፣ የ'ርሷ ብቻ የሆነ። የይምሰል ፈገግ ትልልኛለች። "ተይ፣ አትሳቂ!" አያምርም እላለሁ በውስጤ... እውነት ልምሰል ልምሰል ቢልም ውሸት አምሮ አያውቅም ...

"አ ውሸቷን ነው! የደላት መስላለች። "....

ልብ ልቧን ስለሚበላት የማያልቅ እጦት፣ አንጀቷን ስለቆረጠ ባይተዋርነት፣ ስለማያልቀው መሰበሯ፣ ስለማያንድል ሞልቶ ስለፈሰሰ የበደል ፅዋዋ ለማንም አትነገርም... እንዲሁ በዝምታ ስትኖር አያታለሁ... ወሬያችን ከፊልም እና ከመጽሐፍ፣ 'ከወጥቻለሁ' እና 'መጥቻለሁ'፣ 'ከምን ልሥራ' እና 'ከምሳ ደርሷል' አያልፍም።

ታሳዝነኛለች።

እርሷ ያለችበት የሕይወቴ ገፅ ሁሉ በትካዜ የተሞላ ነው። አብሮነትን አትችልበትም። የምታምነው ጌታ ኩሎ የሰጣት መልኳ ብቸኝነት ነው። እጆቿ ማቀፍን አያውቁም። ሁሌም ጭኖቿ መሐል ወትፋቸው ትቀመጣለች። ዓይኗ ውስጥ ስላለው ከ'ሷ ወዲያ የሚረዳ የለም። ዓይኗ ይከብደኛል፣ ማየቷን አልወደውም፣ ሁሌም እሸሸዋለሁ። .

ልጅነቴን ከወጣትነቷ አዳብላ በልታብኛለች፣ መከፋቷን መቆዘሟን አብሬያት ተግቻለሁ። "ለምን?" የማለት ሥልጣን ባልተሰጠኝ ሕይወቷ ውስጥ ተዱዬ እኒህን ሁሉ ዓመታት ስኖር ከልብ የሳቅነው አንድ የጋራ ሳቅ አላስታውስም። ሊወዷት፣ ሊጠሏት የቸገረች ሆናብኝ ኖራለች። በሐዘኗ ሐዘኔን ታኮስሳለች፣ ፊቷ ላይ የሚታየው መሰበር የ'ኔን ያስረሳኛል፣ "እኔም ስብራት አለኝ!" ማለት እንዳልችል እድርጎኛል።

እርሷ የቅርቤ፣ እርሷ ከሥጋዋ ላይ ከፍላ ሥጋዬን የሞላች፣ ከደሟ ላይ ቀድታ ነፍስን የሰጠችኝ እናቴ - እኔ የልጅ ባዳዋ ...።


ልቀርባት በምጠጋው ልክ ስትሸሸኝ አያታለሁ። እኔን ለተወችባቸው ዓመታት ለራሷ ይቅርን አላገኝችም፣ ታየኝ ታየኝና አንገቷን ትሰብራለች ... "ተይ ይበቃሻል፣ ይቅር ብያለሁ!" እላታለሁ - በልቤ። ልትሆነኝ አለመቻሏ ከዓይኔ ያርቃታል። ስለበዛ ፀፀቷ አዝናለሁ፣ "አምላክ እንዴት እንዴት በደለሽ? እንዴት እንዴት አድርጎ በደለን?" እላለሁ። እናት እና ልጅ አድርጎ እንዳልፈጠረን እንደ ባዳ ሲያኖረን አየውና 'አያ አያልቅበት' እለዋለሁ።

ከአፏ የማትለየው ፈጣሪ አላት። ምን ምን እንዳደረገላት፣ የት የት እያገኘ እንደሚያሳምናት እንጃ "ሁሉ ለበጎ!" ትላለች። "እ'ሱ ያውቃል!" ትላለች። .... ለበጎ የተሰበረ ክንፏን ሲጠግንላት አይቼ አላውቅም። በየስርቻው ስር የተወታተፈ ላባዋን ሰብስቦ ሲገጥምላት አላየሁም። ሳውቃት ጀምሮ እንዲሁ ጥግ ፈልጋ ስትቆራመድ ነው።

ይሄ 'ሁሉ ለበጎ' ተደምሮ እንዴት ሩብ ተስፋ አይወጣውም?

ስለ መናፈቅ የ'ርሷን ያኽል ማፍቀሬም አላስተማረኝ... ስለ ዝምታ የቱን ያኽል ጥልቅ ብገባ በሷም ልክ አላገኝ... የቱም ግንባር፣ የቱም ፊት ላይ የ'ርሷን ያኽል መሰበር አልተፃፈም።

በይ በይ ያላት ቀን ያን ፈገግታዋን ፈገግ እያለች ከሶፍዋ ላይ ተቀምጣ ወረቀት ላይ ትሞነጫጭራለች። የእጅ ጽሑፏ ያምራል። እንዲህ ስትጽፍ ደስ ይለኛል ፣ የማውቃት በ'ርሱ በኩል ነው። ስትጨርስ ይሁን ወይ ሲሰለቻት ትቀዳድድና የቆሻሻ ቅርጫት ውስጥ ትጨምረዋለች። ተደብቄ አነሳና እገጣጥመዋለሁ። የማውቃት እርሷ ላይ ሌላ እርሷን ትንሽ ትንሽ እደምራለሁ ...



ተቀዳጁል።

አያት አያት እና "እወድሻለሁ እኮ!" ልላት እታገላለሁ፣ አፌን ይይዘኛል። "ማዘን እና መውደድ ለየቅል ናቸው።" ይለኛል፣ ማዘኔን እንጂ መውደዴን እኔም አምኜው አላውቅም።

ትነሳና ነጠላዋን ደርባ ትወጣለች ወደ በጎ ጌታ፣ ወደ በጎ አምላኳ ደጅ .... ግን ትጸልያለች? ባትጸልይ ነው እንጂ ሠርክ በምታሞካሸው እሷ ላይ እንዲህ ባልከፋ ነበር። ከጸለየች ደግሞ የጌታዋ ልብ እንደሰው ጆሮ ቅርብ አይሆን ይሆናል። ወይም ደግሞ የበጎነት ትርክት ዘመኑን ካበቃ በኋላ በግድ አራዝመንበት ይሆናል... እንጂ ይኼን ያህል ዳባ የምትባልስ አልነበረችም እላለሁ።

ሸምድጃት ጨርሻለሁ። አሁን አሁን እንደው ለልምድ አፈጥባት እንደሁ እንጂ አንድ አዲስ ነገር ፈልጌ አላገኝባትም። ማልዳ ትነቃለች፣ ቤተ ክርስቲያን ትሳለማለች ። ተመልሳ ቁርስ ትሠራለች፣ ቀሰቅሳ ታቀርብልኝና የራሷን ይዛ ትቀመጣለች። ከቁርስ ኋላ በሮዝመሪ የተቀመመ ሻይዋን ይዛ ሶፋዋ ላይ ትቀመጣለች። ከዚህ የተረፈ ጊዜዋን መጽሐፍ ታነብበታለች። ስትጨርስ ጠብቄ ያስቀመጠችውን አነሳና እጀምራለሁ። እንደዚህ እንደዚህ እሷን ስከተል ነው ማንበብ የለመድኩት።

ከቁንጥር ንግግር መሐል፣
“ዛሬ ፊልም እንይ እንዴ?”
“አሪፍ ፊልም አለሽ?”
“አዎ! ልክፈት?”
“ቆይ አንዴ ተሳልሜ ልምጣና ስመለስ እናያለን።”

ጧፏን ይዛ ስትወጣ አያትና ሳቄን ታመጣዋለች። “የቱ ስለትሽ ሰምሮ ነው?” እላታለሁ በውስጤ። “እግዚአብሔር ተመስገን ብቻ ነው የሚባለው!” ትለኛለች ውስጤ ያለችው እ’ሷ። እ’ሷን ስከተል ነው ፊልም ማየትም የለመድኩት።


የተዋወቅነው በጣም ከረፈደ ነው። ድክድኬን አላየችም። ምን ምን እንደሆንኩ፣ ምን ምን እንደገጠመኝ አታውቅም። ከስሟ በቀር የማውቃት አውርተው በማይጠግቡት ውበቷ እና እነርሱም ለይተው በማያውቁት ግራ ገብ ታሪኳ ነበር። ዛሬም የተደበተ ፊቷ ውበቷን መሸሸግ አልሆነለትም።

ለአለባበሷ ግድ የሌላት፣ ለብሳም የማይሠምርላት ጠይም ቁመታም ናት። የምትደብቀው መከፋት የሰበሰበውን ማድያት በየቀኑ እያነሳ ጥይምናዋ ላይ ይለጥፋል። መሽቶ ሲነጋ አንድ አዲስ ነገሯ ይኼ እያደር የሚሰፋው ማድያት ብቻ ነው። ጸጉሯ ከወግ ያለፈ አይበጠርም፣ ሻሽ አስተሳሰር አትችልም፣ ጥርሷም ሸግኗል፣ ለሳቅ አይሆንም..... ከዚህ ሁሉ ኋላ ግን ዛሬም ታምራለች።

የውበትን ያህል አስማት የሚሠራ ማን አለ?

መከፋት ለነበር ሲሆን ከመኖር ያንድካል ፤ ጎድያለሁ። እሁን የምሆነው መሆን የለኝም። እመጠቀው ዘንድ የሚመጣ የለም። ሁሉነገሮ ሸሽቼ፣ ሸሽቼ እኔ ከእኔ ቀሪቻለሁ። እኔ ከእኔ ምኔ ሁኖ ያውቃል? ክውደደው ሲሉ እንደሰው ደውደዳል? (ያ መውደድ ሬሳ ነው።) ተስፋ ህልም ቦታህ ቦሽን እኔ ዬን በዛለ እግሬ እየንተትሁ እሄዳለሁ።

ይገርማል ሳይኖሩ መሞት ፣ እየሞቱ መኖር ፣ ማማሽ መሆን ፣ ማማሽ ደግሞ እኮመሆን ። ኦኮኔ እሳውቅም ባልኩበት ማግሥት ኦኮእኔ የማይጠፋኝ ነገና ። እኔ ከኔ ረሀባ እሳል እንደሆነኩ እንደይ ደግሞ እኔ ለኔ ወዲዬም ነገና... ያለ መቼት እንደይ ሆኛለሁ። በእርግጥ መቼት ኧነ ያደረጋል? ከመሞት ያንድላል? ባመኖር ይሞላል? አይ አድይኮም ... ግነ የመናልባት የመናልባት ትዝታ ይሆናል።



ተቀዳዷል።

አንዳንዶቹን "ባላነብብኳቸው፣ ምን ነበር በቀረብኝ!?" እላለሁ። አንዱ ላይ ያነበብኩት ፍቅሯ ሌላው ላይ ጥላቻ ሆኖ አገኘዋለሁ። ደማምሬ ደማምሬ የሠራኋት እ'ሷ መልሳ ትፈርሳለች፣ ሌላ አዲስ ጥያቄን ይዛ ትመጣለች። ፀፀቷን አይቼ "ይቅር ብዬሻለሁ!" ባልኳት ልክ ለማላውቀው በደሌ ደግሞ "ይቅር በይኝ!" ማለት ያምረኛል። ሳላገኛት በፊት እንደ'ርሷ የናፈቅሁት ሰው ምድር ላይ አልነበረም። ከእ'ርሷ ጋ ለመኖር ያደግሁበትን ሀገር ለቅቄ ስመጣ ተወዳጅ ልጅ ለመሆን፣ "ተይ!" ስባል የኖርኩትን ሁሉ እርግፍ አድርጌ ጥዬ ነበር። አብዝቼ ስለማን እንደዚህ ተጨነቅሁ? የምትወደኝ ልሆን እሷን እስክመስል ድረስ ያልተውኩት እኔነት ምንስ ቀርቶኝ ነበር? ግን ይኼን ሁሉ መሆን ለእርሷ አላበቃኝም ነበር፣ ስላጎደልኩት አላውቅም። "እኔን ከራሷ አርቃ ለመጣል ከሄደችው ርቀት ሩብ ያህሉን ብቻ ስለመኖር ብናልምበት ቤተሰባችንን የሚመስል ምንስ ይኖር ነበር?" እላለሁ። የመተው መንገድ መች ነው ከመውደድ የበረታው? ለመሆን ባልሞከሩት ልክ ላለመሆን ይለፋል? እርሷ ግን ታደርገዋለች።

አያቴ ስለእናቴም ሆነ ስለአባቴ "ማነው?" አይነት ጥያቄ ሳነሳ የመልዓከ ሞት ፊቷን ፊቴ ላይ እየዘረጋች ሰታባርረኝ ነው ያደግሁት። ስለ እናቴም የማወቃት ትንሽ እውቀት ከመንደር ወሬ የተለቃቀመች ነበረች።

ብዙ ብዙ ይሉ ነበር። አሁን የገባኝ አንድ ነገር አብረው እንደኖሩ እንጂ እንደማይተዋወቁ ነው። አብሮ ቡና መጠጣት ልብ ለልብ መግባባት የሚመስላቸው የዋኃን ናቸው። በአንድ ጣራ ስር እየኖሩ ሩቅ ለሩቅ መሆን እንደሚቻል ኖረው አላዩትም። ብቻ ግን ከልጅነት እስከዛሬ አብሮኝ ያደገ ግራ መጋባት አለኝ። አምርሬ የጠየቅኋት ቀን አለባብሳ የምታልፍብኝ ግራ መጋባት፣ እንዳልሰማ ሆና በነጠላዋ ሸፍና ወስዳ፣ አምላኳ ደጅ ወስዳ ደፋፍታው የምትመጣው ግራ መጋባት። 'በልጅ ነሽ'፣ 'በስታድጊ ይደርሳል'፣ 'በጊዜው አሁን አይደለም!' ተጠቅልሎ የኖረ ግራ መጋባት።

ከቁንጥር ንግግር መሐል
"ይኼን መፅሐፍ ጨረስሽው እንዴ?"
"አዎ ግን ብዙም ደስ አይልም።"
"ያኛውን መጽሐፉን ወደሽው ነበር አ? ሃይላይት ያደረግሽበትን እያየሁ ነበር።"
"አዎ! ሙሉ አቅሙን እዛ' ላይ ነው ጨርሶ የመጣው፣ አልቆበታል በቃ!"

የወደደችውን እንደተከተልኩ ሁሉ የጠላችውንም እከተላለሁ፣ ምን እንደምትጠላ ደግሞ ለማወቅ።

መልስ እንዲሰጥያቄ ቀላል ይመስለታል። ብትሰማው ስሙቷ እነደ ቀድሞ የሚቀሰቅስ፤ ግራ መጋባቷ ቀሪዓ ለላም እግኝታ የምትሮር ይመስላታል። ሄሄሄ... ምስኪን ናት። ያልኳትን አምናለች። ሪዜው ደርሶ የምነግራትን እውነቱ ትሰብቃለች።

ሰያቄዋን ሸለት ከእርሳ የዞርኩት ሌት ለፍቅርም ስጀግን ቀረ። ቀን ስቅሰር ብኖርም፤ ብነግራት የሚያነከስ አላል እነጂ የሚቀሰባ ንዶሎ እነደማይኖራት አውቃለሁና ከአል ሸበጠ የሚጸልልኝ አንድ እውነት ያለኝም። ከመሸርፍ ሌላ ትርፍ የለውም። አንዳንዱ ሊጠይቅ ለኖር አመለሱ ይሻላል። አንዳንድ አለመውቅ ይድናል። አንዳንድ አለመውቅ ያድሁል።

ሸሁን መሄጀዬ ይሪኳል? አሁን መፀስናበቻዬ ነው። ከሁስ ሌጋ መሐመ ባጂ እነደመሆን ልብ የሚስነሳቅ ምን አለ? ወደምትልበት የሳጂ ዝምድና ንዬን አስጠጋለሁ። እንዲምታነሲው አውቃለሁ፤ እርምሽን አውጪ እነግጂህ። ለሕይወት ዘመን ሰያቄዬ መልስሽ ሌላ ሰያቄ ሆኗል። ለ'ተለሰሩ!' ስፈጠረን ÷ ሌላ ምን እንሳለን? ከዛሀ በቀር ቦቀር አቅም የለኝም።

የስንብቴን ግን አንድ ያነሰገኩትን፣ እኔ መጀፍ ያነበረብኝን ግጥም አስቀምጬልሽ እሄዳለሁ። ከእርሱ ሰቀር ጉሣዜ የለችም። ያሳደገሽ ቦኔ ፍቅር እይደለም። ከክብሩት ሰቀር ብገፎ ትርፍ ኖሮኝ አያውቅም። መለፋትሽ ባይቀርም በዙህ አትክፊ። እኔ ወደ እቃሳኪ ደጅ ነው የምመለጋው? ወደገጻም። ሮኔንሶ ጨምሮ ብንፎ ይሳለሽ!

ይቅርታ

ካሳለፍኩት ዕድሜ ÷ ከሰው ተነሳዬ
ካገኘኝኩት ግሶም ÷ ቦትም ቦትም ጥሮ
ይቅርታ

ያኮ ያመንም ሰበጣ ÷ ላፈሰስሁት ዕንባ
ጨለማን ፈርቼ ÷ ላባከንኩት ላም
ይቅርታ

ከሰው ተነሳዬ ÷ ስለመከፋቴ
ከሞት አስቀደመ ÷ ስለመኮርፋቴ
ይቅርታ

ክርስትስን ሳልሁን ÷ ስለቀለሁ ንልንታ
ለው ፊት ስለነገሁ ÷ ሁኜ እርግጎ ታ
ይቅርታ

ባእግሬ ስለመታሁ ÷ የመንገድ እንቅፋት
ሰሩሱ ስላሳበብሁ ÷ የገሣ እግሬን ጥፋት
አላካቃናሁት ÷ የልቤን እጥፋት
አሁዴ አለሻትሁ ÷ ቦሳነፃዩን ሥፋት
ይቅርታ

ብሩህ ቀን ፍለጋ ÷ አቀን ስለሸሸሁ
ቆሎ ስለደከምሁ ÷ ቆ;ሎ ስለመሸሁ
~ ንድ ቾለስ!~ ብቡ ÷ ነፍሴን ስለቀሸሁ
ይቅርታ

የቅጽበት እቅፉት ÷ አለሁኝ ብር ቄ
ለሰው አለቻርኩኝ ÷ ከራሴ ሰር ቄ
ይቅርታ

ከፊዳይቱጥሩን ስዎች ÷ ከጣታቸው ፈለግ
መውደድን ወደጅኩን ፣ ፊለግኩኝ መፈለግ
ይቅርታ

ስለሩቴት ሰውሽዬ ÷ ቦንዳ እየስቅስቄ
አላሳለፍኩት ቀን ÷ ቦውሽቴን ስቄ
ይቅርታ

ብመለሰሪያዬ ወቅት ÷ አለመለሰርሬ
ብዓሸሰሪደ ቀን ÷ ስለመሸበሬ
ጠለች እንደ ስንዴ ÷ ዛሬም አለመርኝ
ወኔ አለከዳኝ ÷ አቅም ስላጠረኝ

ይቅርታ

ዱጤ ሳልሰነገዝር ÷ ወይም ሳልደበቅብ
ለቄ ስላለፍኩት ÷ ነቀፋና ክደብ
ይቅርታ

ችጋር አለለመድሁ ÷ አለደለኝ እጦት
አለቆmcኩት ጣር ÷ እገደሁን ቅጎቦት
ይቅርታ

ለው እየፈለኩኝ ÷ ለለገፉሁት ስው
ፊቤ ለይቅርታ ÷ አቅም ስላነሳው
ቦገ ስላአቀረሁት ÷ ቦዘወዩን ጀሎቷ
ፊጅ እታለኝ ÷ አላልሆነንኩ እናቷ
ይቅርታ

ሳልቦርቅ ሳልጨፍር ÷ ስላለፊኝ ዕድሜዬ
እናት ለለሆነንኩኝ ÷ ለምነም ቀደሚ
ይቅርታ

" እረ አልሞትክም!" ሊለኝ

ፊቤን ስላመነኩት ÷ ሳምኜ ትርታ
እኔ እኔነ ስለሆነኩ ÷ እኔ ሁዩ ይቅርታ!

እ'ርሷ አምላኳን ስትጠጋ እኔ አምላኬን አጣሁ፣ ከእርሷ አብ'ሮ ቤተሰብ የነጠቀኝ አምላክ ምን ይሆነኝ ብዬ?

የስንብት እና የይቅር ብጣሽ ወረቀት ተስፋን የሚከድን፣ ጥያቄን የሚያስረሳ የመሰላት እርሷ ተነስታ ወደ መሸሻ ጌታዋ ሄደች። ከዚያ ወዲያ ይገፉ የማይመስልን የጊዜ ክምርን ከነጥያቄዬ ገፍቻለሁ። ከሚሮጡት ኋላ እንደው ላ'መል ያህል ዝም ብዬ አዝግሜያለሁ።

1. የዮናታን ጌታቸው ግጥም

ወዴት እንደሁ በማላውቀው መንገድ - ስለመዳረሻ ሳይገደኝ ተጉዣለሁ። በስንኩል ልብ መራመድ የት እንደሚያደርስም ሳላውቅ ወደ ነገ ተሻግሬያለሁ። እንደባዳ እንደ ሩቅ ሀገር ሰው በሰው መሐል ሆኜ እንደ መቅረት ያለ መሄድን ለብቻዬ ሄጃለሁ። በመሮጡ መሐል ሁሉም ታልሎ መቅረቱን ያወቀልኝ የለም።


አሁን ብዙ ዘመንን በላዬ ላይ ከደፋሁ ኋላ፣ ለልቤ እኔው እለዋለሁ "እንግዲህ አብቅቷል፣ ምንም አንጠብቅም።" እውነቱ ግን እንደዚያ አይሆንም ፣ አንጠብቅም ብንልም ከጣለን ቀን በአንዱ ጥብቅ ጠባቂ ሆነን እንገኛለን... እንደውም እንደውም "አልፈልግም ከእንግዲህ!" በማለት ውስጥ የተደበቀ መፈለግን ያህል ሽሽግ ተስፋ፣ ብኩን ተስፋ የለም ።

... ይዋሽ ይሆናል እንጂ በበቃኝ የተሸፋፈነ ብዙ ያልበቃ ጉጉት አለ። "አልጓጓም!"፣ "ይበቃል!"፣ "አልናፍቅም!" ብንልም ... ናፍቆቶቹ ከከሸፉበት ሰው በላይ ግን ናፋቂ ልብ የትም የለም። አለ አይደል በአዲስ ናፍቆት አምናና ካቻምና፣ ከጊዜያት በፊት የሞተ ልብን ማንቃት ድል አለው - ትርፍ ባይኖረው ምንም፣ መሻትን አግኝቶ ነፍስን እንደማራስ ባይሆንም፣ "እሰይ! ናፍቄ አገኘሁ፣ ጠብቄ አቀፍኩ!" እንደማለት ባይሆንም፣ ከበረዶ የገገረ ልብን እንደማሞቅ መልሶ ተስፋ ማድረግን፣ መናፈቅ መቻልን እንደማየት ምን ፍስሃ ሊኖር? እንግዲህ እንዲህ ነው አንዳንዴ የሰበረውንም ነገር መልሶ ይሻል ሰው ።

ትርፌ አንድ ነው ፣ እናት መሆንን የተማርኩት እንደዚህ እንደዚህ እሷን ስከተል ነው።




ድግስ



በታዋቂው ኢትዮጵያዊ ቤዚስት ሄኖክ ተመስገን የሚዘጋጀው Henock's Practice Room ላይ ዝነኛው ሳክስፎኒስት ጋሽ ግርማ ወልደ ሚካኤል ተጋብዘው የሠሩት Live Album የዚህ ወር የመዲና መጽሔት የሙዚቃ አልበም ግብዣ ነው። Henock's Practice Room ሙዚቀኞች ተጋብዘው የራሳቸውንም ሆነ የሌሎች ታዋቂ ሙዚቀኞችን ሥራ Live የሚጫወቱበት Platform ነው። በዩትዩብ፣ በፌስቡክ፣ በቲክቶክ እና በሌሎች የማኅበራዊ ሚዲያ አማራጮች መከታተል ይችላሉ። አዘጋጁ ሄኖክ ተመስገን በዓለም የታወቀ የጃዝ ሙዚቀኛ ነው። ከጋሽ ግርማ ጋር ሲገጥሙ ደግሞ የተፈጠረውን ውብ ነገር በዚህ አጭር አልበም በአምስት ሙዚቃዎች ቀንብበው አቅርበውልናል። እንደዚህ ያሉ Live አልበሞች እንዲበዙ ምኞታችን ነው። ተጋበዙልን!







የዚህ ወር የመዲና ዲጂታል መጽሔት የመጽሐፍ ግብዣ የቴዎድሮስ ዕንባ የተሰኘው የብርሃኑ ዘርይሁን መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ በ1958 ዓ.ም በብርሃንና ሰላም ማተምያ ቤት የታተመ ሲሆን መነሻውን ከዘመነ መሳፍንት በኋላ ባለችው ጎንደር ላይ አድርጎ የአጼ ቴዎድሮስን አነሳስና አወዳደቅ፣ ገብርዬን ዋና ገጸ ባሕርይ አድርጎ በ140 ገጾች ቀንብቦ ያሳየናል። ይህ ታሪካዊ ልቦለድ በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ቀደምት ከሚባሉት ውስጥ ከመመደቡም በተጨማሪ በኋላ ለተጻፉት ለነ'የታንጉት ምስጢር'ም ሆነ ለሌሎቹ ታሪካዊ ልቦለዶች ፋና ወጊ የሆነ ሥራ ነው። ብርሃኑ ዘርይሁን ጎንደርን እንደ ዋና ገጸ ባሕርይ ኩሎ ስሏታል። ገብርዬ፣ ዓለሜ፣ ጋረድና አክሊሉ በብርሃኑ ብዕር አካል ገዝተው ለጎንደር ነፍስ፣ በጎንደር አንጻር ለኢትዮጵያ ሕልውና እንዲሁም ለግላዊ ጥቅም ይፋለማሉ። ታነቢት ዘንድ ግብዣችን ነው።

የፊልም ግብዣ

በ83ኛው የ-Academy Awards ላይ በምርጥ የውጪ ቋንቋ የተሠሩ ፊልሞች ዘርፍ ውስጥ በእጩነት የቀረበው የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፊልም የመዲና መጽሔት የዚህ ወር ግብዣ ነው።

ፊልሙ ሁለት ተከታታይ የኦሎምፒክ ወርቅ ሜዳሊያዎችን በማምጣት የሀገር አርማ በሆነው በአትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ ሕይወት ላይ ተመሥርቶ የተሠራ ነው። አትሌቱ - The Athleteን ተጋበዙልን!





ምስል፡ በጨዋታችን ወቅት ዶክተር ፀደይ የተጠቀመችው ወረቀት

ከገጽ 22 የዞረ...

መዲና- በጣም ጥሩ። አሁን ደግሞ ስለ መካነ-ካልእ እናውራ። እዚህ መልክአ ዓለማየሁ ላይ በጻፍሽው ጽሑፍ ውስጥ የሚሼል ፉኮን Heterotopia የተረጎምሽበት ቃል ነው፤ መካነ-ካልእ። በመጀመርያ ስለ ቃሉ እናውራ። ቃሉ የተፈጠረበት መንገድ ትክክል መስሎ አልተሰማኝም። መካን የሚለውን ቃል የ‹-ኧ› ድምጽ ስንጨምርበት እና ‹መካነ-› ስናደርገው ‹የ-› የሚል ነገር ይጨምራል። ስለዚህ ‹ሌላ ቦታ› ወይም ‹ልዩ ቦታ› መባል የነበረበት ‹የሌላ ቦታ› ወይ ‹የልዩ ቦታ› አይሆንም?

ፀደይ- እ...ሺ! አሁን ለምሳሌ በትግርኛ የጥርስ ሐኪም ለማለት ‹ሐኪም ስኒ› ብለህ ነው የምትጽፈው። ግዕዝ እና ትግረኛ ደግሞ ይወራረሳሉ። ‹-ኧ› የምትለው የግድ ‹የ-›ን አታስከትልም። ለምሳሌ ሐኪም ቤት ነው እንጂ የሐኪም ቤት አትልም። ለምሳሌ ምግብ ቤት እንጂ የምግብ ቤት አትልም። በደንብ አስቤበት ነው ያመጣሁት።

መዲና- እኔ ደግሞ የተሻለ ብናናብበው እና አማርኛ ብናደርገው የሚል ሃሳብ አለኝ። አሁን አሁን ብዙዎቹ ከግዕዝ ተስበው የሚኮየኑ ቃላት አገልግሎት ላይ የማይውሉ ሆነው የሚቀሩት ወደአማርኛ ስለማናቀርባቸው ነው። ማናበብ አለብን። አስፈላጊ ከሆነ ሌላ አዲስ ቃልም ቢሆን መፍጠር እንችላለን።

ፀደይ- እንደዚያማ አይሠራም። ለምሳሌ ይኼ Heterotopia የሚለውን እኔ ከዛሬ ጀምሮ ዝም ብዬ ቃል ፈጥሬ 'እምቡጡሉ' ብዬዋለሁ ብል.... [ሳቅ]... አንተ ልትቀበለኝ

ትችላለህ። አካዳሚው ላይ ግን ከየት አመጣሽው እባላለሁ።

መዲና- ‘እምቡጡሉ’ አሪፍ ቃል ነው። ሃሃሃ... እንደውም ከአሁን በኋላ ‘እምቡጡሉ’ ዝም ብሎ ከመሬት ተነስቶ ለሚፈጠር ቃል መጠርያ ይሆናል። ሃሃሃ... ግን አሁን እኔ ያልኩት እንደ ‘እምቡጡሉ’ ከባዶ አይደለም። ለምሳሌ ካልእ መካን የሚለውን ‘ካልመካን’ ብንለው፤ አመክንዮ ይገዛዋል። አማርኛ በባሕርዩ ያናብባል። ድምጾች ይውጣል። ‘እ’ በዚህ ሂደት ትዋጣለች። ብዙ የአማርኛ ቃላት በዘመን ሂደት የተፈጠሩት እንዲህ ባለ መንገድ ከተናበቡ የግዕዝ ቃላት ነው።

ፀደይ- አዎ። ግን ምንድነው መሠለህ? እኔ አሁን ከአንተ የተለየ አመለካከት ነው ያለኝ። ምንድነው መሠለህ? ግዕዝ አሁን ላይ Functional ስላልሆነ፤ እኛ ስለማንጠቀምበት ምናምን ከባሕላችን እየወጣ ነው። በ’ርግጥ ከወጣ ረዥም ጊዜ ሆኖታል። ምዕራባውያን ጋ ግን ላቲን ቢወጣም እስካሁን ይጠቀሙበታል። ምክንያቱም የአንድ ቋንቋ ፍልስፍና የሚገኘው ከEtymologyው ነው። እኛ እኮ... እንኳን የቃሉን ምንጭ ልናጣራ ቀርቶ መዝገበ ቃላት እንኳ አንጠቀምም። አማርኛ Dictionary ማገላበጥ እንዳለብን ራሱ Recognise አናደርግም አሁን። ምዕራባውያን አንዱ ትልቁ ሃብታቸው ምንድነው መሰለህ፤ They Care! ለምሳሌ ‘Knife’ ሲጻፍ ‘K’ አለው አይደለ? ሲነበብ ግን የለውም። የሆነ ዘመን ላይ ግን ይነበብ ነበር። ዘመናዊው እንግሊዘኛ ላይ እንኳ በእነሼክስፒር ዘመን ይነበብ ነበር መሰለኝ፤ በተወሰነ ደረጃ። በኋላ የ‘K’ ድምጽ ከተዋጠ እና መነበብ ከተተወ በኋላ አራግፈው አልጣሉትም። ተሸክመውት ነው የሄዱት። ሌሎችንም ቃላት መመልከት ትችላለህ፤ እንደ Psychology ያሉትን። በእነርሱ ቋንቋ ‘C’ንም፤ ‘K’ንም እንደ ‘ክ’ ብለን እናነባቸዋለን፤ አይደለ? በእርግጥ ይኼ ‘C’ እንደ ‘ች’ም እንደ ‘ክ’ም ይነበባል። ሁለቱንም Preserve አድርገዋል። አንዱን ከግሪክ፤ አንዱን ከላቲን ነው የወረሱት። አየህ፤ አይጥሉም። ላይጠቀሙበት ይችላሉ። ግን አይጥሉም። ተጠንቅቀው መዝገበ ቃላት ያዘጋጃሉ። እኛ ጋ ግን ምን ሆነ መሰለህ? አንጠነቀቅም። አሁን ለምሳሌ አይተህ እንደሆነ ብዙ ጊዜ ‘ው’ እና ‘ዉ’ አንለይም። ... እ... ‘ሁ’ መጠቀም ሲኖርብን ‘ው’ እንላለን፤ [በ‘ህ’ ፈንታ] ‘ክ’ን ምናምን እንጠቀማለን። እንደቋንቋ ለውጥ ልንቀበለው እንችላለን። ግን ችግሩ ምንድነው መሰለህ? የአንድን ቋንቋ Etymology፤ ከየት መጣውን በጠቅላላ ያጠፋዋል። ድምጹ እንዴት እየተቀየረ እንደመጣ እንኳን ማብራራት ካልቻልን ሥሩ ተፋልሶ ነው የሚቀረው። ያ ከሆነ ደግሞ በቋንቋ ውስጥ የሚተላለፍ መአት ፍልስፍና አለ። ያ ሁሉ ይጠፋል። ለምሳሌ በተለምዶ ሞክሼ የምንላቸው ፊደላት ሞክሼ አይደሉም። የተለያየ ድምጽ ነው ያላቸው። ካለማወቅ የተነሳ አንድ አይነት ሆኑ። አሁን ለምሳሌ በትግርኛ የየራሳቸው ድምጽ አላቸው። እኔ ትግርኛ እሰማለሁ፤ እዚያ መቀሌ ስለነበር የማስተምረው። እና ሆነ ብዬ ነው የተማርኩት። እየተንተባተብኩ፤ ‘ትግርኛሽ የሕጻን ይመስላል።’ [ለማበረታታት] እያሉኝ ነው የለመድኩት። መዝገበ ቃላት ገዝቼ ምናምን ምናምን! Consciously ማለት ነው። አሁን ለምሳሌ እዚያ... ሐመሩ ሐ እና ሀሌታው ሀ አንድ አይነት አይደለም ንባባቸው። ‘አ’ እና ‘ዐ’ም እንዲሁ። ‘ሠ’ እና ‘ሰ’ በዐረብኛ ይለያያሉ። አንድ የመኒ አግኝቼ ጠይቄያለሁ...

መዲና- ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌም ከአማርኛ በቀር ሌሎች የሴም ቋንቋዎች እነዚህን ድምጾች ጠብቀዋል ይላሉ።

ፀደይ- አዎ። አማርኛው ለምን መሰለህ? ከኩሽቲክ ጋር ድብልቅ ስለሆነም ነው። ሴሜቲክ ብቻ አይደለም። በአጻጻፍ ብቻ ይዘነው ድምጹ ግን ጠፍቶናል። አንድ ጊዜ ክርክር ነበር። ‘ሞክሼ ፊደላት ይቀነሱ፤ አማርኛ እነዚህን መጠቀም የለበትም። Ethiopic የሚባል ይዘጋጅና እዚያ ውስጥ ይግቡ። ከአማርኛ ግን ይውጡ።’ ምናምን የሚል ክርክር ነበር። ቆይቷል ይኼ ክርክር በነገራችን ላይ። ረዥም ታሪክ ያለው ክርክር ነው። እኔ አልስማማም።

መውጣት የለበትም ነው የምለው። ለምን? እነዚህን አወጣን ማለት እስከዛሬ የተጻፈ መጽሐፍ ማንበብ አንችልም።

መዲና- ግን እኮ ቋንቋ በባሕርዩ እንደዚያ ነው። አይደለም? በጊዜ ሂደት ብዙ ነገሩ እየተቀየረ ሌላ ቋንቋ ነው የሚሆነው።

ፀደይ- አይሆንም። ቅድም ያልኩህ ነገር አለ። Etymology የሚያጠኑ ሰዎች አሉ። አየህ፣ ፈረንጅ ሲጽፍ Conscious ነው። ሲጽፍ እንኳ ቢሳሳት ማሽኑ ኤዲት ያደርገዋል። እኛ ግን በደንብ ስላልያዝነው እየጠፋ ሄደ። እኔ እንግዲህ ሌላው ይቅር፣ የአለቃ ኪዳነ ወልድ፣ የከሳቴ ብርሃን እና የደስታ ተክለ ወልድ... ልፋታቸው ብቻ ያሳዝነኛል። ሠላሳ ምናምን ዓመት፣ አስራ አራት ዓመት... በጣም ነው የተለፋባቸው በነገራችን ላይ።

መዲና- ደግሞ በሆነ Institution አይደለም። በግላቸው ነው የሠሩት።

ፀደይ- አዎ፣ በግላቸው! በነገራችን ላይ የምዕራቡ ዓለም ላይም በግለሰቦች ነው የተጀመረው። የሆነ ፊልም አይቻለሁ፣ ሚል ጊብሰን የሚሠራበት።[5] እውነተኛ ታሪክ ይሁን አይሁን አጣራለሁ ብዬ ረሳሁት። ብቻ በሚገርም ሁኔታ በግለሰቦች ጥረት ነው የተጀመረው። በኋላ ግን እንግሊዞች መዝገበ ቃላቱን ሲያዘጋጁ አሜሪካውያን ደግሞ የተለየን ነን ለማለት Webster's ብለው የራሳቸውን አዘጋጁ። ያው ቅኝ ተገዝተዋል ምናምን ምናምን። ብዙ ታሪክ አለው። ብቻ መዝገበ ቃላት በጣም በጣም ትልቅ ዋጋ ያለው ነገር ነው። ቋንቋን ከነፍልስፍናው መጠበቂያ ነው። አንድ ፀሐፊ ነኝ የሚል ሰው፣ ድርሰት ውስጥም ያለ ይሁን፣ Academician ነኝ የሚልም ሰው መዝገበ ቃላት መጠቀም አለበት። የቃላት ሃብት ነው አንዱ የደራሲያን ሃብት። ለምሳሌ ግጥምን እንደፈለግኩ ማድረግ የምችለው የቃላት ሃብት ሲኖረኝ ነው። Diction የሚባል ነገር አለ፣ ቃላት መምረጥ መቻል። ምክንያቱም ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ቃላት ራሱ አንድ አይነት አይደሉም። የሆነ ትንሽዬ ልዩነት ይኖራቸዋል። ለዚያ Sensitive መሆን መቻል አለብን። ፈረንጆቹ ያደረጉትን ተመልከት። እንግሊዘኛ Amazingly ከየትኛውም ቋንቋ ጎትቶ ያስገባል።

መዲና- ከግማሽ በላይ Vocabularyው ከሌሎች ቋንቋዎች የተወረሰ ነው ይባላል።

ፀደይ- አዎ። አማርኛም ይኼ ባሕል አለው በነገራችን ላይ። ምክንያቱም ሃብት ነው ቋንቋ። ዓለምህን የምታይበት ነው። በነገራችን ላይ እንደ ሰው ልጅ ያለን ብቸኛ Tool ቋንቋ ብቻ ነው። ሌላ ምን አለን? አእምሮ አለ በርግጥ። እርሱም ውስጥ ግን ቋንቋ እና Image ነው የምጠቀመው። Imageን ለአንተ ላሳይህ አልችልም። የሆነ ሌላ Telepathic ችሎታ ከሌለህ በቀር። ዓለምን የምንገነዘበው እና እርስ በእርስ የምንግባባው በቋንቋ ነው። አምላክ ዓለምን ሲፈጥር 'አለ'፣ 'ተናገረ!' ነው የሚለው። ቃል ነው የወጣው። ምን አይነት ቃል እንደወጣ አላውቅም። ግን ይኼ ቋንቋ የምንለው ነገር በጣጣጣ...ም ትልቅ ነገር ነው። በቃ፣ እኔ ለዚያ ነው በጣም Sensitive የምሆነው። በተቻለኝ አቅም። አሁንም በቂ ጥንቃቄ አደርጋለሁ አልልም። በተቻለ መጠን ግን እሞክራለሁ። የሚሠራልኝ ነገር ካለ ወደ አማርኛ ጎትቼ አመጣለሁ። ፈረንጆቹም Scientfic ሥያሜ ሲፈልጉ ወደላቲን ወደግሪክ ነው የሄዱት።

---

5. The Professor and The Mad Man - እ.ኤ.አ በ2019 በእውነተኛ ታሪክ ላይ ተመሥርቶ የተሠራ ፊልም ሲሆን ፕሮፌሰር ጄምስ ሙሬይ የሚባሉትን እና በ1980ዎቹ መጨረሻ አካባቢ አሁን 'Oxford English Dictionary' የሚሰኘውን መዝገበ ቃላት ያዘጋጁትን ሰው ታሪክ ያሳያል። የመጀመርያውን የእንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት እ.ኤ.አ በ1755 ያዘጋጀው በኢትዮጵያውያን ዘንድ 'ራሴላስ : መስፍነ ኢትዮጵያ' በተሰኘ መጽሐፉ የሚታወቀው ሳሙኤል ጆንሰን እንደሆነ የሚታወቅ ነው።

መዲና- ቅድም ወዳነሳነው ሃሳብ እንመለስና አንድን ቃል ዝም ብለን Coin ማድረግ እንችላለን የሚል ሃሳብ ያመጣሁት... “እምቡጡሉ” እንዳልነው ማለት ነው... አማርኛ ቋንቋን ትምህርት ቤት ስንማር ትዝ ይልሽ ከሆነ ቋንቋ ዘፈቀዳዊ ነው ተብለናል። አልቀበለውም በእርግጥ፤ ግን ስንማር... ነገሮች እና መጠሪያቸው መካከል ምንም አይነት ግንኙነት የለም። ይኼ ጠረጴዛ ነው። ጠረጴዛ ቁሱ እና ጠረጴዛ ቃሉ መካከል ምንም ግንኙነት የለም። በእንግሊዘኛ Table ብንለውም ከእንግሊዘኛውም ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ምንም ግንኙነት ከሌላቸው ምን ችግር አለው እንደ “እምቡጡሉ” ዝም ተብሎ ከመሬት ተነስቶ ቢፈጠር? የሆነው ሆኖ የፈለገ Etymologyውን ብንከተል መጨረሻ ላይ እንዲህ ወዳለው ከአመክንዮ ውጪ የሆነ ፈጠራ ላይ መድረሳችን ይቀራል ወይ? ማለት ለመጀመርያ ጊዜ ለጠረጴዛ ስም ያወጣለትን ሰው አስቢው። አመክንዮ ላይኖረው ይችላል። ለሌሎቹስ ለምንድነው እንደዚያ የማይሠራው? የግድ ከሆነ ነገር መመዘዝ አለበት?

ፀደይ- አሁን ምንድነው መሰለህ? ይኼ Concept የማነው ነው ጥያቄው? ይኼንን “ቋንቋ Arbitrary ነው፤ በቁሱ እና በስሙ መሐል ተፈጥሯዊ የሆነ ግንኙነት የለም።” የሚለውን ሃሳብ Ferdinand de Saussure የሚባል ሰው ነው ያመጣው። Genius Linguist ነው ሰውዬው። በ1915 ዓ.ም [እ.አ.አ] የታተመ መጽሐፍ አለው። ከሞተ በኋላ ነው የታተመለት። እንደ ቴዎሪ ለተማሪዎቹ ይነግራቸው ነበር። በነገራችን ላይ Structuralism ፤ Post Structuralism፤ Post Modernism ምናምን ለሚሉት ሁሉ በጣም ትልቅ Tool አቀብሏል። አንደኛው መከራከሪያው ይኼ አሁን ያነሳነው የArbitrariness ጉዳይ ነው። ምክንያቱም እርሱ ብዙ ቋንቋዎች ይችላል። ብዙ ቋንቋዎች ስለሚችል በተለያየ ቋንቋ የሆነ ነገር የተለያየ ስም ነው ያለው። የትኛው ነው ግንኙነት ያለው? ... ምክንያቱም ከፕሌቶ ጀምሮ ሪፐብሊክን ብታነብ በቋንቋው እና በነገርየው መካከል ግንኙነት አለ ተብሎ ይታሰብ ነበር፤ ለረዥም ዘመን። ይኼንን ነው የገለበጠው አሁን። ሁለተኛ Etymology ውን፤ የጊዜው ጉዳይ ማየት የለብህም ይልሃል። ሦስተኛ... ሥነ ጽሑፍ ላይም በጣም ወሳኝ ነገር ያነሳው... Sign የሚባል ሃሳብ Identify አደረገ። Signifier እና Signified የሚባሉ ሁለት ነገሮችን ለየ። ከዚያ Signifier ወደSignified ይቀየራል፤ Signified የሆነውም ወደSignifier ይቀየራል። Signifier ቃሉን የምልበት ድምጻቱ ነው። Signified የሚሆነው ደግሞ ቁሱ/Object ወይም ሃሳቡ/Concept ይሆናል። ስለዚህ አንድ Sign የSignifier እና የSignified ድምር ነው። ሁሉም ነገር እንደዚሁ ነው። ለምሳሌ ብ-ር-ጭ-ቆ ስል ድምጻቱ [tone ለማለት ሳይኾን የድምጾቹ አጠራር] Signifier ነው። Signified የሚሆነው ደግሞ ይኼ ቁሱ ነው። [ጠረጴዛው ላይ ያለውን ብርጭቆ እያመላከትኩ።] ሥዕሉም ሊሆን ይችላል። በነገራችን ላይ! ይህች በጣም Important ግኝቱ ነበረች። ወደአማርኛ ሲያመጡት ትእምርት ብለውታል። ለዚያ ነው አየህ... Signifier የምንለው በየሃገሩ ሊለያይ ይችላል። Signified የሚሆነው ባይለያይም። So ቁሱ ሳይቀየር Signifierኡ ስለተቀያየረ ነው በነገርየው እና በሥያሜው መሐል ምንም ግንኙነት የለም የተባለው። አሁን ግን በሌላ አንጻር ሚቶሎጂውን ብትመለከተው... ያው ሚቶሎጂ ካልነው ማለቴ ነው፤ በእርግጥ እውነታም ሊሆን ይችላል... በባቢሎን ግንብ መፍረስ ጊዜ ከሆነ ቋንቋ የተደበላለቀው፥ እዚያ ጋ የተፈጠረ አንድ አይነትነት ቢኖርስ? ምክንያቱም የሰው ልጆች ባሕል በጣም ለረዥም ጊዜ አንድ አይነት እንደነበረ ይታመናል። ለዚህ አንዱ ማሳያ ምንድነው መሰለህ? ‘አባት’ እና ‘እናት’ የሚሉት ቃላት ናቸው። እነዚህ ቃላት በመላው ዓለም ተመሳሳይ ናቸው። አባ፤ ባባ፤ አባባ፤ ባቢ፤ አባቢ፤ ዳዳ፤ Dad፤ እማ፤ Mom፤ Mother፤ እም ወዘተ... እና ለምንድነው ይኽ Universal የሆነው? ሌላው ሊለያይ ይችላል። ግን በ‘ብ’፤ በ‘ፕ’... Bilabial ነው የሚሏቸው እነዚህን በነገራችን ላይ... በ‘ም’ ድምጽ የሚጠሩ የሆኑት? በቻይነኛ ራሱ አንድ አይነት ነው ብታይ ሲጻፍ። አወጣጡ ወይም Intonationኡ ብቻ ነው ትርጉም የሚሠጠው። አሉ፤ ሌሎች ቃላትም ተመሳሳይ የሆኑ። ግን እንደእነዚህ Unversal አይደሉም። So ይኼ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል። በነገራችን ላይ ይኼንን ጉዳይ አንድ ሺህ ምናምን ቋንቋ አጥንቶ Paper የሠራ

ሰውዬ አለ። ከዚያ እነ Chomsky ጋ ስትመጣ... አስገራሚ ነገር ይናገራል [Noam] Chomsky። አሁን ለምሳሌ... አምታችቼው ካልሆነ... Superstructure እና Deepstructure የሚላቸው ነገሮች አሉት። በSubstructure ከታሰበ ሁሉም ሰው የዓለም ፊደላት እና ድምጻት በሙሉ ውስጡ አሉ። ልዩነታችን ስናወጣው ነው ይላል። Linguistics ላይ ክርክር አለ በነገራችን ላይ። አሁን Chomsky የሚታወቀው በዚህ ሃሳቡ [Universal Grammar የሚለውን ሃሳቡን መቀየሩን ቢያሳውቅም] ነው። Potentially የዓለም ድምጾች በሙሉ ውስጣችን አሉ። ልዩነታችን ከምርጫ የሚመጣ ነው። ቃላቱን አውጥተን ስንጠቀምባቸው በየባሕሉ ልዩነት ፈጥረዋል። ለዚያ ነው የዓለም Phonetics ድርጅት Universally ማግባቢያ ብሎ ሁሉም ቋንቋዎች ውስጥ ያሉ ድምጾችን የሚወክሉ አርባ ምናምን ምልክቶችን አውጥቷል። [International Phonetics Alphabet ይባላል።] አሁን በአካዳሚክስ እንደዚያ ነው የሚጻፈው። ስለዚህ ያ መሠረቱ፣ ሁላችንም ውስጥ ያለው ነገር፣ Inbuilt የሆነ Programmingአችን ይኼ ቢሆንስ? ስናወጣው ቢለያይም የሁላችንም ስረ መሠረቱ አንድ አይነት ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ Ferdinard de Saussureን መሞገት የምፈልገው... ቋንቋዎችን በደንብ ማጥናት ብችል ማለት ነው... አንዱ የማነሳው ነጥብ ይኼንን ነው። አወጣጡ ከሆነ ልዩነቱ ትርጉሙ ግን አንድ አይነት ሊሆን ይችላል። እኛ አሁን አማርኛ ስንማር ስለArbitrariness... ከየት መጣው አይነገረንም። የፈርዲናንድ ስም አይነሳም። ከፕሌቶ ጀምሮ የነበረው ክርክርም አይታይም። በአጠቃላይ ግን እኛ ያልገባን... Inbuilt የሆነ ትስስር ይኖራል ነው። ምክንያቱም... ድምጾች እንደ ኢነርጂም ይጠናሉ በነገራችን ላይ። Frequencyአቸው ይጠናል። ኃይል አላቸው። አንዳንድ ጊዜ አትራገም ምናምን ይባላል አይደል? Effect ሊኖረው ይችላል። ምክንያቱም እኛም Electromagnetic Field አለን። Energy እንለቅቃለን። ምናልባት ከዚያ ጋር የሚጋጭ ነገር ሊኖረው ይችላል። አላውቅም።


መዲና- ሥዕሎች ላይ ራሱ ቀለማት ድምጽ ያወጣሉ የሚል ጥናት አለ። መጠኑ በDb ደረጃ በጣም ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል እንጂ ድምጽ ያወጣሉ።

ፀደይ- አዎ! Exactly! ጠዋት ከበደችን [ተክለአብ] የጠየቅኳት አንድም ይኼንን ነው እኮ። እርሷም ከFrequency ጋር አያይዛ መልሳልኛለች። ምክንያቱም ድምጽም ቀለምም Frequency ነው። ስለዚህ ወደቋንቋ ስንመጣ በእንግሊዘኛ 'Glass' ስልም፣ በአማርኛ 'ብርጭቆ' ስልም Energyው አንድ አይነት ቢሆንስ? አሁን እንደዚያ አይነት ጥናት አላየሁም በእርግጥ። ግን ቢሆንስ? ብዙ ጥያቄ ልታነሳ ትችላለህ። እና እኔ ዝም ብዬ አልቀበለውም ይኼንን ነገር። በጣም ነው የምወደው Ferdinand de Saussureን። በጣም Genius ሰው ነው። ቅድም እንዳልኩህ ከጥናቱ ለተማሪዎቹ የነገራቸው ነገር ነበረ። በ1915 ይመስለኛል፣ በድንገት ሕይወቱ አለፈ። በኋላ ከተማሪዎቹ ደብተር ተሰብስቦ ነው መጽሐፉ የወጣው እንጂ፣ እርሱ በሕይወት ኖሮ የደመደመው ነገር አይደለም። በእርግጥ የተናገሩት ነገር ትክክል ነው፣ ብዙ ነገር በሥርዓት Record ስለሚደረግ። ግን Final የሆነውን ነገር እርሱ አልሠራውም። እርሱ ጨርሻለሁ በሚልበት ደረጃ አይደለም የታተመው። ለዚያ ነው አየህ፣ ባለበት እኔ ዝም ብዬ አልውጠውም። የምሞግታቸው ብዙ ነገሮች አሉት።

መዲና- ለእኛ ባሕል የሚቀርበውም ይኼ ነው። አይመስልሽም? በኢትዮጵያዊ መረዳት በነገሮች እና በስሞቻቸው መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት አለ። ጥንቆላ ምናምን እንደዚያ ነው የሚሠራው እኮ። አይደለ? ለምሳሌ የክርስትና ስም ጠርተው ያስደግማሉ። ስለዚህ የክርስትና ስምሽ እና አንቺ መካከል የሆነ ግንኙነት አለ ማለት ነው። ወይ ደግሞ የእግዚአብሔርም፣ የሰይጣንም ጎበዝ ስሞች ምናምን ተብሎ ያንን ስም ስጠራ ከዚያ ኃይል ጋር የሆነ ግንኙነት እፈጥራለሁ ነው። ሌላ ሌላውን ብትተዪው ሁላ... ለምሳሌ ስቅ ሲልሽ

ሰው እያነሳኝ ነው ትያለሽ። ‘ዕድሜህ ረዥም ነው፤ ስናነሳህ መጣህ!’ ምናምን ስባል ‘ታውቆኝ ነበር፣’ ምናምን እላለሁ። ወዘተ...

ፀደይ- ልክ ነው። ልክ ነው።



መዲና- እ...ሺ! ሌላ ጥያቄ! ከአዲስ ቅኝት ጋር የነበረሽ ቆይታ ላይ ግጥምሽ ሲነበብ አዳመጥኩ። እና ግጥም ወይም ሌላ አይነት Creative Writing ውስጥ አለሽበት ወይ?

ፀደይ- በነገራችን ላይ Short Storyዎች በየመጽሔቱ የታተሙ አሉኝ። ቁም ነገር ላይ አሁን... ድ...ሮ የታተመ አለ። እኔ፤ ምን አይነት መሰለህ እወድ የነበረው [ለመጻፍ]? Science Fictionኦች እና Fantasy። ምናልባት የመጀመርያዋ ልሆን እችላለሁ፤ በ Sci-Fi ዘርፍ፤ ሴት።

መዲና- በወንድም ቢሆን ሁለት ሦስት ሰው ነው ያለው በነገራችን ላይ።

ፀደይ- አዎ። እና.... ቁም ነገር [መጽሔት] ላይ ወጥታ የነበረችው 'እጁ' የምትል Story ናት። እንዲሁ ድንገት የሚመጡ ሃሳቦች አሉ። የዚህች Story ሃሳብ ምን መሰለህ? ለምሳሌ የኢቮልሽን ቲዎሪ ልክ ከሆነ ይኼ ሁሉ ፍጥረት ከአንድ ፕሮቶዝዋ ነው አይደል የመጣው? እንሽላሊት አሁን ጭራዋ ሲቆረጥ ይበቅልላታል። ‘ለምንድነው የሰው ልጅ እጅ እግሩ ተቆርጦ የማይበቅልለት?’ የሚል ነው ጥያቄው። አንድ ደግሞ UFO ምናምን መጥቶ... የሚልም ነበር። ሌላ ፋና ላይም ድሮ የተነበበ አለ፤ ‘የዶክተሩ ማስታወሻ’ የሚል ፋንታሲ ነገር ነው። እና አሁንም ድረስ የሚገርመኝ... ይኼ መብቀል ምናምን ያልኩህን እኔ በጣም ድሮ ነው የጻፍኩት። ጃፓኖች ግን አሁን እየሠሩበት ነው የሚል አየሁኝ። [የተነቀለ ጥርስ መልሶ እንዲበቅል ለማድረግ እየተደረገ ያለ ምርምር]። ገርሞኛል ይኼ። Short Short Storiesም ብዙ አልነበሩም ያኔ። [ያዘጋጀችው የአጫጭር ልቦለዶች ስብስብ መኖሩን ነግራናለች]፤ በመሐል በመሐል ከትቻለሁ Short Short Stories። አተኩር የነበረው እንደዚያ አይነት ነገሮች ላይ ነው።

መዲና- አንዱ በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ የጎደለን ነገር በነገራችን ላይ ይኼ Sci-Fi ነው።

ለቴክኖሎጂውም መሪ ይሆናል። ቢወጡ ጥሩ ነው። ከዚያ ውጪ ደግም አንቺም፣ ቴዎድሮስ አጥላውም... ምናልባት ሌሎችም ሐያሲዎች የሒስ ሥራችሁን አካዳሚክ በሆነ መንገድ ሳይሆን ለሠፊው አንባቢ የማሳተም ሃሳብ የለም ወይ?

ፀደይ- አዎ! ሃሳቡ አለ። ግን ምንድነው? እኔ በጣም ሰነፍ ነኝ። የሆነ ነገር ጽፌ ወይም ሠርቼ ስጨርስ ጨረስኩ ነው። በቃ፣ Hustlingኡን እጠላዋለሁ። እኛ ሃገር ያለውን የማሳተም ጣጣ።

መዲና- በጣም ክፍት ቦታ አለ እኮ። ታውቂያለሽ? በተለይ በሂሱ ዘርፍ!

ፀደይ- አውቃለሁ። ግን ምንድነው መሰለህ? እንኳን መጽሐፍ ሆኖ ፌስቡኩ ላይ እንኳ የምትሞክረውን ብዙ ሰው አያነብልህም። ስትጽፍ ብዙ ቀናት ሊፈጅ ይችላል። ብዙ ኢነርጂ ነው የምታወጣው። ምናምን ምናምን... ያን ሁሉ Effort አውጥተህ ሰዎች ግድ የማይሰጣቸው ከሆነ ጥቅም የለውም። ምክንያቱም የምጽፈው ለሰው ነው። So ምንድነው የማደርገው? በቃ! ለራሴ አስቤ እተወዋለሁ። አሁን የዓለማየሁ ገላጋይ መጽሐፍ ሲጻፍ ጻፊ ምናምን ባይሉኝ አልጽፈውም። ካሰብኩት ቆይቷል። የሆነ ደረጃ መታሸት ይቀረዋል በነገራችን ላይ። የመልክአ ስብሐቱም ከአሌክስ ጋር እንዲሁ እናወራ ስለነበረ 'ለምን አትጽፈውም። አሁን መጽሐፍ ላወጣ ስለሆነ...' ምናምን በሚል ነው የታተመው። እንደዚህ አይነት ነገር ሲኖር ነው የምጽፈው። እንጂ የእኛ ሃገር የጎትመት ነገር ጥሩ አይደለም። 120 ሚልየን ሕዝብ ይዘህ ሦስት ሺህ ኮፒ ለመሸጥ መከራ ነው።

መዲና- ግን ባይታተምም፣ እየጻፍሽ ብታስቀምጪ ለወደፊት ሊጠቅም ይችላል። የመጨረሻ አንድ ጥያቄ... ከፖስትሞደርኒዝም ጋር የተያያዘ አለኝ። ፖስትሞደርኒዝም ደራሲዎቻችን ላይ የተጫነ ቴዎሪ ነው ብዬ አስባለሁ አንዳንዴ። ድሮ ድሮ ሸገር ሼልፍ ላይ ትዝ ይልሽ ከሆነ አዳምም ሲጠየቅ እንደዚያ ነበር ያለው።[6] ስለዚህ ነጥቡ ምንድነው? አንደኛ Classification የሒስ ጉዳይ ስለሆነ ፖስትሞደርኒስት ስለመሆን ጉዳይ ደራሲዎቹ ግድ ሊሰጣቸው ይገባል ወይ? ሁለተኛ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ ዕድሜው አጭር ስለሆነ፣ Modernismን በቅጡ ሳያጣጥም በቀጥታ ከብሉዩ ሥልት እንዴት ወደፖስትሞደርኒዝም ሊደርስ ይችላል? ሦስተኛ የፖስትሞደርኒዝም የብቻው ያልሆኑ ቴክኒኮችን ብቻ አይተን ድርሰቶችን ፖስትሞደርኒስት ናቸው ማለት እንችላለን ወይ? ማለት ፖስትሞደርኒስት የሚያሰኘው ፍልስፍናው ነው እንጂ ቴክኒኩ አይደለም አይደለ? በሴራ እንኳን ብንለየው የሞደርኒስት ግጭት ከእግዜር አለመኖር ጋር ወይም ከራስ ጋር የሚደረግ ነው። በፖስትሞደርኒዝም ግን ግጭት ከሪያሊቲ እና ከደራሲ ጋር ነበር መሆን የነበረበት። አብዛኛዎቹ የአማርኛ ልቦለዶች አሁንም የሞደርኒዝምን እና ክላሲካሉን ግጭት ተጠቅመው ነው ታሪካቸውን የሚያስኬዱት። ቴክኒኩም ቢሆን... ለምሳሌ Intertextuality... እኔ በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ውስጥ በትክክል የተሠራበትን ቦታ አላየሁም። አሪፉ ምሳሌ የጄምስ ጆይስ Ulysses ነው አይደለ? Ulysses ራሱ Modernist የሚባል ነው። በአጠቃላይ 'ከዚህ ሁሉ አንጻር የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ላይ ፖስትሞደርኒዝም እንዲህ ገንኖ የወጣው በምን አግባብ ነው?' ነው ጥያቄው።

ፀደይ- በነገራችን ላይ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ላይ ፖስትሞደርኒዝምን እንደመመልከቻ በመጠቀም የእኔ ጽሑፍ የመጀመርያው ነበር። [19]99 ላይ የማስተርሱን የመመረቂያ ጽሑፍ ሚውዚክ ሜይደይ አቅርቤው ነበር። እና ያኔ ብዙ ሰው አልተረዳውም። እኔ ራሴ ፖስትሞደርኒዝም ላይ የማልደግፋቸው ነገሮች አሉ። ወደ ናይሊዝም [Nihilism] ይወስዳል

---

6. የሸገር ሼልፉን ዝግጅት ለማዳመጥ የሚከተለውን ማስፈንጠሪያ (Link) ይጠቀሙ።
https://youtu.be/sQ10hSaEL90?si=pSf-efuFtzeZZHUc

ምናምን የሚል ሥጋቶች አሉበት። ብዙ ክርክር ያመጣው 2003 ላይ ይመስለኛል፤ ‘ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ’ ፖስትሞደርኒስት ነው ብዬ Paper ሳቀርብ። ከዚያ በፊት ተለይቶ አያውቅም። አንዳንድ ሰዎች ጋም ተከራክረናል እንደዚህ። አሁን ምንድነው? አንደኛ የፒ ኤች ዲ Paperኡን አላሳተምኩትም እንጂ እዚያ ላይ የተለየ አይነት ፖስትሞደርኒዝም ነው ብዬ Identify ለማድረግ የሞከርኩት አለ። ግን በምዕራባውያኑ ራሱ ከሄድን ፖስትሞደርኒዝም እና ፖስት ሞደርኒቲ ይለያያል። ፖስት መደርኒቲ ይኼ ትልቁ ዓለም ነው። የሚታይ ነገር ነው። በማኅበራዊ ሕይወቱ፤ በUrbanizationኡ... በብዙ በብዙ ነገር... ፖስትሞደርኒዝም እንደ ቴክኒክ ግን ሥነ ጽሑፍ ላይ ሊኖር ይችላል። በነገራችን ላይ [Jean-Francois] Lyotard.... ፖስትሞደርኒስት ፈላስፋ ነው... ምን ይላል መሰለህ? “Postmodernism is not after modernism. It is the nascent state.” ይላል።[7] ሞደርኒዝም ልክ ሲነቃ ያለው State እንደማለት ነው። ስለዚህ እንደውም ፖስትሞደርኒዝም ከሞደርኒዝም ሁሉ ይቀድማል ብሎ ይከራከራል። በነገራችን ላይ በጣም ብዙ አይነት ክርክር ነው ያለው። ‘Post-’ የሚለው ‘የጊዜ ቅደም ተከተልን ያመለክታል ወይ?’ የሚለው በራሱ ክርክር አለ። ለምሳሌ የ[Miguel de] Cervantes ዶን ኪሾቴ ፖስትሞደርኒስት ነው ብለው የሚከራከሩ ሰዎች አሉ። ምክንያቱም Feature አቹ በደንብ ይታያሉ እዚያ ውስጥ። ስለዚህ የመቀዳደም ምናምን ጉዳይ ላይሆን ይችላል። የሚያነሳው ሃሳብ ነው ዋናው። ሁለተኛ ሞደርኒዝምና ፖስትሞደርኒዝም ተመሳሳይ ቴክኒክ ቢጠቀሙም የሚጠቀሙበት Purpose ይለያያል። ሲቀጥል እንደ Reality እንደውም ከምዕራባውያኑ ቀድመን ፖስት ሞደርን የሆንነው እኛ ነን ብዬ ነው የምከራከረው እኔ። ለምንድነው እንደዚያ የምልህ? ለምሳሌ አንዱ የፖስትሞደርኒዝም መገለጫ የOld እና የ New አንድ ላይ Exist ማድረግ ነው። ይኼ ነገር እኛ ጋ Already አለ። መርካቶን እየው። እንደ Modern ዘመናዊ ሕንጻዎች አሉት። ግን Neat የሆነ ነገር የለውም። እኔ አሁን መርካቶ ገብቼ ሰው አቅጣጫ ሳልጠይቅ ወጥቼ አላውቅም። ሞደርኒቲ አንዱ መገለጫው ምንድነው መሰለህ? ወጥ እና በደንብ Identified የሆነ መሆን አለበት። ፖስት ሞደርን ግን እንደዚያ አይደለም። ገባህ? ለዚያ ነው... Spatially... እኛ Already ፖስት ሞደርን ነን ብዬ የምከራከረው። አሁን እንደውም አፈረሱብን እንጂ አሪፉ ምሳሌ ፒያሳ ነበር። የሆነ Amazing ፎቅ እና አንድ የጥንት ሕንጻ Coexist ያደርጋሉ። እንደዚህ አይነት Space የለም ሌላ ቦታ። አንዱ የፖስትሞደርኒዝም መገለጫው ይኼ ነው። በዘመናቸው የማይገጥሙ ነገሮች Juxtaposed ይሆናሉ፤ እንደጎረቤት። ሞደርኒቲ ጽድት ያለ ነው። ለምሳሌ የሆነ ክፍለ ሃገርን እና አዲስ አበባን ተመልከት። ሁለቱም አንድ ሃገር ናቸው። እዚያ ለብዙ ሺህ ዓመታት ያልተቀየረ ነገር ታገኛለህ። እዚህም ልታገኝ ትችላለህ። በጣም Modern የምትለውም Space እዚሁ አለ። አንዱ መገለጫው ይኼ ነው። ሌላው መገለጫው ምን መሰለህ ደግሞ፤ ለምሳሌ ቤት የማይመታ፤ ስሜት የማይሰጥ ግጥም። በጣም ብዙ አለን በነገራችን ላይ፤ በአማርኛም በግዕዝም። ምንድነው ይኼ... ‘ተንከባለለ እንደሙቀጫ፤ ምናምን አይኑ ፍጥጥ አለ።’ አይነት።[8] ሃሃሃሃ... በቃላት መጫወት የምትለው። አሁን [Jacques] Derida ይኼ ነው ሃሳቡ፤ በቋንቋ መጫወት። ‘Play’ የሚልህ ይኼንን ነው። Already እኛ ባሕል ውስጥ አለ። ስለዚህ ፖስትሞደርኒዝም

---

7. "...postmodernism is not modernism at its end but in the nascent state..." Lyotard, The Postmodern Condition, 1984 [1979], 79
"Furthermore, says Lyotard, a work can become modern only if it is first postmodern, for postmodernism is not modernism at its end but in its nascent state, that is, at the moment it attempts to present the unpresentable, 'and this state is constant.' " Stanford Encyclopedia of Philosophy, Postmodernism - https://plato.stanford.edu/entries/postmodernism/#:~:text=Furthermore%2C%20says%20Lyotard%2C%20a%20work,%5B1979%5D%2C%2079).
የLyotardን መጽሐፍ ለማንበብ የሚከተለውን ማስፈንጠርያ (Link) ይጠቀሙ።
https://drive.google.com/file/d/1doiyvdoiMNMQU76wX3QcJdqbJNxrBp_s/view?usp=drivesdk
8. ወጣ ወጣ እና እንደሸንበቆ፥ ተንከባለለ እንደ ሙቀጫ!

የሚለው የግድ የጊዜ ቅደም ተከተልን ማመልከቻ አይደለም። ሰው ነው ብሎ ሊከራከርህ ይችላል። ምክንያቱም ፖስትሞደርኒዝም ፍልስፍና ነው? ወይስ የሆነ Movement ነው? ምናምን... ገና አልተወሰነም። ብዙ ክርክሮች አሉ። ገና ይኼን ሳንጨርስ Post-Post Modernism የሚባል ደግሞ መጣ። ሌላ...

መዲና- በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ...

ፀደይ- አይነት ነገር። ሃሃሃ...

መዲና- እሺ! ሥነ ጽሑፋችንስ ግን!

ፀደይ- እንዳልኩህ ነው። አዳም [ረታ] እኔ ሳነብ ያገኘኋቸው፣ በትክክል የፖስትሞደርኒዝምን እንትኖች የሚያሟሉ፣ ግን At the same time ቅድም ወዳልኩህ ወደ Nihilism የማይሄዱ አይነት Featureኦች ስላየሁበት... መለስ ያለ ፖስትሞደርኒዝም ነው ብዬ ነው የምከራከረው። ምክንያቱም አንዳንዶቹ የፖስትሞደርኒዝም ሥራዎች Totally ወደ ትርጉም አልባነት ሊወስዱህ ይችላሉ። አላቸው Meaning... ግን ይኼ Meaning፣ Meaninglessness ሊሆን ይችላል። በምዕራቡም መለስ ያሉ ፖስትሞደርኒስት ፀሐፍያን አሉ በነገራችን ላይ። አንዳንዶቹ ደግሞ ድንበር ላይ ናቸው፣ በጣም ብዙ ሰው ይከራከርባቸዋል።

መዲና- እሺ! ግን ከእነዚህ ውጪ ያለውስ ሥነ ጽሑፍ...

ፀደይ- ማለት.... ሊሉት የሚፈልጉትን ነገር ይኼ የተሻለ ይገልጽልኛል ብለው ካሰቡ ችግር ያለው አይመስለኝም። ለምሳሌ አሁን ያለንበት ዘመን Chaotic ነው። 21ኛው ክፈለ ዘመን ላይ ሆነን 18ኛው እና 19ኛው ክፍለ ዘመን ላይ የነበረ ነገር ነው እያባላን ያለው። በጣም Amazing Coexistence ነው። 21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ እንዳለ ሰው መሄድ አልቻልንም። አሁንም ያልፈታናቸው ችግሮች አሉ። ይኼንን እንዴት ታስማማዋለህ? አንድ ደራሲ ይኼንን Absurd የሆነ Coexistence ፖስትሞደርኒዝም የተሻለ ይገልጥልኛል ካለ መብቱ ነው። ትክክልም ነው ደግሞ። አሁን ለምሳሌ አዳም እንደ ሞደርኒስት 'ማኅሌት' ላይ ሞከረ። ሞደርኒስት እና ሞደርን ራሱ ልዩነት አላቸው በነገራችን ላይ። 'ፍቅር እስከ መቃብር' ሞደርን ነው። 'ከአድማስ ባሻገር' ሞደርን ነው። 'አደፍርስ' ግን ሞደርኒስት ነው። Experimental ነገር አላቸው ሞደርኒስቶች። 'ማኅሌት' በጣም Experimental ነው። 'ግራጫ ቃጭሎች' ላይ ሲመጣ ግን Totally የተለየ ሆነ። Identify ላደርግ የቻልኩትም ለዚያ ነው። እና ደግሞ በብዛት ነው የተጠቀመበት፣ ፖስትሞደርኒዝምን። ምክንያቱም ሊል የሚፈልገው ነገር አለ በዚያ Novel። ሊል የሚፈልገውን ነገር መባያ መንገድ ያገኘው በዚህ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ አንድ ደራሲ 'መናገር የምፈልግበት መንገድ ይኼ ነው።' ብሎ ካለ ለእኔ በቂ ነው። ዘመን አልጠብቅም። ምክንያቱም ሁሉንም ከውጪ ነው ያመጣናቸው። እኛ የራሳችን የፈጠርነው ገና የለንም። በመንፈሳዊው ሊኖር ይችላል፣ ቅድም እንደተባባልነው። በዓለማዊው ግን የለም። የእኛ የምናደርግበት መንገድ ሰጥቶናል አዳም። ለምሳሌ ፖስት ሞደርኒስቶች Kit የሚሉት ነገር አለ። የምትልበትን መንገድ፣ የራስህን ሞዴል መፈለግ። አሁን እርሱ እንጀራን ነው ሞዴል አድርጎ የወሰደው። አሁን ለምሳሌ የምትልበትን ከገለጸልህ፣ እና ባሕልህ ውስጥ ያለ ነገር ከሆነ ለምን አትጠቀምበትም? የእሱባለውን [አበራ] የወደድኩት ለዚያ ነው። ማለት... የተሻለ ማድረግ የሚቻልባቸው መንገዶች ነበሩ ብዬ አስባለሁ። ግን እንደ መጣሪያ Local የሆነ ነገር ለመፈለግ መሞከሩ። አሁን ኮምፕዩተር ላይ የሉም የያሬድ የዜማ ምልክቶች። በእጅ ጽፈው ወይ የሚቀራረብ ምልክት ፈልገው ነው የሚያስገቡት። አሁን ግን እንዲህ ሲሆን ትኩረት

ይሠጠዋል። ይጠናል። አገልግሎት ላይ የሚውልበት መንገድ ካለ Keyboard ላይ ይገባል። Philosophize ታደርገዋለህ። አሁን እንጀራ ሰባ በመቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚያስተሣሥር ነገር ነው። Philosophize አላደረግነውም። ዕድል ይሠጥኻል Philosophize ለማድረግ። የምዕራቡ ዓለም እንጀራ የለውም ለምሳሌ። የተለየ ነገር ነው። ምክንያቱም ፖስትሞደርኒዝም አንዱ የሚያተኩርበት ነገር Difference ነው። ሁሉም Culture አንድ አይደለም። ልዩነቶች አሉት። ሞደርኒቲ በባሕርዩ ጨፍላቂ ነው። ፖስት ሞደርኒዝም ግን 'የለም፣ ልዩነቶች አሉን። Entertain ማድረግ አለብን። Marginalized የተደረጉ ወደመሐል መምጣት አለባቸው።' ምናምን ምናምን ይላል። አየህ! ወደ መሐል አመጣው። ስለዚህ የተጫነ ነገር ነው ብዬ አላምንም። እኔም ያኔ ፖስትሞደርኒስት ነው ስል የተሻለ ሥነ ጽሑፉን እንድንረዳው ነው። ምሳሌ ልስጥህ። አሁን ይኼንን ዓረፍተ ነገር አንብበው።

[ስልኳ ላይ የፒ ኤች ዲ ጽሑፏን ከፍታ አቀበለችኝ።]

መዲና- Withoutspacesnocoherentsentencewouldexist. ይላል። ግን Space የለውም።

ፀደይ- አዎ። አሁን ምንድነው ትርጉሙ መሰለህ? Space ከሌለ በፊደላት መካከል ማንበብ አትችልም ነው። ሙሉ መጽሐፍ እንደዚህ ቢጻፍ ማንበብ አያቅትህም? ያቅትሃል። አሁን ምን አደረግኩ መሰለህ? አዳም ሕጽን የሚላቸው አሉ። የሚገርምህ ነገር በግዕዝ ቋንቋ ላይ በፊደላት መካከል ያለው ክፍት ቦታ ስም አላቸው። ሁለት ነጥብ እንጠቀማለን እንጂ Space አንሰጥም። አሁን እየተለመደ ስለመጣ ነው ቃል ጽፈን Space የምንጠቀመው። በትክክለኛው ግን Space አይሰጥም። ምናልባት "Space is not Empty" የሚል Philosophy አለ ማለት ነው። የሆነ Occupy የሚያደርገው ነገር ይኖራል እንጂ Vacuum የሚባል ነገር የለም ይሆናል።

መዲና- ለዚያም ይሆናል ዜሮ ቁጥር የሌለው በግዕዝ።

ፀደይ- አለ የሚሉ አሉ በእርግጥ። እንደ ሃሳብም ደግም ካለመኖር ወደ መኖር አይደለ እግዚአብሔር ፈጠረ የሚባለው?[9] ስለዚህ ባዶነት ነበር ማለት ነው። ከዚያ በኋላ የለም ይሆናል ባዶነት። ግን ለምሳሌ 'ቀ' ስትጻፍ... ወገቧን የምትይዝበት ክፍት ቦታ ሁሉ ስም አለው። አየህ! የእኛንም ፍልስፍና መልሰን እንድናይ በር የሚከፍት ነው የሕጽን Concept ። ከልብስ ጋርም Define ያደረገው ነገር አለ በእርግጥ። መነሻ ነው። በጣም ብዙ ነገር ሊወጣው ይችላል። ስለዚህ ወደራስህ ፍልስፍና ሊመልስህ ይችላል። Imposition አይደለም የምልህ ለዚያ ነው። ፖስትሞደርኒዝም አንዱ በረከቱ... ቅድም እንዳልኩህ ብዙ ችግሮች ቢኖሩበትም... ዳር የነበረውን መሐል ያደርጋል። Marginalize የተደረገን ባህል፣ ትኩረት ያልተሰጠውን ትኩረት እንዲሰጠው ያደርጋል። እያንዳንዱ Culture Contribute ማድረግ የሚችለው ነገር ካለው ያን የሚያደርግበትን ዕድል ይፈጥራል። ግን To The Extreme ሲሄድ ደግሞ አደጋዎች አሉት። እና... አሁን 'ይኼ ይኼ ጽሑፍ ፖስትሞደርኒስት አይደለም። እንዲህ እንዲህ አይነት ነገሮቹ ይኼንን ያፈርሳሉ።' የሚል ደግሞ ሌላ ሰው መኖር አለበት። እኔ ደስ ይለኛል። እንደዚህ አይነት Dialogueኦች ያስፈልጋሉ።


---

9. Ex Nihilo - እም ኀበ አልቦ ኀበ ቦ የሚሉት። አልቦ ዜሮ ማለት እንደሆነ ልብ ይሏል።

መዲና- ጨርሰናል። በጣም አመሰግናለሁ ጸዲ።

ፀደይ- Thank you በጣም። አሪፍ ጊዜ አሳለፍን።

[ከዶክተር ፀደይ ጋር ያለንን ቆይታ ጊዜ ገታው። ጨዋታችንን ጨርሰን ስንነሳ ግን ቀኑ ጨልሞ ነበር። ተሰነባብተን ተለያየን። ብዙ ያላነሳናቸው ርዕሰ ጉዳዮች ነበሩ። ወደፊት የምናካክስበት መንገድ እንፈጥራለን። ለዛሬ ግን ይብቃን!]



ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን
(1928 - 1998)

"አምባ ወጥቼ እኩለ-ሌት ፥ ስለት ገብቼ በስሟ፤
ከርሞ ሰይጣን በእርሷ አስቶኝ፥ ልገላገል ከሕመሟ፤
ጠበሷ አፋፍ በጨረቃ፥ ደጋግሜ ማጎሌት ቆሜ፤
ሆዴ ቃትቶ ባር ባር ብሎ፥ እርቃኔን ከሷ ታድሜ፤
ደጀ ሰላሟን በአራት እግር፥ ተንበርክኬ ተሳልሜ፤
በስጋዬ እሚነደውን፥ በጸሎት ላቤ አጣጥሜ፤
እፎይ ብዬ አመስግኜ፥ ውዳሴዋን ደጋግሜ...
ገና ከደጅዋ እልፍ ሳልል፥ ደሞ ይምጣ የቁም ህልሜ?
ሌት በጥምቀቷ የነጣው፥ ነጋ፤ ደፈረሰ ደሜ።
ለእርሷ እንጂ ለእኔ አልያዘልኝ፥ አዬ የስለት አታምጣ!
በውጣ ውረድ በጠበል፥ ባሣር ወዜ ቢገረጣ፤
ልክፍቷ እንደሁ አልለቀቀኝ፥ መሸ ደሞ አምባ ልውጣ!"

መሸ ደግሞ አምባ ልውጣ - ሎሬት ጸጋዬ ገብረ መድኅን

አጤሬራ

አዘጋጅ | ሚሊ የን



ዋቢ ሳቢ
WABI SABI

በጭንቀት ተዘፍቄ ራሴን የማገኝባቸው ቀናት በጣት የሚቆጠሩ አይደሉም። ጭንቀቱ ተስፋ መቁረጥ ድረስ ባይሆንም ሕመም እንዲሰማኝ ያደርገኛል። ይህ ሁሉ የመጣው ፍጹምነትን በመሻት ነው። አዎ! በምሠራው፣ በምጽፈው፣ በማነበው እና በምናገረው ነገር አንድ ወጥ መስተዋት የሚመስል ፍጽምናን ከራሴ ጠበቅሁ። ራሴን ያገኘሁት ግን እንደተሰባበረ መስተዋት ነበር።

በዙሪያዬ ያሉ ሰዎችንም አየሁ። ፍጹም ተብለው የሚጠሩ እንኳ ስማቸው ጋር መድረስ እንደማይችሉ ገባኝ። ሰው ሲባል በድካምና ጥንካሬ የተመላ እንጂ ፍጹም የበረታ እንዳልሆነ ተገለጠልኝ። ይህን ፍጽምና አለመድረስ አካባቢያችን ላይ በማየው ነገርም አስተውያለሁ። ለምሳሌ በምሠራበት ተቋም ውስጥ እጅግ ደስ ያሰኘኝ የነበረው ነገር ግቢው መሐል በሚገኝ ዋና አስፋልት ላይ የሚረግፉ የባሕር ዛፍ ቅጠሎችን መመልከት ነበር። በየዕለቱ ያጸዱታል፣ በየዕለቱ ይቆሽሻል። በእርግጥ እንደመቆሸሽ አልነበረም ያየሁት፣ እንደዉበት እንጂ። ከዚህ ጋር በተያያዘ የዋቢ ሳቢ ፍልስፍናም መነሻ ተደርጎ የሚቆጠረው በ16ኛው ክ.ዘ የተመዘዘ ተቀራራቢ አፈታሪክ ነው። አንድ ሪኩ የሚባል ወጣት፣ በጊዜው የታወቁ ታኪኑ ጆ የተእባሉ የዜን መነኩሴ/የሻይ ማስተር ጋር በመሄድ ስለቀደምት የሻይ አቀራረብ (Tea Ceremony) ለመማር ፈለገ። መነኩሴውም ሊፈትኑት ብለው የአትክልት ቦታውን እንዲያጸዳ አዘዙት። ከጥግ እስከጥግ፣ አንዲትም ቆሻሻ እንዳትገኝ አድርጎ ካጸዳ በኋላ፣ ለታኪኑ ጆ ለማሳየት ሲል፣ ጥቁር እንጨት (Prunus sp) የሚባለውን ዛፍ ሲነቀንቅ ቅጠሉ ወደመሬት ረገፈ።[1] [መነኩሴው መጥተው ሲያዩት፣ ምናልባት ተደስተው ቢሆን ነው ለፍልስፍናው መነሻ ተደርጎ የተወሰደው።]

ዋቢ ሳቢ ሕይወትን ከነጉድለቱ እንድንቀበል የሚያስተምር ውብ የአኗኗር ዘይቤ ነው። አንድ ገጸ-ድር ላይ ያገኘኹት ጽሑፍ አንድ ሰው አብርሆት ላይ የሚደርሰው ጉድለቱን መቀበል ሲችል እንደሆነ ይናገራል።

> *According to Zen, all things (our selves included) are impermanent and imperfect and the way to satori, or enlightenment is through embracing this imperfection.*[2]

1.https://japanobjects.com/features/wabi-sabi
2.https://spiritofjapantours.com/zen-philosophy-of-life/#:~:text=Finding%20beauty%20in%20imperfection%20%E2%80%93%20the,is%20through%20embracing%20this%20imperfection.

ዋቢ (Wabi) የሚለው ቃል ቀለል ባለ ኑሮ ውስጥ ያለውን ዉበት እንድንገነዘብ ሲያደርገን፣ ሳቢ (Sabi) በተራው ዕድሜያቸው የገፉ እና አይጠቅሙም የሚባሉ ነገሮችን ዉበት እንድናስተውል ይጠቁመናል።

ይህ ፍልስፍና ወይም የአኗኗር ዘይቤ በጃፓን ጥበብ (Haiku ተብሎ በሚጠራው ሦስት መስመር ግጥም ውስጥ)፣ ባህል፣ የሻይ ሥነ-ሥርዓት ውስጥ በሚገባ ይተገበራል።

ከእነዚህ መሐል ውስጤ በጣም የቀረልኝን፣ ወርቃማው ጠባሳ (Golden scars) ወይም Kintsugi የተሰኘው ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢተ ኤርሚያስ፣ ምዕራፍ 18 ላይ ስለሸክላ እና ሸክላ ሠሪ ይገልጻል። ያ ሸክላ ሠሪ ይሠራው የነበረው ሸክላ ሲበላሽበት እንደወደደ ሌላ ዕቃ አድርጎ ይሠራዋል።

ተወዳጁ በዕውቀቱ ስዩም በስብስብ ግጥሞቹ ደ'ሞ እንዲህ ይላል

ጋን ከጀርባ ወድቆ፣ ገል ኾኖ ቀጠለ
ከመሰበር ወዲያ፣ ሌላ ህላዌ አለ[3]

ጋን እንደቀድሞው ውኃ መያዝ ባይችልም፣ ከስብራቱ በኋላ ባለው ህላዌ ገል ሆኖ ይቀጥላል። ዋቢ ሳቢ ውስጥ የሚጠቃለለው 'ኪንሱጊ' ግን ከተጠቀሱት ሁለት ማንጸሪያዎች ለየት ይልብኛል። በኪንሱጊ መሠረት አንድ ጋን ቢወድቅ፣ በሌላ ህላዌ አይደለም የሚቀጥለው። ስብርባሪው ተሰብስቦ ወደቀድሞ ማንነቱ ይመለሳል። ይህም ብቻ አይደለም። ቅድሚያ በሙጫ (Lacquer) የተጣበቀው ስብርባሪ፣ የተጣበቀበት ሥፍራ በወርቅ ቅብ ያጌጣል።

Kintsugi reminds us that there is great beauty in broken things because scars tell a story.[4]

ኪንሱጊ ዋናው መልዕክቱ ስብራትም የሚነግረው የራሱ አንዳች ነገር ስላለው ዉብ መሆኑን መግለጽ ነው። ከዚህ ጋር በተገናኘ አንድ የታሪክ ሁነት ብናስታውስስ? የታሪኩ መነሻ ከዐድዋ ድል በፊት ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን ድል መቀሌ እና አምባላጌ ላይ ስትቀናጅ አፄ ምኒልክ ከእቴጌ ጣይቱ ጋር ያረፉት በደብረ ምሕረት ጨለቆት ሥላሴ፣ በቀይ ድንኳን ውስጥ ነበር። በድንኳናቸው እንዳሉ በማታ የተነሣው አውሎ ነፋስ፣ ድንኳኑን ጨምሮ ልብሰ መንግሥታቸውን ይወስዳል። በዚህ ተገርመው በነጋታው ሥላሴ ቤተክርስቲያን ገብተው፣ ተሳልመው፣ ጸሎት ካደረሱ በኋላ የቤተክርስቲያኑ ካህናት የወርቅ መስቀል ይዘው ያሳልሟቸዋል። ቀጥሎ ያለውን ከመጽሐፉ እናንብብ...

አፄ ምኒልክም ታላቁን የወርቅ መስቀል እንዳዩ በትልቅነቱ ተደንቀው፣ "ይህ መስቀል ሙሉ በሙሉ ወርቅ ነው? ወይስ ቅብ?" ብለው ጠየቁ። ካህናቱም፣ "ሙሉ በሙሉ ወርቅ ነው" ብለው መለሱ። ወዲያውም የንጉሡ አንጥረኛ ተጠርቶ የመስቀሉን ቀኝ ክንፍ አስቆርጠው ቢያስመረምሩት ሙሉ በሙሉ ወርቅ መሆኑን አረጋገጡ። ከዚያም የተሰበረው ጫፍ እንደነበር በወርቅ ይሠራ ብለው አዘዙ። ካህናቱ ግን፣ "ግርማዊ ሆይ፣ የመስቀሉ ክንፍ ተቆርጦ መታየት ታሪክ ስለሆነ በብር መጠገን አለበት።" ብለው ስለአመለከቱ ንጉሠ ነገሥቱም በብር እንዲጠገን ፈቀዱ። እስከዛሬም ድረስ ይኸው ይታያል።[5]

3.በዕውቀቱ ስዩም፣ ስብስብ ግጥሞች፣ ገጽ 115
4.https://www.omaritani.com/blog/wabi-sabi-philosophy-teachings
5. ከመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት፣ በዐድዋ ጦርነትና ድል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ድርሻ፣ ገጽ 34

ካህናቱ መሰበሩን ለትውልድ የሚተላለፍ ትልቅ ታሪክ እንደሆነ ገብቷቸው መስቀሉን በብር አሳደሱ። ይህን ተወዳጅ የኪንሱጊ ዐሳብ ሄኖክ በቀለ ለማ በቅርቡ ካሳተመው የግጥም መጽሐፍ፣ አራት ስንኞችን በመዋስ ልደምድመው።

... እንደ'ኔ ምትሻ፥
የመዳንን መንገድ
ከ'ንቧይ ካብህ ውረድ፥
ሰባራህን ውደድ [6]

ስብራት በራሱ የሚናገረው ታሪክ አለና ውብ ነው። ለሕይወታችን ልምድን እንቀስማለን፣ ሌሎችን እናክማለን (ወዳለመሰበር እንዳይደርሱም እንመክራለን)።

... ሩጫ፣ ፉክክር እና መታየትን መሻት ለበዛበት ኑሯችን፣ ሳንሠራም ሳናርፍም ለሚያልፈው ዕድሜያችን፣ ብናግበሰብስም ለማይጠረቃው ፍላጎታችን ዋቢ ሳቢ ቀለል ያለ መድኃኒት ይሆንልናል።

---

6. ሄኖክ በቀለ ለማ፣ ይናፍቀኛል፣ ገጽ 97



መጣጥፍ

REMEMBER ME

አዘጋጅ | መስዑድ ጀማል

“የሰው ልጅ ለምን የተወለደበትን ቀን ብቻ ያከብራል? የሞተበትስ ለምን አይከበርም?” ብለው ሜክሲኳዊያን “dia de los muertos” በማለት የሙታን ቀንን (Day of the dead) ያከብራሉ። በዓለም ላይ የማጂላንን ዱካ ተከትላችሁ ብታስሱ ከሜክሲኮ ውጭ የሙታንን ቀን የሚያከብር አንድም ሃገር አታገኙም። ታዲያ ይሄ ገራሚ ባህል ለአንድ ልዩ፣ አስደናቂና አይረሴ አኒሜሽን ፊልም መነሻ ሆኗል። COCO.

የፊልሙን ታሪክ በአጭሩ ላወራበት ካሰብኩት ጉዳይ ጋር አስተሳስሬ ሳቀርበው እንዲህ ነው...

ፊልሙ ላይ ሰዎች ከሞቱ በኋላ የሚሄዱበት ዓለም አለ፣ 'Land of the dead' ይባላል። ሕያዋን የሚኖሩበት ደግሞ 'Land of the living' ይሰኛል

ሚቾች የሚሄዱበት 'Land of the dead' የሚባለው ቦታ፣ ድጋሚ ሳይሞቱ፣ አፅማቸው ሳይፈርስ፣ ሉሲን ወይም አርዲን መስለው የሚኖሩበት ቦታ ነው።

ታዲያ እኒህ ሕያዋን አፅሞች የሚኖሩት በምድር ላይ እነርሱን የሚያስታውሳቸው ሰው እስካለ ድረስ ብቻ ነው። ፊልሙ ላይ አንድ የሚያሳዝን ሄክቶር የሚባል ገጸ ባሕርይ አለ። 'በጨው ደንደስ በርበሬ ተወደስ' የሚሉት ብሂል ደርሶበት መታወሻ ምግባር ሳያንሰው - ተዘንግቶ... ተረስቶ ሊሞት ጫፍ የደረሰ ... ሕላዌው በአንድ ሰው ማስታወስ ብቻ ተንጠልጥላ የቀረች... ላለመረሳትና ለመታወስ ሲባዝን የምናየው ምስኪን ፍጡር። ምስኪኑ ሄክቶር ስለገጠመው እጣ ፈንታ እንዲህ ይላል...


“When there’s no one left in the living world who remembers you , you disappear from this world. we call it the final death.”

አዎ! በሕይወት ያለ አንድም ሰው የሚያስታውስህ ካልሆነ የመጨረሻውን ሞት (The Final Death) ጽዋ ትቀምሳለህ። ሄክቶርም የገጠመው ይኼ ነበር። መረሳት!!!

ፊልሙ ላይ ዝነኛ የሆነች አንድ ዘፈን አለች። 'Remember Me' የምትል፤ ሄክቶር ለልጁ የደረሳት የነፍስ ሙዚቃ። የፊልሙን ሃሳብ የተሸከመች ናት። ሄክቶር ቀድሞ ይህ እጣ ፈንታ እንደሚገጥመው ሳይታወቀው አይቀርም።

Remember me, even if I have to emigrate.
Remember me, if you hear my guitar cry.

የሚሉት ስንኞች ትዝ ይሉኛል።



መረሳት- እውነትም የመጨረሻ ሞት ነው።

በሰዎች ልብ ውስጥ ቦታ ማጣት እውነትም የሞት ሞት ነው። ታዲያ ይህንን ሚስጥር ለሰው ልጅ ማን ሹክ ብሎት ነው? ልክ እንደፊልሙ ከሞት በኋላ ያለው ሕይወቱ እዚህ በቀሩት ሕያዋን ትውስታ ላይ ተንጠልጥሎ ይቀራል ብሎ ማነው የነገረው? እንጃ! ድርጊቱን ከታዘባችሁ ግን የሰማው አልያም የደረሰበት ሚስጥር እንዳለ የሚያሳብቅ ነው፡፡ የአደም ዘር እንደመረሳት የሚፈራው ነገር በዚህ ምድር ላይ የለም። ሰውን በተለያዩ አጋጣሚዎች 'አላስታወስኩህም!' ስትሉት እንዴት ነው የሚንጨረጨረው? መረሳትን ፍፁም አይሻምና ነው።

የሰው ልጅ በዚች ዓለም የሚከውናት እያንዳንዷ ቅንጣት ተግባር መታወስን ዒላማ ያደረገች ናት። የዛሬ ልፋቱ ነገ በሰዎች አእምሮ ላይ የራሱን የትውስታ መስክ አጥሮ ይዞ ለመቦረቅ በማለም የሚደረግ ነው።

ቢችል በመላው ዓለም፤ ካልሆነ ደግሞ በሚወዳቸው ሰዎች ዘንድ ብቻ ለመታወስ ይፍገመገማል። ታዲያ እንደመልኩ ሁሉ ለመታወስ የሚጥርበት መንገድም የተለያየ ነው።

አባወራው ዛሬ በሚስቱ በኩል ያለውን ዋሻ የሚምሰው ከዘኪዮስ ያጠረችውን ሐሴት ለማጣጣም ብቻ አይደለም! ነገ የእርሱን ስም እንደባቡር ፉርጎ ከኋላቸው አስከትለው በዘመን ሀዲድ ላይ የሚነጉዱ መታወሻዎቹን ለማግኘት ነው። 'ስም ከመቃብር በላይ ይውላል!' ማለቱስ ለዚህ አይደል?

አንዴ አምባሰል፤ አንዴ አንቺ ሆዬ እያለ በጉሮሮው ላይ ታች የሚንከለከለው ዘፋኝ ምን ከጅሎ ነው? ትንፋሹን ጆሯችን ላይ ሁ ብሎ ፈለጉን ሊያኖር... ከዚያም ባለ ሦስት መኝታ የተንጣለለ የትውስታ ጎጆ ከአእምሯችን ሊገዛ አስቦ ነው። ሀቁ ይሄ ነው፤[1] እኔ ልንገራችሁ።

1.ምንም እንኳ Sotheby የተባለው የኪነ ጥበብ ኢንስቲትዩት እ.ኤ.አ በ2018 ዓ.ም ባወጣው ጥናት መሠረት አሁን ካሉት የጥበብ ሥራዎች መሐል (በተለይ የሥነ ሥዕል እና የቅርጻ ቅርጽ ሥራዎች ማለት ነው።) የሚቀጥለውን ምእት ዓመት ተሻግረው ለቀጣዩ ትውልድ ትውስታ የሚበቁት ከአምስት በመቶ የማይበልጡት እንደሆኑ ግምቱን ቢያስቀምጥም፤ ማን ይሰማዋልና።

“በቁም ካፈቀርሽኝ
ስሞት እንዳትረሽኝ” ብሎ ጨርሶታል'ኮ ጥሌ።

አንገቱን ቀብሮ ወረቀቱን በእስክርቢቶው እያረሰ ዘሩን የሚዘራው ደራሲም ግቡ የጥበብ ሃራራውን ማስታገስ አልያም ውስጣዊ ሃሴትን መሸመት ብቻ አይመስለኝም። ስሙን በተነቀሱ የጥበብ ፍሬዎቹ ነገ ሊታወስ ፈልጎ ነው። ለሌላ አይደለም።

በ'ርግጥ እዚህ ጋር እንደፍራንዝ ካፍካ እና ፈርናንዶ ፔሽዋ ያሉ በሠሩት ሥራ መታወስ የማይፈልጉ ደራሲያን መኖራቸውን ዘንግቼ አይደለም። ሁለቱም በሕይወት ዘመናቸው በስማቸው ያሳተሙት ነገር በብዛት ካለመኖሩም በተጨማሪ ሲሞቱም ጽሑፎቻቸው እንዲቃጠሉ ወይ እንዳይታተሙ ተናዝዘው የሞቱ ናቸው። ምንም እንኳ በኑዛዜ አስፈጻሚዎቹ መልካም ፈቃድ እና አለመታዘዝ ሥራዎቻቸው ለትውልድ ተርፎ ዘመን አልፈው ቢታወሱም።

በተለይ ፈርናንዶ ፔሽዋ ለመታወስ ካለመፈለጉ የተነሳ ሲፅፍ ከመቶ በላይ የብዕር ስሞችን እና ማንነቶችን ይጠቀም ነበር። ልጨኛ ሥራውን 'The Book of Disquite'ን ይመለከቷል። ይሄን ታሪክ ስሰማ መጀመሪያ ገረሞኝ ነበር። “የመታወስን ፍላጎት በአዕምሮው ሸጉጦ ያላኖረ ሰብእ እውን ይኖራልን? እንዴት?” ብዬ ትንሽ አሰላ አደረግኩኝ። እናም ላለመታወስ ብሎ ለቁጥር በሚያታክቱ የብዕር ስሞች ሲፅፍ ኑሮ የሞተው ገጣሚ If, After I Die በተሰኘ ግጥሙ ልክ እንደ ማንኛውም ሰው መታወስን በሩቁ ሲታከክ እንደነበር አስተዋልኩ።

If, after I die, they want to write my biography,
There is nothing more simple.
There are only two dates – the one of my birth and that of my death.
Between the two every day things are mine.
I’m pretty easy to define.
I saw myself as a fool.
I loved things without any sentimentality.
I never had a desire that I couldn’t realise, because I never blinded myself.

እኒህን ስንኞች ለማስረጃ ባቀርብ በቂ ይመስለኛል። አንዳንዴ እንዲህ ይሆናል። መታወስን እሸሻለሁ የሚልን ጀግና፣ ቀረብ ብላችሁ ብታጤኑት በስውር መታወስን ሲያባርር ልትይዙት ትችላላችሁ።

በርካቶችም የዝና ማማ ላይ ተንጠላጥለው መሰቀል የሚፈልጉት ከማማው ላይ ሆነው ነፋስ ሊቀበሉ አስበው አይደለም። ይልቁንስ በበርካቶች ዘንድ ዘመናትን ተሻግሮ ለመታወስ ነው።

የሰው ልጅ ሞትን የሚፈራ ይመስላችኋል? በጭራሽ! መረሳትን ነው የሚፈራው። አለመታወስን ነው የሚሸሸው። እዚህ ጋር የሄኖክ በቀለ ለማ “ሀገር ያጣ ሞት” መፅሐፍ ውስጥ ያለ ‘ተስፋ’ የተባለ አንድ ሚስኪን ገፀ ባሕርይ ትዝ አለኝ። ‘ተስፋ’ እንዲህ ይላል...




"ሞትን እፈራዋለሁ? አ! አ! ይልቅ መረሳትን ነው የምፈራው። ነገ ውስጥ ዕድል ፈንታ ማጣትን ነው የምፈራው። ነገ የማልተነፍሰው አየር ይነፍሳል፤ ነገ አበጀህ የማልለው፤ አጠፋህ የማልለው ንጉሥ ይነግሣል። ነገ የማልጠለለው ዝናብ ይዘንባል፤ ነገ የማልሰማው ወሬ ሀገሩን ያዳርሳል። የምፈራው ይህንን ነው። የምፈራው መብነን ነው። ነገ ተስፋ ማን እንደሆነ ትርጉም የማይሰጥበት ጊዜ ይመጣል። የምፈራው እርሱን ነው።"[2]

በቃ ይኼው ነው። በዚች ምድር አንድ ሰው በሠራው ሥራ እንደሚታወስ እርግጠኛ ከሆነ ሞትን ለምን ብሎ ነው የሚፈራው? አሁን ሻለቃ አትሌት ኃይሌ ገብረ ሥላሴ ሞትን የሚፈራ ይመስላችኋል? አስቴር አወቀስ? እኔን'ኛ! እኔ አይመስለኝም። ምክንያቱም ነገ የሚታወሱበትን ሥራ ባላቸው ጊዜ ሠርተዋልና ነው።

አጋፋሪ እንደሻው ሞትን የሚፈሩትና የሚሸሹት ለመታወስ የሚያበቃቸውን ሥራ ስላልሠሩ ይመስለኛል። አገር እያሳበሩ ምድርን በጹካቸው ከሚያዳርሱ... ምናለ በሰዎች አእምሮ ውስጥ ትውስታቸውን ለማኖር ቢኳትኑ!? ቀላሉ መንገድ ይሄ ነበር። ምክንያቱም[3] ሞትን ሸሽተን አናመልጠውምና።

ሕይወት አጭር ናት፤ በእጃችን እንዳለ አረፋ አልያም ቀና ብለን ሰማይ ላይ እንደምናየው ጉም። ሰዎች ካለፉ በኋላ በክፉም በደጉም ይታወሳሉ። ሁሉም ሰው በተመሳሳይ መንገድ አይታወስም። እነ ሂትለርን፤ ጆሴፍ ስታሊንን፤ ኤዲ አሚንን ዛሬም እናስታውሳቸዋለን፤ ግን ጥሩ ባልሆነ መልኩ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ማንዴላን፤ ጋንዲን፤ ካትሪን ሀምሊንን፤ ማዘር ትሬዛን... ወ.ዘ.ተ ምድር ለይ ሠርተውት በሄዱት መልካም ሥራ እናስታውሳቸዋለን።

Herostratus የተባለውን ሰው 'Madman' ብለው ይጠሩታል ፈረንጆቹ፤ የታላቁ እስክንድርን መወለድ እና የአማልክቱን መዘገናጋት ተጠቅሞ ከሰባቱ የዓለም ድንቅ ቅርሳ ቅርስ መካከል የሚቆጠረውን የአርጤምሲስን ቤተ መቅደስ (The Temple of Artemis) ጣርያ በእሳት አያይዞ ያቃጠለው በታሪክ ስሙ እንዲታወስ ስለፈለገ ብቻ እንደሆነ ይነገራል። በዚህም ምክንያት 'Herastratus' የሚለው ቃል በመዝገበ ቃላት ውስጥ ራሱን በየትኛውም ዓይነት መንገድ ተጠቅሞ ዝነኛ እና የሚታወስ ሰው ለማድረግ ለሚጥር ሰው የተሰጠ ገላጭ ሆኖ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ውስጥ ገብቷል። ይህ ሰው ተሳክቶለት ዘመን አልፎ እኛም በዚህ ሰበብ የምናስታውሰው ሆነናል።





2. ሀገር ያጣ ሞት፤ ሄኖክ በቀለ ለማ፤ ገጽ 163

3.አጋፋሪ እንደሻውን ከነ ሞት ፍርሃታቸው ዛሬ ላይ ማስታወሳችን አልቀረም፤ ዕድሜ ለስብሐት ገብረ እግዚአብሔር

እንጂ አጋፋሪን ማን አባ ከና ይላቸው ነበር አሁን?

አንድ ነገር ግን ልብ በሉ!

እንደነ 'Herostratus' በክፉ ነገር ከመታወስ መረሳት ይሻላል ባይ ነኝ። ሰው በመልካም ነገር መታወስ ሲችል ነው ያልባከነ ሕይወት ኖሮ አለፈ የሚባለው። እዚህ ጋር አንድ ሌላ ታሪክ ትዝ አለኝ። አንድ ሰው ሀገር አማን ብሎ፣ ከወንበሩ ላይ እንደተቀመጠ የጠዋቱን ዜና ለማንበብ ጋዜጣ ያገላብጣል። ድንገት ግን የራሱን ስምና ፎቶ ከጋዜጣው መግቢያ ላይ ይመለከታል።

ጋዜጣው እርሱ መሞቱን ይገልፃል። ዝቅ ሲል ደግሞ ስለራሱ የሕይወት ታሪክ የተፃፈውን ጽሑፍ አነበበ። ሰውየው ይህን ሲመለከት በጣም ደነገጠ። 'እንዴ... ሞቻለሁ እንዴ?' ብሎ ብቻ አልነበረም የደነገጠው።

የዚህን ሰው ሞት ለመግለፅ በጋዜጣው ላይ 'የተቀጣጣይ ፈንጂው ንጉሥ ሞተ! (Dynamite King Dies)' እንዲሁም 'የሞት ነጋዴው ሞተ! (Merchant of Death Dies)' የሚሉ ርዕሶች ተሰጥተውት ማየቱ ነበር ያስደነገጠው።

ይህ ሰው ግዙፍ ተራራዎችን፣ ህንፃዎችን ለማውደም የሚያስችል ተቀጣጣይ ፈንጂን (Dynamite) የፈለሰፈ እንዲሁም ጦር መሳሪያዎችን በመሸጥ ኪሱን በረብጣ ዶላሮች መሙላት የቻለ ታዋቂ ባለሀብት ነው።

ጋዜጣው ላይ ስለ እርሱ ሞት ሲዘገብ 'የሞት ነጋዴ' ተብሎ የተገለፀበትን ቃል ሲያነብ ውስጡ ላይ 'እንደዚህ ነው የምታወሰው ማለት ነው?' የሚል ጥያቄ ፈጠረበት።

ይህ ሰው አልፍሬድ ኖቤል ነበር። በወቅቱ የሞተው ወንድሙ ሲሆን ጋዜጣው ግን ኖቤል የሞተ መስሎት ነበር።

አልፍሬድ ኖቤል የራሱን የሕይወት ታሪክ ከጋዜጣው ላይ ሲያነብ በጣም ደንገጠ፤ አዘነም። እስከዚያን ቀን ድረስ



አልፍሬድ ለሰው ልጆች የሚጠቅም ነገር እንደሠራ እና ከሞተም በኋላ ሰዎች በሠራው ሥራ እንደሚያስታውሱት ያስብ ነበር። ጋዜጣው ላይ የእርሱ የሕይወት ታሪክ ግን "በሞት ነግዶ ያተረፈው ሀብታም ሞተ!" በሚል ርዕሰ አንቀፅ ነበር የወጣው። የተሳሳተው ጋዜጣ ኖቤልን አነቃው። ከዚያች ቀን በኋላ እንቅልፍ አጣ።

አልፍሬድ ኖቤል ይህን ታሪኩን ካነበበ በኋላ ሰዎች የእርሱን ውስጣዊ እውነተኛ ማንነት እና ለሰዎች ያለውን ቅን አስተሳሰብ እንዲረዱለት ለማድረግ ቆርጦ ተነሳ። ዓለም በሰላምና በመልካም መልኩ እንዲያስታውሰው የኖቤል ሽልማትን መሠረተ።

እነሆ ዛሬ በመላው ዓለም ከሚሰጡ ሽልማቶች ሁሉ የኖቤል ሽልማት እጅግ ከፍተኛ ክብር ያለው ለመሆን በቃ። ሽልማቱ በፊዚክስ፣ በኬሚስትሪ፣ በሕክምና እና በፊዚኦሎጅ፣ በሥነ ጽሑፍ፣ በሰላም፣ እና በኢኮኖሚክስ የላቀ አስዋጽኦ ላበረከቱ በየዓመቱ ይሰጣል።

ወንድሜ... ዛሬ አልፍሬድ ኖቤል ሲባል ትዝ የሚልህ ምንድን ነው? እንደው ለመሆኑ አልፍሬድ ኖቤል ድማሚት እንደፈጠረስ የምናውቀው ስንቶቻችን ነን? ይኼው ነው፡፡ በዚች ዓለም ትርጉም ያለው ሕይወት ኑረን አለፍን የሚባለው በወዳጆቻችን፣ በቤተሰቦቻችን፣ በሀገራችን

ብሎም በዓለም በመልካሙ መታወስ ስንችል ነው።

ወደ ተነሳሁበት ፊልም ልመልሳችሁ፤ ሄክቶር ‘Remember Me’ የሚለውን ሙዚቃ የፃፈው ለልጁ ለCoco ነበር። ምክንያቱም በሥራ ለጉብኝት ራቅ ወዳለ ቦታ ሲሄድ ስለነበር። Coco በዚያ ሰዓት ህጻን ነበረች። ዝም ብሎ መሄድ ይችል ነበር። ግን እንዴት ብሎ? የሰው ልጅ አይደል? የሆነ ነገር ሳይጥል ርቆ መሄድ አይችልም። እንድታስታወሰው ስለፈለገ ‘Remember Me’ን ደርሶ ዘፈነላት። ከዚያ ግን አልተመለሰም ነበር። ልጁ Coco አባቷን የምታስታውሰው ሌላ በምንም አልነረም፤ በሙዚቃው ነው፤ በሠራው ሥራ። የመጨረሻውን ሞት ያመለጠውም በሕይወት እያለ መታወሻ እንዲሆነኝ ብሎ በሠራው ሥራ ነው። ይሄው ነው። ለሰው ልጅ የዛሬ ሥራው ለነገ ቤዛው ነው። ዝም ብሎ እንዲሄድ አልተፈቀደለትም። እርሱም አይችልም።

እኔስ በዚህ ጣትን እንደሰንሰለት በሚያሳስር ብርድ እስክርቢቶ ይዤ ወረቀቱን የምፈትገው ለምንድን ነው? ልክ እንደክብሪት በእስክርቢቶዬ ከወረቀቱ እሳት ጭሬ ልሞቅ? አይ አይደለም።

የሆነ ነገር ማለት ፈልጌ ነው!

ምን?

REMEMBER ME!



ገጣሚ | ቃለአብ አባይነህ

የመሸነፍ ማኒፌስቶ

ያልሰነፍኩበት የጦር ሰልፍ፤
ያልተሸነፍኩት መሸነፍ፤
ያልገፈተረኝ ቀኝም፤
ተፈልጎ አይገኝም።

ገናና የውስጤ ጽልመት፥
ስጨፍን የሚፈረጥም፤
ከታየኝ፤
ዓይኔን ስገልጥም...

አጎንብሼ ያሳለፍኩት፥
ማዶ ያለ መከራ አውሎ፤
ምናልባት አቅም አግኝቶ፤
ዳግመኛ ከቆመ ብሎ፤
ከቆየኝ፤
አስፋልት ተሻግሮ...

የትም ብጠለል ከዶፉ፤
አላመልጥም ከወጨፉ።

ይልቅ...
ሰማዩን ምድሩን ያስነባ፥
የሐዘን ቀን አመለጠኝ።
***
እኔ ውስጥ አይደል ወይ?
ጎልያድ ዳዊትን፥ እንደ ትጓን ያፈረጠው...

እኔ ውስጥ አይደል ወይ?
ጌዴዎን ከነትምክህቱ፤
ከነሥስት ምዕት ሠራዊቱ፤
እምጥ ይግባ ስምጥ፥ ያልታወቀው።

እኔ አይደለሁም ወይ?
መሸነፍ እንደሱስ፥ የተጠናወተኝ፤
ብሸነፍ ብሸነፍ፥ ሠርክ እማይታክተኝ፤

እኔ አይደለሁም ወይ?
ውድቀቴ 'ንኳ፤
ያልተሳካ፤
በወጉ መውደቅ ያቃተኝ።
***
በናፍቆት እጇን ዘርግቼ፤
በናፍቆት አፈን ከፍቼ፤
የጠበቅኩት ተስፋ መቁረጥ፥ ከክረምቱ ጋር
አለፈኝ፤
መጻው ነፋስ ተከናንቦ፥
አደይ አበባ ጨንብሎ፥ ተስፋ ታግሎ አሸነፈኝ።

ጳጉሜ 3፤ 2015 ዓ.ም

ልብወለድ

የክረምት ቀለም

ደራሲ | በረከት ጌታነህ

ሰማዩ ያጉረመርማል። ዝናብ “መጣኹ መጣኹ” እያለ ይፎክራል። እርጥበት ሲነካው ከሚፈርስ የገላ ዐምድ እንደተሰራ ኹሉ መንገዱን የሞላው መንገደኛ ከአረማመዱ መፍጠን ጀምሯል።

እርሱም የግሩን ስልተ-ምት አስተካከለ።

ከሰዉ አናት በላይ የተዘረጉ ጃንጥላዎችን እየገፋ ሲጣደፍ የእንጉዳይ ማሳ ውስጥ የሚሽሎከሎክ ትንሽ ፍጥረት የሆነ መሰለው። ከልጅነቱ እና ከዝናብ ሲሸሽ እዚህ ደርሷል።

እያንዳንዱ እርምጃ ከልጅነትና ከዝናብ ሽሽቱ የሚጠለልበት ጥግ የሚያደርሰው ጥድፊያው ነው። የልጅነት ጊዜውን ዶፍ እንደ አሽን ከንፍ አርግፎበታል። ባልንጀሮቹ ብር ትር ሲሉ በደረቱ እየተሳበ ለመቆም እንደሚፍጨረጨር ነፍሳት ነበር። “ዝናቡ አሳድገኝ!” እያሉ ከሚዘምሩ ሕፃናት እኩል እጆቹን ዘርግቶ አናቱን እስከሚያዞረው ተሽከርክሯል። ዝናቡ ሲከር ጓደኞቹ በወላጆቻቸው እየተጠሩ ሲኼዱ የተሸከረከረበት ቦታ ላይ ተደፍቶ የበረዶ አንኳር በኩርኩም አፍልሶታል። በውድ ባይሆንም በግድ የብዙ ክረምት ዝናብ በቁሙ ተግቷል። መንታ አንቴናውን ሰብስቦ ወደዛጎሉ የሚሸሸግ ዝልግልግ ፍጥረት እንኳን ሳይቀር ከዝናብ የሚሸሸበትን አልባስ የቸረ የተፈጥሮ አድሏዊ ሚዛን ምስል በልጅነት ልቡናው ታትሞ ቀርቷል።

ጊዜ እንደ ዔሊ የተንቀራፈፈበትን የልጅነቱን ትዝታ ከነድንጋዩ ትቶ በሕይወት እውራ ጎዳና ወደኋላ ሳይንሸራተት ወደፊት መንጎድን ይሻል። ማደጉ ትርፉን አስልቶት ባያውቅም ከዝናብ የሚሸሽበትን ጉልበት ግን ሰጥቶታልና ያንን ማእዘን ፍለጋ ከ’ርምጃው መፍጠን፣ እና ከዝናብ ማምለጥ አለበት።

በደመ ነፍሳዊ እርምጃ ከትናንቱ የሚያባርረውን ዝናብ የሚያመልጥበትን ሥፍራ ጎሠሣ ተራወጠ።

የሥጋቸው ክብደት ግድ የሚላቸውን በመመዘን ሳንቲም የሚለቅሙ ሕፃናትና ሚዛናቸው እንዳያደናቅፉት ዘለለ። አንጀት በሚያንሰፈሰፍ የዋሽንት እንጉርጉሮ ታጅቦ የሚለምን ባለ ክራንች ወጠምሻ ያነጠፈው ምጽዋት መቀበያ ግምጃ ቅልጥሙን ፈተነው። ምርኩዙን የሚያወዛውዝ ዐይነ-በሲር እንዳይገጭ እየተጠነቀቀ፣ ውሃ ያቆረ ኩሬ እንዳያንቦራጭቅ እየተሳቀቀ መንገዱን ተሻገረ።

እግሩ ያደረሰው ህንጻ ውስጥ ገባ። አካባቢውን ሲቃኝ የህንጻው አስራ አንደኛ ወለል ካፌ መኖሩን የሚናገር ማስታወቂያ ተመልክቶ አሳንሰር ተሳፈረ።

እንደልብ የሚንሸራሸሩበት የካፌው እልፍኝ አፉን ከፍቶ ሰለቀጠው። በሚያየው

እንግዳ ትእይንት ለአፍታ ተደናገረው።

የአገልግሎት ዘመናቸው ያበቃ ቁሳቁሶች ለጌጥነት በየጥጉ ተቀምጠዋል። ካሴት ጎራሽ ራዲዮ፣ የድሮ ቴሌቪዥን፣ መቅረጸ ምስል፣ የሽክላ ማጫወቻ፣ ዓይኖቻቸው እንቁላል የሚያካክሉ አንገታቸው ቀጭን ጸጉረ አፍሮ ሥዕሎች፣ በሃረግ ተክል ዐይነት ተጠላልፎ የተሰናሰለ ሥነ-ጥበብ ካፌ የሚል ጥቁር ጽሑፍ በነጭ መደብ ላይ ተሥሏል።

በሙዚቃ መሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ የኃይሉ መርጊያ ሙዚቃ ይሰማል። አንዳንድ ተስተናጋጆች የቁም ጠረጴዛ በክርናቸው ተደግፈው እርስ በርስ ያወጋሉ። ብቻቸውን የተቀመጡም ይታዩታል።

ወርቃማ ቅብ ያላቸው አምፖሎች የሚያፈልቁትን ቢጫ የብርሃን ባህር እየቀዘፈ ጥጉን ፈለገ። እንደውሻ የሠራ አካሉን አርገፍግፎ የተሸከማቸውን የዝናብ ነጠብጣቦች ማራገፍ አሰኘው። ፊት ለፊቱ የሚታየው ግድግዳ ላይ

ውድ እንግዶቻችን በሳምንት አንድ የተመረጠ ቀን የምንወደውን ደራሲ እዚህ የመጋበዝ ልዩ ልማድ ያለን መሆኑ ይታወቃል። እንደተለመደው ዙሉ የዚህ ሳምንት የሥነ-ጥበብ ካፌ ባለሟል---------- ነው ። በመሆኑም ደራሲውን ማግኘትና ከእርሱ ጋር መወያየት፣ ማስፈረም እና ማስታወሻ ፎቶግራፍ መነሳት የምትፈልጉ በ-----ቀን ተገኝታችሹ ከቡና ቁርስ ጋር መቋደስ የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን።

የሚል መግለጫ በነጭ ጠመኔ የተተየበበት ጥቁር ሰሌዳ ተሰቅሏል።

የውጭውን ዓለም የሚያሳየውን ባለመስታወት ግድግዳ ለይቶ ባለመሰላል አይነት መቀመጫ ላይ ተንጠላጥሎ ተቀመጠ።

ቢጫውን የብርሃን ባህር ሰንጥቃ የመጣች አስተናጋጅ በትግል በተሳቀ ፈገግታ ምን እንደሚፈልግ ጠየቀችው። የጀበና ቡና አዘዘ።

ዝናብ ሲሸሽ ትቶት የመጣውን ቀዬ በመስታወቱ ባሻገር ቁልቁል ይመለከታል። ህዝበ አዳም የስኳር ቅንጣት እንዳገኘ ሠራዊተ ጉንዳን ይርመሰመሳል። በሕይወት ማዕበል እየተጋፋ ከኑሮ ጎርፍ ለመትረፍ ሲውተረተር ይታያል። ነዳያን ምጽዋት ለመቀበል የዘረጉትን ምንጣፍ ለመጠቅለል ጎንብስ ቀና ይላሉ። ወጠምሻው ክራንቹንና ግሳንግሱን በብብቱ ወሽቆ ሶምሶማ ሲሮጥ አየው።

ተቀጣጣዩ የከተማ ባስ ሲያዘግም በደረቱ የሚሳብ ትል ይመስላል። ትናንሾቹ የቤት መኪኖች እየተሽሎከሎኩ እንደ ገበጣ ጉድጓድ ውሃ ያቆረ አስፓልት ላይ ሲደርሱ ካንድ ጎናቸው ያዘነብላሉ። ሕያዋኑም ግዑዛኑም እንዲህ ኼደው ኼደው የት እንደሚደርሱ በዓይነ ህሊናው ያስባል። በመለኮት አክናፍ በርሮ ሞትን ያላሸነፈውን ጊዜን ላይቀድሙ። በመስታወቱ ባሻገር ተንጣሎ እንደሚታየው ደመና የተባዘተበት አድማስ ጠርዝ የሌለው የሃሳብ ማጥ ውስጥ ተዘፍቆ ነፍሱን ያስጨንቃል።

ስስ ዝናብ ብን ብን እያለ ሲወርድ ይታየዋል። ጃንጥላ የዘረጉ መንገደኞች ለዓይኑ ካለው እርቀት አንጻር ቁልቁል ሲታዩ ተንቀሳቃሽ እንጉዳይ ይመስላሉ። ከደቂቃዎች በፊት እዚህ የ'ንጉዳይ ማሳ ውስጥ የጃንጥላ ሽቦ እንዳይወጋው አጎንብሶ ሲሽሎከሎክ እንደነበረ አስታወሰ ።

በቅርቡ የፈረሰ ጥንታዊ ግንብ ታንጾ የነበረበት ቦታ የሳር መስክ ለብሷል። ዐየር ላይ የሚዋልል ጥቁር ጃንጥላ አስተዋለ። ጃንጥላውን የዘረጋ ሰው ግን ሊታየው አልቻለም። ጃንጥው በሚንሳፈፍበት አግዳሚ ወንበር ላይ የብርሃን ውጤት የፈጠረው የግዑዝ ጥላ ይንቀሳቀሳል። በሁኔታው ባእድነት ተገርሞ መስተዋቱ ላይ የተጋረደውን የትንፋሽ ጉም በጣቶቹ ሞዥቆ ትክ ብሎ ለማየት ቢሞክርም በውል ሊለየው አልቻለም። መቃብር ፈንቅሎ የወጣ

ጽልማሞት ይመስላል። የጊዜን ውደት ሽሮ ዛሬ ላይ የተገኘ የትናንት ዘመን ሰው ይሆን ሲል አሰበ።

በውጭ በኩል ከሚያየው ትእይንት ዐይኖቹን ወደ ካፌው መለሰ።

በስተቀኝ በኩል ባለው የካፌው ግድግዳ ሃገሪቱ ከድህነቷ ጀርባ አሉኝ የምትላቸው አንጋፋ የሥነ-ጽሑፍ ውበቶች ካንገት በላይ ያለ ገጻቸው የተሞነጫጨረ በሚመስል ዘዬ ተነድፎ በወርቃማ ፍሬም ተገጥግጦበታል። የጸ.ገ.መ፣ ነብይ መኮንን፣ ደበበ ሰይፉ፣ መንግሥቱ ለማ፣ በዓሉ ግርማ፣ ስብሃት ገ/እግዚአብሔር፣ ገብረ ክርስቶስ ደስታ፣ ሙሉጌታ ተስፋዬ፣ ሰለሞን ደሬሳ። ይኼን ኹሉ የሥነ-ጽሑፍ አውራ በአንድ ሥፍራ ያሳረፉበት ፉካ ይመስላል። አዳም ረታ፣ ዓለማየሁ ገላጋይ፣ በእውቀቱ ሥዩም... በስም የሚያውቃቸውን እያየ ወደ ሌሎቹ ሲያማትር...

ባለ ተረከዝ ረዥም ጥቁር ቡትስ ያጠለቀ መንታ እግር ፊት እና ኋላ እየተራመደ ወደካፌው ሲዘልቅ ታየው። ከላዩ ላይ የዝናብ እንክብሎች የሚንጠባጠቡበት የተሸበሸበ የቢራቢሮ ክንፍ የሚመስል ቁልቁል የተዘቀዘቀ ጃንጥላ ተከትሎታል። ቡናማ ቀለም ያለው ክብ ሉል የተሰካበት የጃንጥላው የብረት እጀታ ሮዝ ቀለም የተቀቡ ጥፍሮች ያሏቸው ጣቶች በቄንጥ አንጠልጥለውታል። ዚግዛግ ዜማ የሚመታው ክር ቡትሱ ላይ የተጠመጠመ ሃረግ መስሎ ውሉን ሲቋጭ ሆን ተብሎ የተራቆተ ቀይ ገላ የሚመስል ባዶ የወሽመጥ ቅርጽ ከተቀደደለት ጥቁር ጉርድ ቀሚስ ውስጥ ብቅ እልም ይላል።

ሥነ-ጥበብ ካፌ የሚል ጽሑፍ በክር የተጠለፈበት የደንብ ልብስ የለበሰች ጃኒተር ከጃንጥላው ወደ ወለሉ የተንጠባጠቡ የዝናብ ርጋፊዎችን ለማጽዳት መወልወያ ይዛ ስትቆም ዓይኑን ከተከለበት ነቅሎ በምን ይሉኝ ሃፍረት ዙሪያ ገባውን ከቃኘ በኋላ አቀረቀረ።

ጠረጴዛው ላይ ዴና የተሰኘ መጽሔት ስኳር የተሰፈረበት ትንሽ ሙዳይ ተጭኖት መቀመጡን አስተዋለ።

ሙዳዩ ላይ በተሻጠ ማንኪያ ስኳር ዝቆ መዳፉ ላይ ከዘረገፈ በኋላ እንደ ክኒን ወዳ'ፉ ወረወረው። ጥቂት የስኳር ቅንጣቶች ሲረግፉ ሁሉንም ቀልቦታል። ሙዳዩን ሲያንቀሳቅስ ተደብቃ የነበረች ሆሄ ከመጽሔቱ ገላ ብቅ አለች። ከጓደኞቿ ጋር ቀላቅሎ ሲያነባት መዲና ይላል።

የመጽሔቱን ገጾች ባለፍ ገደም እየገለጠ ባ'ይኑ ዳሰሳቸው። ቀልብ በሚገዛ ዲዛይን የታተሙትን የውስጥ ቅጠሎች በጣቶቹ ኼደባቸው። ልዩ ቁስ እንደሚዳብስ ኹሉ ልስላሴውን አጣጣመ። ርዕሰ መዲና በሚል መሪ ርዕስ የተዘረዘሩ የጽሑፍ ቡፌ ገረመመ። በድጋሚ መጽሔቱን ከፊት ወደ ኋላ፣ ከኋላ ወደፊት። የመጽሔቱ ገጾች ሲርገበገቡ ያስነሱት የነፋስ ማዕበል ፊቱን ገረፈው። የወረቀት ጠረን ማገ።

ያዘዘው ቡና በትንሽ ጋቻ በሚትጎለጎል ነጭ የእጣን ጭስ፣ በእፍኝ የሚዘገኑ የፈንድሻ ፍሬዎች እና በጤና'ዳም ቅጠል ታጅቦ ቀረበለት።

ከጀበናው የሚቀዳው ጥቁር ፏፏቴ ፍንጃሉ ላይ ሲያርፍ ጎልቆ ቢስ ደቃቅ እንክብሎችን እየፈጠረ ኮረፈ። እንክብሎቹ ወዲያዉኑ ከሰሙ። እጣኑ ካለበት የካፌ ኑባሬ በነጭ ጢስ ጋረደው። ጭጋጋማ ዓለም ውስጥ የሰመጠ ሲመስለው ካ'ፍታ በኋላ ጭሱ የራሱን ተጥመልማይ ሰንበር እየተወ የቤቱ ቢጫ ብርሃን ውስጥ ሰረገ።

አጥፎ ያስቀመጠውን መዲና በድጋሚ ገለጠው።

በስኒ የተሰፈረለትን የቡና ባህር እንዳይፈጀው እየተጠነቀቀ በከንፈሩ ጠርዝ ፉፉፉፉፉፉፉፉፉፉፉፉፉፉፉፉፉፉፉፉፉፉ ፉፉት አለለት።

በቡናው ምሬት ፊቱን ከስክሶ ስኳር ጨመረ። በቀኝ እጁ የፍንጃሉን ቡና እያማሳለ ወደ ገለጠው መጽሔት ተመለሰ።

*****

መዲና፡ እስኪ አሁን ደግሞ በልጅነትህ ስላሳለፍከው ክረምት ትንሽ አጫውተን። ሥዕሎችህ የልጅነት መልኮች ያጠላባቸው መሆናቸው ያስታውቃል። 'ኖስታሊጂያ' ያረበበባቸው ናቸው።

ሠዓሊው፡ አዎ ትክክለኛ ነጥብ ነው። አየሽ፣ አሁን አሁን ካደግኩ በኋላ በ▯ያንዳንዱ ክረምት የሚያንዘረዝረኝ ብርዱ ሳይሆን የማይመለስ ልጅነቴን አብዝቼ መናፈቁ ይሆናል። በዕድሜ ንብርብሮሽ ስር ተቀብሮ የተዳፈነ የዘመኔ ፍርስራሽ የሚጠረግ ቢሆን ኖሮ ከፍተኛ ዋጋ የምሰጠውን ወርቄን አገኝ ነበር። እንደ እባብ ቆዳዬን ገሸልጬ የልጅነት ልባሴን የቀየርኩበትን ዘመን ለመለየት ግን አይቻለኝም። መቼ ነው ያደግሁት? ከልጅነት ወደ እድገት የተጠመዘዝኩበትን ኩርባ በውል አላውቀውም፣ አዬሽ።

[በጣቶቹ መካከል ያለችውን ሲጃራ ወደውስጥ መጦጦጦጦጦ ከአፉ ረዥም የጢስ ሰንበር አስወጣ።]

በኮልታፋ አንደበታችን፣ በህብረ ዝማሬያችን እንዲያሳድገን የለመንነውን ዝናብ ጠጥተን አደግን። ተመነደግን። ማደጋችንን ወንዶቹ በጢም፣ ሴቶቹ በአንጠንጨ አስመሰከርን። ጨዋታ ዝናብና ክረምት ተዋህደው ባቦኩት ጭቃ የተለሰነ ገላችን የማንነታችን ውል ነው። ዛሬ ዛሬ በዝናብ መካከል እየተሸከረከሩ "አሳድገኝን" የሚዘምሩ ሕፃናት የሉም። ቢኖሩም የሚሸከረከሩበትን ቦታ ህንጻ ወርሶታል። ጭቃ ማላቆጥ የሚፈልጉ ሞሳዎች ቢኖሩም የት ሄደው ማቡካት እንደሚችሉ አላውቅም። መረሬ ጭቃ ለማግኘት ምናልባትም ብዙ ኪሎ ሜትሮችን ማቆራረጥ የሚጠበቅባቸው የከተማ እንብርት ላይ ላሉ ታዳጊዎች ይህ ቅዠት ሊሆን ይችላል፤ ለ'ኛ ግን የዓይናችን ቆብ ሳይከደን እያየነው የተቀየረ እውነተኛ ኹነት ነው።

ክረምትና ዝናብ ተፈጥሮ ቀስተ ደመና እንደመቀነት ወገቧ ላይ አደግድጋ፣ እንደ ነጎድጓድ ከአድማስ እስከ አድማስ የሚያስገመግም መብረቃዊ ቁጣዋን የምታብለጨልጭባትን ሠፈሬን ያስታውሰኛል። በህልምና በእውን መካከል ባለ ድንግዝግዝ ዓለም ውስጥ ስትዳክር የከረመችው መንደር ክረምቱን በቆሎ ለመጥበስ የተቀጣጠለ ምድጃ ትሞቅና ትነቃለች። የሐምሌ ነፋስ ዛፎቹን ያሰግዳቸዋል። ደርቀው የበደኑ ቅርንጫፎቻቸውን እና ቅጠሎቻቸውን ያራግፋሉ። እና ሥዕሎቼ የሚፈክሩት ይህንን ሐቂቃ ነው፣ አየሽ? ዕድሜ ለክረምት እንጂ ሠዓሊው ብሩሹን ቀለም ነክሮ ንድፉን የሚያደምቅበት የመንደራችን ኑሮ የተሰመሩባቸው መስመሮች በጉልህ ይታያሉ። እንደ ዓይነ ርግብ የተከናነበችውን ቆሻሻ ትገልጣለች። ከቆዳዋ ላይ ጭቅቅቷን ፈትጎ የሚያነጻት ሰማያዊ ጸበሏ ነው ዝናብ።

እርጥበቱ የሚያሳሳ ጨሌ በየመንገዱ ጠርዝ የተቀመቀመ የጎረምሳ ጢም መስሎ ይበቅላል። መንገደኛ ጭቃ ያላቆጠበትን የጫማውን ጉንጭ ይጠርግበታል። የማገዶ እንጨት ተሸክሞ የሚሄድ ጌኛ በሳሩ ይጎመዥና የጌታው ለበቅ እየወደቀበትም ቢሆን አጎንብሶ ይነጨዋል እርሱን እያመሰኳ አገሩ ይገባል።

በበጋ ዘመድ ጥየቃ የመጣ ሰው በክረምት ሠፈራችን መኻል ቢገኝ ይደናገረዋል ይባላል። እንዲያውም የሠፈራችን መታወቂያ ከዚህ ኹነት ጋ እንደሚያያዝ ታሪካዊ መነሻውን የሚያወሱ ሰዎች ሲያወሩ ይሰማል። አንድ በጋውን በበረባሶዉ አፈር እየጋፈ ሲያልፍ ያሳበራት መንገደኛ ተዐቡን ተክሮ በክረምት ሲመለስ ለምልክት ያተመው አቧራማ የኮቴው ዱካ ይጠፋዋል። ይኼኔ ጭንቅላቱን ይዞ "እሪሪሪሪሪሪ" አለ። ቀማኛ ንብረቱን የገፈፈው የመሰለው የመንደሩ ሰው ተሰብስቦ ምን አጋጥሞት እንደሁ ሲጠየቅ "ኮቴዬ ጠፍታብኝ" ብሎ መለሰ።

[ነጎድጓዳማ ወፍራም ሳቅ። እንደ ጥጃ አንገቱ ላይ በወፍራም ክር ገምዶ ያንጠለጠላቸው ዶቃዎች፣ የብር ቀለበቶች ተቅጨለጨሉ።]

እና ይገርምሻል የሥዕሎቼ መዳረሻ እነዚህ ናቸው። አንቺም በአውደ ርዕዩ እንዳየሻቸው አንዳች መንፈስ ይጠናወተኝና የልጅነቴ ባህር ውስጥ ይከተኛል። ከእርሱ እያጠቀስኩ ነው ወደሸራ የምገለብጠው። የ'ኔ ቀለም ልጅነቴ ነው ማለት እችላለሁ። የኩሬ ውሃ አንበጫርቀን፣ ጭቃ አቡክተን የምንደሰትበትን ጊዜ ለመመለስ የማደርገው መፍጨርጨር ነው ልልሽ ነው።

መዲና: *ከጓደኞችህ ጋራ ትጫወቷቸው የነበሩ ...*

ሠዓሊው: *ኦ..! ልነግርሽ እኮ ነው...በጣም እንጂ...! ጨዋታስ ቢሉ ዝም ብሎ መሰለሽ?*

[እጁ ላይ ያለቀችውን ሲጃራ አሽትሬይ ላይ ተርኩሶ ቁሮዋን አስቀመጠ።]

እንዳልኩሽ ክረምት ዝናብ ብቻ አያመጣም፣ እረፍትና ጨዋታም ይከተሉታል። ትምህርት ቤት የሚዘጋበት ወቅት ስለሆነ ሁሉም የጨዋታ አራራውን ለመወጣት በጉጉት የሚጠብቀው ወቅት ነው። በሚያካፋ ዝናብ መካከል ፀሐይ ወጥታ ስናይ "ጅብ ወለደች" እንላለን። በቀለማት ህብር የተጎነጎነ ሰምበር ሰማይ ላይ ሲወጣ ቀስተ ደመና የሚባል መሆኑን አውቀናል። አሞሌ ጨውና ጠገራ ከሃገሪቱ አፈሚላዊ የመገበያያ ቁስነት ሲሰረዙ እኛ በቆርኪ ቁጥር ብዛት የሠፈራችንን ቁንጮ ባለሃብት እንሠፍራለን። የጨዋታ አሸናፊ ኹሉ የድሉን ፍሬ የሚለካው በቆርኪ ብዛት ነው፤ የጨዋታ አሸናፊ ከተረቺው እጅ ቆርኪ ይቀበላል፤ በክረምት የላቆጠው የሚዳችን ጭቃ ሲደርቅ የበጋ ጨዋታ ኳስ ነውና ፍልሚያውን ያሸነፈ ቡድን በተጠፈጠፈ ቆርቂ ተቆላልፎ የሚሰራ ዋንጫ ይበላል፤ ዋንጫ አሳምረው በመስራት የተካኑ የመንደራችን ጩጩዎች ከንፈራቸውን በፓስቲና በጮርናቄ ዘይት የሚያወዙበት ፍራንክ ለኪሳቸው አያጡም። ካልሲ ከተሰጣበት ገመድ ላይ ሁሉ አንስተን ኳስ እንሰራበት ነበር። ከሁሉ ከሁሉ በክረምት የተትረፈረፈ የጨዋታ እቃ ማምረቻ ጭቃ ነው፤ ጎራ ለይቶ የተድቦለበለ ጭቃ በመወራወር ተጋጣሚን ከምሽጉ ማባረር ከክረምት መሳጭ ጨዋታዎቻችን አንዱ ነበር።

እንደልብ የሚበቅለውን የሙጃ አንጓ በምላጭ ሰልጥጠን ስንነፋው የሠፈራችንን ሲንፎኒ ያሰማል። ሌላው መምች ነው። ጠፍጣፋ ድንጊያ ወደ ፊት እየወረወሩ በሌላኛው ድንጊያ መጀመሪያ የተጣለውን መምታት ነው፤ የሳተ መምቹን የመታውን ባላጋራ አዝሎ ድንጋዩ እስከተወረወረበት ርቀት ድረስ በጀርባ አዝሎ መውሰድ ይጠበቅበታል።

[ትከሻውን አልፈው ወደ ፊቱ የመጡ ኹለት የድሬድ ሎክ ዘለላዎችን ወደጀርባው መልሶ በላይተር አዲስ ሲጃራ ለኮሰ።]

ሠዓሊው: *ስለምን ነበር ያወራነው?*

[የቀለበት ቅርጽ ያላቸው የሲጃራ ጭሶች አከታትሎ ተፋ።]

መዲና: *በክረምት ስላላለፍከው ጊዜ እና ስለ ልጅነት ባልንጀ...*

ሠዓሊው: *ያ....!ያ...! ልመጣልሽ እኮ ነው። እሚገርምሽ... ቅድም እንዳልኩሽ የጊዜ ዑደት ይገርመኛል። ማለት ዓይንሽ እያየ ስትለወጭ። ግን የሚለውጥሽን ኃይል ማወቅና መለየት አይቻልሽም። በዚህ ኃይል ተገፍትሬ ከልጅነት ማማ ላይነው ቁልቁል ወደ እልቅና የወረድኩት።*

[ባ'መልካች እና በመሐል ጣቱ መካከል ያጣበቃትን ሲጃራ ባ'ውራ ጣቱ እየገፋ አሽትሬዩ ላይ ተመተመ። የአመድ ብናኝ ተነሳ።]

መዲና፡ ለሥዕሎችህ ሞዴል ያደረካቸው...

ሠዓሊው፡ ልክ ነሽ እውነትሽን ነው። አብዛኞቹን ብረሳቸውም ግን አብሮ አደጎች ነበርን። እምልሽ... ያው ስታድጊ እኮ አእምሮሽ ብዙ ነገር እየተወ ነው። ማለት ትዝታው እየደበዘዘ ነው። ቶሎ ቶሎ እያስታወስሽ ካላደመቅሽው። ሥዕሎቹም ቢሆኑ የነሱ ተች አላቸው።

[ሲጃራ የያዘበትን እጁን ዘርግቶ ለእይታ ወደቀረቡት ሥዕሎች ሲጠቁም ከሲጃራው ጫፍ አመድ ተንጠባጠበ።]

የተሰቀሉትን ሥዕሎቹን ተመልከቺ።

[ብቻውን ቆሞ በዝናብ የሚበሰብስ ብላቴና፣ ሰማይ ላይ ግማሽ ቅብ ቅርጽ ያሰመረ ቀስተ ደመና፣ የረገፉ የአሸን ከንፎች ወዘተ... ከሁሉም ጎልተው ይታያሉ። እጃቸውን መስቀለኛ ዘርግተው ዝናብ መካከል የሚሽከረከሩ ህጻናት፣ ቢጫ ብርሃን ውስጥ የምትጠልቅ ቡትስ የተጫማች እና ፍጥቅጥቅማ ጃንጥላ ያጠላች እንስት በአውደ ርዕዩ ከቀረቡ ሥዕሎች መካከል ይገኙበታል።]

እና እነ'ሱ እነ'ሱ በሆነ መንገድ ትናንቴን የተጋሩኝ የልጅነቴ መልኮች ናቸው፣ አብዛኞቹ የት እንደደረሱ ፍጹም አላውቅም። ጥቂቶቹ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በሩቁም ቢሆን ወሬያቸውን እሰማ ነበር። ከሁሉ ከሁሉ ግን ዝናብ ሲዘንብ እኛ ወደየቤት ስንኼድ አውላላ ሜዳ ላይ ብቻውን ቆሞ ዝናብ የሚደበደብ ልጅ ፍጹም ከህሊናዬ አይጠፋም። እና ሌላኛዋ መቅዲ ነች። መቅዲ ጋራ ሁለተኛ ዲግሪዬን ስሠራ ተገናኝተን ነበር፣ እና ብዙ ተለውጣ ነው ያገኘኋት። ደግሞ ወፍራለች። አውሎ እንዳያንሳፍፋት የምታሰጋ ነበረች'ኮ! 'ሚገርምሽ የ'ኔን ለውጥ ማስተዋል የቻልኩት በ'ርሷ መቀየር ነው። ግዙፍ እና ድንቡሽቡሽ ተክለ ሰውነቷ እና ቀይነቷ በቀላሉ ዓይነ ግቡ ያደርጓታል ...ፐ...!ፐ...! የእንግሊዘኛ ችሎታዋን ልነግርሽ አልችልም፣ እንዴት እንደምታግለበልበው። መቅዲ ኮሚኒኬሽን ላይ ልዩ ችሎታ ነበራት። ቶሎ ትግባባለች ከሰው። በዚሁ ሙያዋ አንድ የውጭ ተራድዖ ድርጅት ትሠራ ነበር። እና...

[ዓይኖቹ ያረገፏቸውን የዕንባ ጠብታዎች በጭፍኑ ጨምቆ ጉሮሮውን ጠረገ።]

ሶሪ። ካ'መታት በፊት በጮርቃ ልቡናችን ስንቦርቅ የነበርን ሰዎች ዛሬ አድገን ስንታይ የሚያሳድርብኝ ስሜት አለ ልልሽ ነው። እና ሕይወት እንደ አሸን ዕድሜ አጭር ናት አየሽ? ማለዳ እንደጤዛ ረግፈው የቀትሩ ወላፈን ያለፋቸውን ነፍሶች ሩሃችን እስካለች ድረስ ጽላት ቀርጸን በልባችን፣ በብሩሽ ቀለም ጠቅሰን ሸራ ላይ እናኖራቸዋለን። እና ከሞላ ጎደል ይኼን ነው ልልሽ የምችለው።

[ድንገት የሳሪያን ኮቱን የደረት ኪስ ፈተሸ። የተነፋነፍ ቅድ ሱሪዉን ኪሶች አዳረሰ። የከተማ አውቶብስ ቲኬት፣ ባዶ የሲጃራ ፓኮ፣ ቁራጭ ማስቲካ እያወጣ መለሰ።]

'ሚገርምሽ አልፎ አልፎም ቢሆን በል ሲለኝ ብሩሽ አስቀምጬ ብዕር እይዛለኹ፣ እና ካ'ሁኑ ኢንተርቪው ጋር የሚገናኝ ነገር ሳይኖረው አይቀርም ብዬ ያሰብኩት አንድ ጽሑፍ ነበረኝ። አየሽ፣ የሚጠቅም ከሆነ እንድታይው ብዬ ነበር። ግን...

መዲና፡ ችግር የለውም! በማንኛውም ጊዜ ሃሳብህን ብትልክልን ለማስተናገድ ዝግጁ ነን። ከክረምት እንውጣና እስኪ ደግሞ ስለ ጥቢ ወራት እናውራ። በዚያውም የወራት መፈራረቅ በሠዓሊ ዓይን ምን ዐይነት ቀለም እንደሚኖረውና ብሩሽ ለመጨበጥ፣ ቀለም ለማጥቀስ ወይም ደግሞ ሃሳብ ለማፍለቅ ያለው አስተዋጽዖ ምን እንደሚመስል ንገረን።

ውድ አንባቢያን ከሠዓሊው ጋራ ያደረግነውን ወግ ሁለተኛውንና የመጨረሻውን ክፍል በሚቀጥለው ህትመት ይዘን እንቀርባለን።

መጽሔቱን ባገኘበት አኳኋን አስቀምጦ፣ የጀበና ቡና የጠጣበትን ሂሳብ ከ10.00 ብር ተጨማሪ ጉርሻ ጋራ አኑሮ ቢጫ የብርሃን ባህር እየቀዘፈ ወጣ።

*****

ታሪኩን ደግሜ አነበብኩት። ግን ምኑም አይጥምም። በተለይ ደግሞ መጨረሻውን ልወጥነው አልተቻለኝም። ይኼንን ታሪክ የጻፍኩበትን ባለመስመር ሉክ አስቀምጬ ተንጠራራኹ። ይኼኔ ከዛሬ ነገ አነበዋለኹ ብዬ ያስቀመጥኩትን Ernest Hemingway የተባለ ዝነኛ ደራሲ የጻፈውን A Moveable Feast አገኘሁና አነሳሁት። የማንበብ ስሜት ላይ ባልሆንም የተወሰነ ገጽ ድረስ ስታገል ቆይቼ "....But sometimes when I was starting a new story and I could not get it going, I would sit in front of the fire and squeeze the peel of the little oranges into the edge of the flame and watch the sputter of blue that they made. I would stand and look out over the roofs of Paris and think, 'Do not worry" የሚል ሃሳብ ሳገኝ አንድ ክፍል ቤቴን ባ'ይኖቼ ጎበኘኋት። የብርቱኳን ልጣጭ እየቆሰቆስኩ ቆፈኔን የማላቅቅበት ነበልባሉ የሚንቀለቀል እሳት መሞቂያ ምድጃ የለም። በምትኩ በኤሌትሪክ ኃይል የሚሰራ ስቶቭ ተመለከትኹ። ከመቀመጫዬ ተነስቼ ቆምኹ። መስኮቱ ላይ የተንጠለጠለ እራፊ ጨርቅ ገልጬ ሳጮልቅ በውጭ በኩል ተረከዙ የተቦደሰ የ'ግር ሹራብ የልብስ ማስጫ ገመድ ላይ ተንጠልጥሎ ሲገለፍጥብኝ ታየኝ። እና እንደ ንሥር እያንጎበጎብኩ ከተማዋን ቁልቁል ማየት የሚያስችለኝ ጣሪያ ላይ መውጣት ባልችል በጎዳናዋ እንኳን ልረማመድ ብዬ ቆረጥኹ። ብን ብን ከሚለው ካፊያ ለመዳን ጥቁር ጃንጥላ ያዝኩ። አናቴ ላይ ቆብ ደፋሁ። ባለፈው ሳልቫጅ ከሚሸጥበት ገበያ የገዛሁትን ደንዳና ካፖርት ደረብኩ። አንገቴ ላይ ስካርቭ ጠመጠምኩ። ጽፎ ያላሳተመ ግን ራሱን ለራሱ ደራሲ በሚል ማዕረግ የሾመ ሰው ስመስል ይታወቀኛል።

ጽሑፉን ካስቀመጥኩበት አንስቼ ካኪ ወረቀት ውስጥ አስገብቼ የካኪው ጫፍ ላይ የተለጠፈች ቀጭን ወረቀት ልጩ የካኪውን ከንፈር አጣብቄ አሸግኹት። የመጽሔቱን አድራሻ ከካኪው የውጭ ገጽ ላይ ጽፌ እንደሚያነቡት እጓጓለሁ የሚል ይዘት ያለው በአስራ ስድስት መስመር የተቀነበበ አጭር ተማጥኖ አከልኩበትና ካኪወን ኩርቱ ፌስታል ውስጥ አስገባሁት።

*****

ባዕድ አውድ አጋጠመኝ። ከብዙ ዘመናት በኋላ እንደተከሰትኹ ሁሉ ባዳነት ተጠናወተኝ። ባር ባር አለኝ። እዚህም እዚያም አንገተ ሰጋጋ ማሽኖች የግምብ አምድ ተግተው ሲንዱ ይታያል። መንገዶቹ ተራምጄባቸው የማውቃቸው አይደሉም፤ ወይም ተለውጠዋል። ዙሪያ ገባው አፈር አፈር ይሰነፍጋል። እየፈረሰች ያለች ከተማ መኻል በህልሜ የተገኘሁ መሰለኝ። ታሪክ አቧራ ሲለብስ አስተዋልኩ፤ የየግል ደስታና ሳቃችንን አዋህደን የገነባነው የጋራ ትዝታ ቅጽር እንደዘበት ሲናድ ተመለከትኹ። የአዋቂዎች እርግማን የደረሰብን ይመስላል። ቅዠት አለመሆኑን ሳውቅ አማተብኹ። የትናንትን አሻራ ሰርዞ የራስን ቀለም ማጥቀስ ለማን እንደጠቀመ የታሪክ ዶሴዎች አልመዘገቡም፤ አዲስ ታሪክ መፈልሰፍ

ሲሳናቸው ነባር ማንነት አጥፍተው የተሰረዘ መልእክት ለመደረት የሚሞክሩ ግብዞች ሞልተዋል። ስማቸው አዲስ ነገር በመሥራት ሳይሆን ቅርስ በማፍረስ የሚጠራ ጎበዛዝት ሃገሩን ወረውታል፤ ትናንት በሰሩት ሥራ ስማቸው ከነሱ በላይ ሲሞገስ መስማትን የማይወዱ ቅናተኞች የሚኼዱበት የጥፋት ጎዳና ማፍረስ ነው፥ አዲስ መንገድ መቀየስን አያውቁምና። "ከ'ኛ በላይ ላሳር" በሚል ክፉ መንፈስ የተበከሉ አውሬዎች ከ'ነሱ ሌላ መልካም ስም ሲጠራ ደንብረው የሚሰብሩት ውድ ብርጭቆ ታሪክ ነው። ወልካፋ እግራቸው መገኘት በሌለባቸው ሥፍራ ላይ ሲያቆማቸው የመራገጥን እና የመንፈራገጥን ደመ ነፍሳዊ ባህርይ እንጂ የማስተዋልን ሰብአዊ ጠባይ አያንጸባርቁም። ዛሬንና ትናንትን ለማፋታት አጉል ገመድ ጉተታ ተያይዘዋል። ከትውልድ ሕልውና ተሰርዘው ዜጋ ተጉመጥምጦ ሲተፋቸው ከወደቁበት ሆነው ለመነሳት ሲፍጨረጨሩ፥ ያገኙትን ሲጨብጡ የታሪክ ምሰሶ ይገረሰሳሉ።

ይኼን እያብሰለሰልኩ በድንግርግር ስወናበድ በፊት የማውቃት የከተማ አውቶብስ ቆማ ሳያት ባይተዋርነቴ ለቀቀኝ። በህልም ከቆምኩበት ሥፍራ አሳፍራ በ'ውኔ ወደማውቀው ቦታ እንደምትወስደኝ ተስፋ አድርጌ፤ ጃንጥላዬን አጥፌ ከዶሴዬ ጋር ባንድ ያዝኩና በመኪናዋ መስኮት ሳንቲም የያዘ እጁን ሽቅብ አንጨፍርሮ ትኬት ለመቁረጥ ከሚጋፉ ከመንገደኛ ጎራ ገባኹ። እንደ ባህታዊ ጸጉሩን ሹሩባ ተጎንጉኖ በጀርባው የለቀቀ አንድ ጀብራራ ይታከከኛል። ትንባሆ ትንባሆ ይሸታል። ገንዘብ ለማውጣት ይውተፈተፋል። ኪሰ ብዙ ይሁን አልያ ገንዘብ የለው ኖሮ ባላውቅም ግን ብዙ ለፋ። ከ'ሱ ኋላ ትኬቴን ይዤ ልገባ ስል አንዲት እንስት "ከኪስዎ ነው የወደቀው" ብላ ወደመሬት አሳየችኝ።

በብዙ እጥፋት የተኮረታተመች ወረቀት ናት። ታጥፋ የከረመችበት ጠርዝ ላሽቶ መቀደድ ጀምሯል። ኪሴ ውስጥ የዘነጋኋት መስሎኝ እጥፋቷን ስዘረጋ የልብስ ሽቀጥ እና ደቃቅ አቧራ ተራገፈ። በውልግድግድ ጽሑፍ የተሞላ ገጽ አገኘሁባት። አልፎ አልፎ የማይም ፊርማ የመሰለ የቀለም አሻራ ታትሞባታል። የ'ኔ እንዳልሆነች ብረዳም ግን ልተዋት አልፈቀድኩም።

ከዚህ በፊት የማውቀውን የሠፈር ስም የጠሩ ተሳፋሪዎች "ወራጅ አለ!" ማለታቸውን ሰምቼ ከአውቶብስ ወረድኩ። አሁንም ሌላ ቅዝት አስቃዠኝ። ፖስታ ቤቱ ፈርሶ አረንጓዴ መስክ ተክቶታል። ጫፋቸው የደረቀ ዛፎች ከአካባቢያቸው ጋራ ለመላመድ እየታገሉ በድናቸውን ይናውዛሉ። የዘመናትን ጥሻ አቋርጦ እንደመጣ ሲራራ ነጋዴ በቁሜ ጠውልጌ ለመጽደቅ የሚጣጣሩትን ችግኞች መሰልኩ። መሐል ላይ የተተከለ ባለእንጨት አግዳሚ ወንበር ላይ ተቀመጥኩ። እና ያቺን የወረቀት ቅሪት በጥንቃቄ ገለጥኳት።

ብዥ በሚል ቀለም ሠዓሊ ሸራው ላይ እንደነደፈው ንድፍ ፍዝ ዓለም ውስጥ የሰነበተችው መንደራችን የምትደምቀው አሸንና ውሪ እኩል ውርውር በሚሉበት በክረምት ነው። ክረምት በቀናት እድሜ ውስጥ ነፍስ ዘርቶ ውርውር ከሚለው አሸን በብዛት የማይተናነስ ውሪ ከ'ናት ካ'ባቱ ኩይሳ እየፈለቀ የሠፈራችንን ገጣባ ሜዳ ይሞላታል። የበጋ እድፏን በዝናብ ውሃ ተለቃልቃ ጸአዳ ትለብሳለች። የበጋ አቧራ የጠገቡ ዛፎቿ ሙሉ ሻወር ወስደው አረንጓዴ ልምላሜ ይመለስላቸዋል። ኮሲ የተጠራቀመባቸው መንገዶቿ ክረምቱን አስታከው በሚፈጠሩ ጊዜያዊ ዥረቶች ያላሰለሰ ጥረት ቆሻሻቸውን አራግፈው ለመንገደኛ እግር ያሳሳሉ። ክረምት ሲመጣ ተብሎ በይደር የተቀመጠ የጓሮ ቆሻሻ ተወግዶ አፍንጫ በነጻነት አየር ይስባል። ክረምት መንደራችን ተፈጥሯዊ ለዛዋን የምትመልስበት የሁለት ወራት ቫኬሽን ነው። ስማይ ልሳኑን እንደዘጋ ፲፪ ወራት ሙሉ ጸሐይ ብቻ ብትንቦገቦግ ኖሮ የመንደራችንን የኑባሬ ገጽ ማሰብ ይከብዳል። ትርክምክም ቆሻሻዋን ተሸክማ እንደፈዘዘች የዘለዓለም ፍርዷን የምትፈጽም ተካዥ እና ናዋዥ ንድፍ ሆና በቀረች ነበር።

የበቆሎ እሸት የያዙ ጉሊት ሻጮች አዳፋ ተከናንበው የእሳት ፍም ከሚያቀጣጥሉበት

ምድጃ ስር ገሹ ሲጠባበቁ የክረምት ጎርፍ አምጥቶ የጣላቸው ግፋፊዎች ይመስላሉ። ጉሊት ወርዳ የምትቸረችረውን ኮተት በቅርጫት ተሸክማ ቁልቁል ስታዘግም የሚያለግ ቀንድ አውጣ ትመስላለች። መንገዱን የአሸን ክንፍ እርጋፊ ተጎዝጉዞበታል። ሕይወት ያላቸው አየር ላይ ብር ትር ይላሉ። ገሚሶቹ ከኩይሳቸው ወጥተው ለመብረር ያኮበኩባሉ። እነሱን በልተው ሆዳቸው የተወጠቀ እንቁራሪቶች መራመድ አቅቷቸው ያቃስታሉ። ቀዬና መንደሩ እንኳን ዘወትሯዊ አውዱ ይቀየራል። እብድ ሲያብድበት የሚውለው፣ መንገደኛ ሲጸዳዳበት፣ አላፊ አግዳሚ ቆሻሻውን ሲጥልበት የኖረው ኮሲ ተለውጦ አረንጓዴ ግምጃ ይለብሳል።

ከዚህ ሁሉ ውሪ ተነጥዬ ፊደል ለቀማ ላይ የተሰማራኹ ብላቴና እኔ ነኝ... መንደሬን ከማ'ይም አዘቅት ነጣ ላወጣ የዘመትኩ ነብይ እንደሆንኩ ሁሉ የበጋው ሳይበቃኝ በክረምትም ፊደል እንድቆጥር ይፈረድብኛል።

ማለዳ ለዘመቻ ስሰማራ በመጎምዣት ምራቄን እየዋጥኹ አልፌ የኼድኩት የጨዋታ ቡፌ ከፊደል ቆጠራ ስመለስ ደርቷል። አስኳላ የተዘጋለት ውሪ በየፊናው ይፈነጫል። ነገ ተነገ ወዲያ እጅ እጃቸውን ይዤ በሰንበሌጥ መጠቆሚያ የፊደል ገበታ ላይ እንዲያንጋጥጡ አድርጌ "ሀ በሉ..." "ለ በሉ..." ስል አስተካክሎ የማይጠራውን፣ የፊደል መልክ ባ'ግባቡ የማይለየውን ባ'ኮርባጅ ስነጨው እየታየኝ ብቻዬን እገለፍጣለኹ። ያቺ ኮልታፋ ምን ትሆን ስል አሰብኩ። "ጨ" ከሚል የውሪ ህብረ ዝማሬ መካከል "ቸ" የሚል ሰላላ ድምጽ ሲሰማ ወገቡን ባ'ኮርባጅ ቸብ ሳደርግ እየታሰበኝ ሳቅኹ።

ጉድጓድ ውስጥ ከቋተው ኩሬ የእንቁራሪቶች አርኬስትራ ይሰማል። የልጆች ዋይታና ጩኸት ታክሎበት ሠፈራችን የምታዜመው መወድሰ ክረምት ይመስላል። የድሪያ መርሃ ግብር ላይ የተሰማሩ ውሾች በህብረት ሆነው የጨዋታ ሜዳችንን ይዞሯታል። ሴቶች ሱዚ ይዘላሉ። ገመድ ወጥረው በቆሙ ኮረዶች ዙሪያ ግን አሸን ሳይሆን በኪሳቸው የፊት መስታወት ቁራጭ ይዘው የሚዞሩ ወንዶች ያንጣብባሉ።

የፊደል ገበታዬን ይዤ የጨዋታውን ገበታ ልቋደስ ዘለቅኹ። ዘንባባ ዝንጣፊ ሳይሆን ከአሸን ገላ ላይ የረገፈ ክንፍ ተጎዝጉዞ ጠበቀኝ። መቅዲ ሬዲሜድ ጉርድ ቀሚሷን ለብሳ ተራዋን ትጠብቃለች። ካልታወቀ የምድር ሰርጥ ባ'ውታረ ነፋስ ተገፍታ የመንደራችን ሰማይ ላይ ደርሳ የምትንሳፈፍ እፍዬ ገላ ናት፣ ቅለቷም ውበቷም ያሳሳሉ። ሮዝ ቀለም ያለው ቀሚሷ አየር ላይ እያንሳፈፉት እንደ ትንኝ ስታንጣብብኝ ደስታ ይውጠኝ ነበር። የፊደል ገበታ ላይ ያሉ ሆሄያትን አሸጋሽጌ እርሷን መሳግ እፈልጋለኹ። ሁሉም ሰው ያጠናታል። የአሸን ክንፍ ገጥሜ እፕፍፍፍ ብላት በ'ንቁራሪት እስልካተዋጠች ድረስ አየር ላይ ትኖራለች።

(?) ዋልካ ጭቃ ባላቆጠበት እጁ የሚመጠው ሸንኮራ የከሰል ጉማጅ መስሏል። ከአሸን ገላ የረገፉ በድን ክንፎች በተጣበቁባቸው ጣቶቹ አጥቅ መካከል የሸንኮራው ጭማቂ የእጁን እድፍ እያጠበ ይንጠባጠባል። እየመጠጠ የሚጥለው ልጣጭ ላይ የዝንብ መንጋ ሠፍሯል።

በጨዋታ ተወጥሮ ውርውር ከሚል ማቲ መዐት ተነጥሎ ሱዚ ከሚጫወቱት ሴቶች ጓላ ወደ'ኔ ሲንደረደር መጣና አለልማዱ በግ ይመስል በግንባሩ እየታከከ ሰላምታ ሰጠኝ። የተንኮሉን ቀንድ አብሮ ተላጭቶታል መሰል የሬንጅ ቅጠል ቀጥቅጦ የተቀባው ቋቁቻም አናቱ ሽፋኑ ያልተላጠ አረንጓዴ ዱላ ከረሜላ መስሏል። ወደጓላ አፈግፍጎ በቱስታ እንዳያፈልሰኝ እርሱን ሸሽቼ ስንደረደር በኪሴ ውስጥ እጁን ሲሰድ ተሰማኝ።

"ይፈተሽ!"... "ይፈተሽ!" የደቦ ጉርምርምታ ይሰማኛል። ዓይኔን ካ'ይኑ ሳልነቅል እጄን ቀስ አድርጌ ወደ ኪሴ ሰደድኩ። መስታወት እንደተቀመጠ ገባኝ። ከንፈሬን ነክሼ

አየሁት። የበጋ ቆሻሻዋውን ተሸክሞ ይገለፍጣል።

ቀደም ብሎ በተንኮለኛ አእምሮ የተጠለፈ የነገር መረብ ውስጥ እንደተጠመድኹ አወቅሁ። ትብታቡን እንዴት ፈትቼ እንደምወጣ እያሰላሰልኩ ስናውዝ በዘንዘራ ውስጥ ገብቼ የምዋኝ ትንሽ ክረምት አግቢ የሆንኩ መሰለኝ። ጩኸቱ "ይሰቀል...ይሰቀል!" የሚል መስሎ ተሰማኝ።

ሠፈራችንን ውሃ እንደጠጣ ሰፍነግ ጠምዝዞ የሚያሰጣት ጠንካራ መዳፍ የለም እንጂ ከውስጧ ተንጠፍጥፈው ሊወጡላት የሚገቡ ጭቅቅቶች ግን አሏት።

ውሃ ስንራጭ ፍፁም ሀሴት የሚያደርግ ህሊናችንን ማን ነጠቀን? ማደግ አይደል..? 'እደጉ! ተመንደጉ!' ብለው የመረቁን አበው ክልጅነት ጥዑም ህልም እየቀሰቀሱን እንደሆነ ያውቁ ነበር? እንደ ናና ከረሜላ የምናጣጥመው የታሪካችን ጣፋጭ ጊዜ በእድገት ስም የአዋቂነትን ካባ ደርበን ከመቆማችን በፊት ያለው ደግ ዘመናችን ነው። ዝልግልግ ለኻጭ ከደረታችን ስንጠርግ ድግግሞሽ ለበዛበት ጭጋጋማ ዓለም ራሳችንን እያጨን መሆኑን አናውቅም። ዛሬ ማን እርቃኑን ይፈናደሳል? ማንስ ይኮላተፋል? መንዘላዘልና መጀጀልም እንዲህ እንደጥላ ሲከተሉን ታሪክ የተቸከቸከበት ዶሴ መስሎ የወየበ ገጻችን ትናንት እና ዛሬ በሚባል የጊዜ ማእቀፍ ያንቀላፉት ባዶ ቅዠት መሆኑን ለራሳችን ዋሽተን ከአሽን ነፍስ የረዘመ ዘላለማዊ ሕይወት እንደምንኖር ኹሉ አንዳች የኑሮ ሽክም ተጭኖን ስንባዝን የመቃብር አፋፍ ላይ መገኘታችን ይገርመኛል። ትናንት መቼ ነበር? ይቺም ዕድሜ ሆና ለሞት ታጭተንባታል። አንድ የልጅነት ክረምት ሳይመረቅልን ጃጀን። ጃንጥላ ዘርግቶ እንደማጠፍ ያለ ውልብታ ነው ቆይታችን። እርሱን ቅጽበት ግን የዘላለም ለማድረግ መዋደቃችን ይገርማል።

በልጅነቴ የቦረቅኩባቸው ሜዳዎች ደመና ውስጥ ለመስረግ ታትረው በሚንጠራሩ የህንጻ ቁጥቋጦዎች ተሞልተዋል። ምናልባትም የብሳና ቁጥቋጦ ተከልለን ቁጢጥ ባልንበት የሆዳችንን ግሳንግስ ያስወገድንበት ቦታ ላይ የተገነባ ህንጻ ውስጥ ክራቫቱን የገጠገጠ ባለሱፍ ለሚያስተዳድራቸው ሠራተኞቹ ቀጭን ትእዛዝ እያስተላለፈ ይሆናል። ከ'ናታችን ማጎጸን ወጥተን ይቺን ምድር ስንቀላቀል የመንደር አዋላጅ ባልታጠበ ምላጭ የቆረጡትን እትብት በስንጥር እንጨት ጭረው የቀበሩበት ጓሮ የኤክስካቫተር ጥርስ ላይ ተሰክቶ ሲጎተት የዓይን እማኞች ሲያወጉ ተሰምቷል። ከ'ናቶቻችን መቀነት ሾልከው በመጥፋታቸው ለኩርኩምና ለአለንጋ ያጋለጡን ሽልንጎች የተጫናቸውን ትቢያ አራግፈው የወየበ ገላቸውን እያሳዩ ተገኝተዋል። የማንም ኪስ ውስጥ የሚያስገባ ዋጋ የላቸውም እንጂ፣ የጊዜ ንብርብር ሕልውናቸውን ሸሯልና። ከዘመናት በፊት የተነጠቅነውን ፍትሕ ለማስመለስ አንጮህም። ኮርኳሚዎቻችንም፣ ገራፊዎቻችንም በገዛ መቀነታቸው ተገንዘው መቃብር ወርደዋልና።

ከ'ለት ዕለት ጥድፊያ ፋታ ወስደን እስቲ አንዴ ጭቃ አቡክተን እንወራወር? እስቲ ለቅጽበት ውሃ እናንቦራጭቅ? በ'ድሜ እሳት ከክረምት በቆሎ ጋር ጠብሰን ለበላነው ልጅነት መታሰቢያ ሃውልት ብናንጽስ? ህብረ ዝማሬ ብናሰማስ? እኔ ሸራ፣ ብሩሽና ቀለም መርጫለኹ። እርስዎስ?

ሽርሽር

የት ይመስላችኋል?

ስለ ህንጻው ሰምታችሁ፣ በምስል አይታችሁት ተገርማችሁ በአካል disappointed የሆናችሁበት ቦታ የለም? ለእኔ ይህ ህንጻ የመጀመሪያው ነው።

ነገሩ እንዲህ ነው ፤ 2010 እና 2013 ላይ ላዘጋጀነው የአርኪቴክቸር እና የአርት ኤግዚቢሽን ከቦታው ሥፋትም አንጻር፣ እናም ያለምንም ክፍያ እንድንጠቀምበት ፈቃድ በማግኘታችን... እዚህ ሕንጻ ላይ ሥራ ጀመርን። በየወለሉ ላይ መሥሪያ ቤቶች እና የንግድ ሱቆች ቢኖሩትም ህንጻው ይህንን ያህል እንቅስቃሴ አልነበረውም። ከተሠራ እና ወደ አገልግሎት ከገባ ጥቂት ጊዜው ነው። የሚከራዩ ብዙ ክፍት ቦታዎች ከመኖራቸውም በላይ ቦታውን ለንግድ ፍቃድ ማውጫ እና ቢሮ አለኝ ለማለት ብቻ የሚጠቀሙበት ይበልጣሉ። ከእርሱ ሁሉ በላይ የህንጻው ግድግዳዎች በስብሰው ህንጻው አገልግሎት ሳይሰጥ አርጅቷል።

በስምምነታችን መሰረት Escalator የሚያሠሩ መሆኑን እና የተዘጉትንም እንደሚከፍቱልን ቢነግሩንም ካለው የሃገራችን ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ከኃይል መቆራረጥ ጋር ጨምሮ የህንጻውን 7/8 ደረጃዎች በእግር ለመውጣት ተገደድን። (ይህ ታዲያ በቀን ውስጥ ብዙ ጊዜ ሊሆን ይችላል።)

የውስጣዊ ጨለማነት/አነስተኛ ብርሃን፣ በቦታው ላይ እንቅስቃሴ አለመኖሩ፣ ከውስጥ ወደ ውጪ ወይም ከውጪ ወደ ውስጥ ምንም አይነት እይታ አለመኖሩ፣ ህንጻው ከሌላ ቦታ መጥቶ የተቀመጠ ባዕድ እንጂ ከአካባቢው ጋር ስምምነት ያጣ እንደሆነ ታዘብን። ከአንድ ከአስር ወር በፊት ለቢሮ ድርጅቱ የሰጠው ዋጋ ገበያው ላይ በቅርብ ካሉት ህንጻዎች ሲነጻጸር ከ30 ፐርሰንት በላይ ቅናሽ ነበረው።

ከሁለት ወይ ከሦስት ወር በፊት ቢሮ ቦታ መኖሩን ስንጠይቅ የዋጋ ለውጥ መኖሩንም አያይዘው ነገሩኝ። "ቴዲ እዚያ ሁለተኛ ቤት ከከፈተ በኋላ ዋጋ ጨምረ እኮ.." የሚል ነበር ምክንያቱ። ቴዲ ልደታ ኮንዶሚኒየም አካባቢ የሚገኝ ቆንጆ ቡና ቤት ነው። እርሱን ጨምሮ Flint food court በሚል አንድ አራት ምግብ ቤቶች የመጀመሪያው ወለል ላይ ተከፍተዋል።

ህንፃው በእነዚህ ዓመታት ውስጥ በሚያስገርም ሁኔታ አርጅቶ ግርግዳው ተፋፍቆ እና ቆሽሾ ይታያል። ብረት ያሉባቸው ግርግዳዎች ዝገው እና ተበላሽተዋል።

context/ ነባራዊ ሁኔታ ለግንባታም ሆነ ለህንጻ ንድፍ ከመሠራታዊያን መካከል ነው። የዚህ ህንጻ ዋነኛው ግድፈት ተብሎ ሊጠቀስ የሚያስችለውም ያለበት ቦታ ሙሉ በሙሉ ሊባል በሚያስችል ሁኔታ መቃረኑ ነው። በአካባቢው ላይ የኮንዶሚኒየም መኖሪያ ቤቶች መኖራቸው እና ከፍተኛ ህዝብ እና እንቅስቃሴ መኖሩ ትልቅ Potential ቢኖረውም ለዓመታት ህንጻው ብቻውን እንደቀረ ይሰማኛል። ህንጻው ለታሰበለት ዓላማ መዋል እንዳልቻለ እና አገልግሎቱን አቅም ወዳለው ፣ ከአካባቢውም ሆነ ፣ ከራሱ ከህንጻው ማንነት ጋር ተናናባቢ ወደ ሆነ Function ለምን እንዳልተቀየረ ትልቁ ጥያቄዬ ነው።

መፍትሔው ሰዎች ወደ ውስጥ እንዲመጡ እና እንዲንቀሳቀሱ፣ እንዲሁም እንዲቆዩ የሚያስችሉ ፕሮግራሞች፣ የምግብ ቤቶች፣ የጨዋታ ቦታዎች ፣ ጋለሪዎች እንዲሁም የሲኒማ ቤቶችን እና የጋራ የሥራ ቦታዎችን ማምጣት ነው። እነዚህ እና መሰል እንቅስቃሴዎች ሰዎች ወደ ህንፃው ውስጥ እንዲገቡ፣ እንዲቆዩ እና እንዲገበያዩ ያስችላል። Include a Food Court, Game Zones.

በስተመጨረሻም ይህንን የምግብ ዞን ለሠራው ባለሙያ ቺርስ! ቅርብ እንደመሆኑ መጠን ደጋግሜ የሄድኩ ሲሆን ንፁህ እና ቀላል መሆኑ እንድወደው አድርጎኛል። አረንጓዴ አትክልቶችን ማካተቱ ደሞ ቦታው ሕይወት እንዲኖረው እና እንዳይሰለች አርጓል። እያንዳንዱ ቦታ ራሱን እንደቻለ፣ የራሱን መልክ ሳይስት በጥሩ መልክ አብሮ ተዋሕዷል።

እንደየካራክተሩ የተጠቀመው ማቴሪያል እና ላይቲንግ ደግሞ ጥሩ ነው። በተለይ ድቁስ የሀበሻ ምግብ ቤት ላይ፣ ያልተሠራ እንጨት፣ ገመድ፣ ሰሌን መጠቀሙ የተለየ ውበት እና መልክ አስይዞታል። ባህላዊም ሆነ ዘመናዊ ምግባቸው በተለያየ ግዜ ሞክሬው ነበር። በጣም ቆንጆ ሲሆን፣ የደንበኛ አያያዛቸውም የሚያስመሰግን ነው።

Lideta Market in Addis Ababa, Ethiopia by Vilalta Arquitectura (aeccafe.com)











እንቆቅልሽ



በቅጽ5 ላይ ወጥቶ ለነበረው እንቆቅልሽ መልስ። ምን ያህሉን አግኝተዋል? በዚህኛው ቅጽ ያለውን እንቆቅልሽ ይሞክሩና መልስዎን በቴሌግራም ይላኩልን።



ፎነሮ 1

የሚከተሉትን ተረትና ምሳሌዎች ያሟሉ::

※ እንደመረብ ሽፍን/ 1፡ 13፡ */ 1፡ 13፡ 24፡ *፡ 4/ 12፡ 16፡ 13።
※ የምጣዱ እያለ / *፡ 1፡ 13፡ *፡ */ 5፡ 13፡ 17፡17።
※ እንኳን ተልባ ሸትቶሽ/ 1፡ 13፡ *፡ *፡ */ *፡ *፡ */ 14፡17/ 10፡ *፡ *፡ *፡ 3።
※ ዶሮ ከጮኸ የለም ሌሊት/ 22፡ 15/ *፡*፡*/ *፡ *፡ */ *፡ *፡ *፡10።
※ እንጀራ በሰፈድ/ 21፡ *፡ */ *፡ *፡ *፡12።
※ ለቁንጫ / 29፡ 2፡ 2፡ *።
※ ሠርግ በጭብጨባው/ 29፡ *፡ *፡ *፡ */ 9፡ 21፡ 9፡ 12፡ */ 30፡ 27፡ 11፡ *፡ 4።
※ በጨው ደንደስ/ 9፡ *፡ 9፡ */ 5፡ 11፡ *፡ 26።
※ የቡሄ ዕለት የደነቆረ/ *፡ */ *፡ 28/ *፡ 4/ *፡ *፡ *፡ 4።
※ ካላዩ አይበሳጩ/ *፡ 4፡ 6፡ 23/ 21፡ 30፡ *፡ *።
※ አልጠግብ ባይ/ *፡ 5፡ 18/ *፡ 12፡ *፡ 4።
※ ቅልና ድንጋይ ተማቶ/ 8፡ 27፡ */ *፡ */ 5፡ 17፡ 4፡ *።
※ *፡ 2፡ */ 30፡ 20/ ቤት አይገቡም።
※ ለመከራ የጣፈው/ 25፡ 19፡ *፡ 12/ 21፡ 30፡ 5፡ *፡ *፡ *።

ፎነሮ 2 (የቄሳርን ለቄሳር)

kwwsv://grfv.jrrjoh.frp/grfxphqw/g/4k8BSScHT5UoFF8U9j20UJi2wflt6WhM5/hglw?xvs=gulyhvgn&rxlg=433940652196403540605&uwsri=wuxh&vg=wuxh

---

ማስታወሻ!

የእንቆቅልሽ መልስ በቀጣይ ዕትም የሚወጣ ሲሆን ፡ የሞከሩትን በቴሌግራም፡ ፌሰቡክ እና ኢንስታግራም አድራሻችን ማጋራት አይርሱ።

መዲና ቅጽ 1 ቁጥር 6 ይህችን ትመስል ነበር።

ሀሳብ አስተያየት ካላችኹ በmedinadigitalmagazine@gmail.com ወይም t.me/bismartmb ቢልኩልን ለቀጣይ ዕትም እናርማለን።

በወደዱት አምድ ላይ ያዘጋጁት ጽሑፍ ካለ ለመላክ አያመንቱ። አድራሻ medinadigitalmagazine@gmail.com

መዲና መጽሔትን በሁሉም ሶሻል ሚድያዎች ላይ ይወዳጁ!

Medina መዲና

Medina መዲና

@Medinamagazine